ኅብረት ለምርጫ(CECOE)
የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ
Coalition of Ethiopian Civil Society Organizations for Elections

# የትዝብት ሪፖርት

## በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ሶማሌ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም የተካሄዱ ቀሪ እና ድጋሚ ምርጫዎች



ጥቅምት 28 ቀን 2017
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ማውጫ


ስለ ኅብረት ለምርጫ . . . . . . . . . . 2

ማሳሰቢያ . . . . . . . . . . 2

የምህጻረ ቃላት ዝርዝር . . . . . . . . . . 3

ምስጋና. . . . . . . . . . 4

ዋና ዋና ማጠቃለያዎች . . . . . . . . . . 5

ምዕራፍ አንድ፡ ዳራ. . . . . . . . . . 7

- የምርጫ ህግ ማዕቀፎች . . . . . . . . . . 7
- ፖለቲካዊ አውድ . . . . . . . . . . 8

ምዕራፍ ሁለት፡ የትዝብት ዘዴ . . . . . . . . . . 11

- የረዥም ጊዜ የትዝብት ዘዴ . . . . . . . . . . 11
- የድምጽ መስጫ ቀን ትዝብት . . . . . . . . . . 11
  - የታዛቢዎች ስምሪት እና የድምጽ መስጫ ቀን ትዝብት ዝርዝር መረጃ. . . . . . . . . . 12
  - የሪፖርት እና የመረጃ አሰባሰብ ሂደት. . . . . . . . . . 13
- የኅብረት ለምርጫ የመረጃ ማዕከል . . . . . . . . . . 13

ምዕራፍ ሣስት፡ የትዝብት ግኝቶች. . . . . . . . . . 14

- የቅድመ-ምርጫ ትዝብት ግኝቶች. . . . . . . . . . 14
  - የመራጮች ትምህርት . . . . . . . . . . 14
  - የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች እና ክርክሮች . . . . . . . . . . 17
  - የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ተሳትፎን በተመለከተ . . . . . . . . . . 19
- የድምፅ መስጫ ቀን የትዝብት ግኝቶች. . . . . . . . . . 20
  - የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል. . . . . . . . . . 20
  - አፋር ክልል. . . . . . . . . . 23
  - ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል (መስቃን እና ማረቆ የምርጫ ክልል) . . . . . . . . . . 27
  - ሶማሌ ክልል (ጅግጅጋ የምርጫ ክልል) . . . . . . . . . . 30
- የድህረ-ምርጫ ምልከታ ግኝቶች . . . . . . . . . . 34
  - በድህረ-ምርጫው የተከሰቱ ተቃውሞዎች. . . . . . . . . . 34
  - የመራጮች ግብረ መልስ (አስተያየት) በምርጫ ውጤቶች ላይ . . . . . . . . . . 34
  - በሲቪክ ምህዳሩ ላይ የነበሩ ገደቦችን በተመለከተ . . . . . . . . . . 34

ምዕራፍ አራት፡ የሪፖርት ግኝቶች ትንተና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .35
ቅድመ- ምርጫ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 35
የመራጮች ትምህርት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .35
የድምፅ መስጫ ቀን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .36
ድህረ-ምርጫ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .37
ምዕራፍ አምስት፡ መደምደሚያ እና ምክረ-ሃሳቦች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .38
መደምደሚያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 38
ምክረ-ሃሳቦች. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 38

# ስለ ኅብረት ለምርጫ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) ከ175 በላይ የሆኑ አገር በቀል የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ሲሆን፤ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። ኅብረት ለምርጫ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት፣ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 4748 በ2011 ዓ.ም ሕጋዊ ሰውነቱን ያገኘ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው።

ኅብረት ለምርጫ የተመሰረተበት ዋና አላማ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በምርጫ ምልከታ እና ክትትል፣ በመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ እና ከምርጫ በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶችን በመከላከል ላይ ያላቸውን ሚና ለማስተባበር እና ለማሳደግ ነው። ኅብረት ለምርጫ የምስራቅ እና የአፍሪካ ቀንድ የምርጫ ታዛቢዎች ኔትወርክ (East and Horn of Africa Election Observers Network (E-HORN)፣ የመላው አፍሪካ የምርጫ ታዛቢዎች አስተባባሪ መድረክ የሆነው የአፍሪካ የምርጫ ታዛቢዎች ኔትወርክ (African Election Observers Network (AfEONet) አባል እና በዓለም ዙሪያ ከ88 ሃገራት በላይ ቀጠናዊ ትስስር እና ድርጅቶችን አገናኝ ድርጅት የሆነው የአለም አቀፍ የሀገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች ኔትወርክ (Global Network of Domestic Election Monitors (GNDEM)) አባል ነው።

# ማሳሰቢያ

ይህ ሪፖርት ሊሳካ የቻለው በአየርላንድ ኤምባሲ እና በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ኤጀንሲ(USAID) ባደረጉት የላቀ የገንዘብ ድጋፍ ነው። በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ወይም አስተያየቶች የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ እንጂ የአየርላንድ ኤምባሲ፣ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ኤጀንሲ (USAID)፣ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም(NDI) ወይም ሌሎች አጋር ድርጅቶችን አቋም እና ምልከታ የሚያንፀባርቁ አይደሉም።

# የምህጻረ ቃላት ዝርዝር

**CECOE** የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ)

**NEBE**: የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ

**CSO**: የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች

**ACSO**: ኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን

**USAID**: የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ

**NDI**: ብሔራዊ የዲሞክራሲ ተቋም

**HoPR**: የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

**E-HORN**: የምስራቅ እና የአፍሪካ ቀንድ የምርጫ ታዛቢዎች ኔትወርክ/ትስስር

**AfEONet**: የአፍሪካ ምርጫ ታዛቢዎች ኔትወርክ/ትስስር

**GNDEM**: አለም-አቀፍ የሃገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች ኔትወርክ/ትስስር

**FDRE:** የኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

**LTO:** የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች

**GHC:** የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

**PwD:** አካል ጉዳተኛ  የሆኑ ግለሰቦች

**IDP:** የውስጥ ተፈናቃይ ግለሰቦች

# ምስጋና

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ(ኅብረት ለምርጫ) ተግባራዊ ሲያደርገው የነበረው የምርጫ መታዘብ ሂደት ከፍተኛ ሥራና ቁርጠኝነትን እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍን ይጠይቅ ነበረ። በመሆኑም ለትግበራው ኅብረት ለምርጫ የተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶችን ድጋፍ ባያገኝ ኖሮ መሳካቱ በጣም አስቸጋሪ ነበር። በመሆኑም ኅብረት ለምርጫ ከመጀመሪያው አንስቶ እስከመጨረሻው ሲያደርገው የነበረው የምርጫ ትዝብት ሂደት እና ይህንን ሪፖርት በማዘጋጀት ጠቃሚ አስተዋፅኦ እና ድጋፍ ላደረጉልን በርካታ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል።

በመጀመሪያ ለብሔራዊ ዲሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (NDI) ዳይሬክተር ለሆኑት ዶ/ር ፍራንክሊን ኦዱሮ፣ እና ለሁሉም የተቋሙ ሰራተኞች ላደረጉት የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ ኅብረት ለምርጫ ያመሰግናል። በተጨማሪም የአየርላድ እርዳታ ድርጅት (Irish Aid) እና የአየርላንድ ኤምባሲ ላደረጉት የፋይናንስ ድጋፍ ኅብረት ለምርጫ ማመስገን ይፈልጋል።

በተጨማሪም ኅብረት ለምርጫ  የአባላቱን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን - ማለትም Central Ethiopia Teachers' Association- CETA፣ Somali Non-State Actors Coalition- SONSAC፣  Redeem the Generation, Empathy for Life and Development Association- ELIDA፣ Development for All- DFA ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ልማት ማህበር እና የቦሮ ሺናሻ ልማት ማህበር በጠቅላላ ምልከታ ሂደት ላደረጉት አስተዋፅኦ  ያመሰግናል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ኅብረት ለምርጫ የምርጫ ሂደቶቹን ለመታዘብ ፈቃደኛ የሆኑ የአጭር ጊዜ እና የረዥም ጊዜ ታዛቢዎች ላበረከቱት አስተዋፅኦ እና ጥረት ከፍተኛ እውቅና ይሰጣል፤ያመሰግናል። በመጨረሻም ለድርጅቱ የቦርድ አባላት፣ ስራ አመራር፣ ሰራተኞች እና ለበጎ ፈቃደኞች ይህ ሪፖርት ስኬታማ እንዲሆን ስላደረጉልን ልባዊ ምስጋናን ኅብረት ለምርጫ ያቀርባል።

# ዋና ዋና ማጠቃለያዎች

## ዳራ

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በምርጫ ምልከታ እና ክትትል፣ በመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ እና ከምርጫ በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶችን በመከላከል ላይ ያላቸውን ሚና ለማስተባበር  እና ለማሳደግ የተመሰረተ ድርጅት ነው። ኅብረት ለምርጫ በሰኔ 16 2016 ዓ.ም የተካሄዱትን ቀሪን እና ድጋሚ ምርጫዎች ታዝቧል።

እነዚህ ምርጫዎች በአራት ክልሎች ማለትም ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ሶማሌ ክልሎች በሚገኙ የምርጫ ክልሎች ተካሂደዋል። የኅብረት ለምርጫ የምርጫ ታዛቢዎች የዚህን የምርጫ ሂደት ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና ከዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ጋር አብሮ መሄድ የመታዘብ ዓላም ይዞ ነበር። ይህ ዋና ማጠቃለያ የምርጫ ሂደቶችን ከመታዘብ የተገኙ ግኝቶች እና ምክረ ሃሳቦችን የያዘ ነው። ኅብረት ለምርጫ 13 የረዥም ጊዜ ታዛቢዎችን ከግንቦት 24 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ሰኔ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ተሰማርተው የቅድመ ምርጫ ሂደቶችን ታዝበዋል። በድምጽ መስጫ ቀን ኅብረት ለምርጫ ተጨማሪ 77 ታዛቢዎችን ስልታዊ የሆነ የስምሪት መንገድን በመጠቀም አመቺ እና ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ አሰማርቷል።

ታዛቢዎች ቀድመው የተዘጋጁ ቅጾችን በመጠቀም በቅድመ ምርጫ፣ በድምጽ መስጫ ቀን እና በድህረ ምርጫ ሂደቶች ላይ ያገኟቸውን ከመራጮች ትምህርት፣ የቅስቀሳ ተግባራት፣ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት፣ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ፣ የድምጽ ቆጠራ ጋር የተገናኙ የትዝብት ግኝቶችን አሰባስቧል።

## ዋና ዋና ግኝቶች

ኅብረት ለምርጫ ትዝብት ባከናወነባቸው ቦታዎች ሰላማዊ የምርጫ ሂድት ነበር። ኅብረት ለምጫ በተለያዩ የምርጫ ሂደቶች ላይ ከዚህ ቀደም ከተደረጉ ምርጫዎች አኳያ መሻሻሎች ተስተውለዋል። የድምጽ መስጫ ቁሳቁሶች መሟላትን በተመለከተ ጥሩ የሚባል አፈጻጸም እንደነበር ለማወቅ ተችሏል። የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ተደራሽነትን በተመለከተ ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች ጣቢያዎች አካል ጉዳት ላለባቸው መራጮች ተደራሽነት የተሻለ ነበር። በምርጫ ሕጉ የተደነገገው የምርጫ ጣቢያ አስፈጻሚዎች ቁጥር በተሻለ የተሟላ ነበር።

## ቅድመ - ምርጫ

ከቅድመ-ምርጫ  የመራጮች ትምህርት  ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ጉድለቶች ነበሩ። በቤንሻንጉል ጉሙዝ ሲሰጥ የነበረው የመራጮች ትምህርት የተደራሽነት እንዲሁም ከድግግሞሽ እጥረት አኳያ ውሱንነቶች ተስተውለዋል። የመራጮች ትምህርት ለሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ውሱብ የሆነ ተደራሽነት እንደነበረው ለመታዘብ ተችሏል። በቂ የገንዘብ አቅርቦት አለመኖር እንዲሁም የቋንቋ ውሱንነቶች የመራጮች ትምህርት ውጤታማነትን ገድበውታል። የምርጫ ቅስቀሳ ላይ የተጣሉ ገደቦች በአጠቃላይ ባይኖሩም አንዳንድ አሳሳቢ ጉዳዮች ነበሩ። በዚህም መሰረት በፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴዎች ላይ የተጣሉ ገደቦች በተለይም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተወዳደረው የቦሮ ሽናሻ ፓርቲ ላይ ገደቦች ተስተውለዋል። የጥላቻ ንግግሮች እና ጠብ አጫሪ ንግግሮች በተለይም በቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ሶማሌ ክልሎች ተመዝግበዋል።

## የድምጽ መስጫ ቀን

መሻሻሎች የታዩ ቢሆንም ከድምጽ መስጫ ሂደቶች አኳያ የተለያዩ ክፍተቶች ተመዝግበዋል። በአብዛኛው ትዝብት በተደረገባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለተሰለፉ መራጮች መጠለያ አለመመቻቸቱን ለመታዘብ ተችሏል። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሕጉ መሰረት በስፋት አለመቋቋማቸው ሌላው አሳሳቢ ግኝት ነው።  መራጮች ጣት ላይ የማይለቅ የጣት ቀለም ሳይደረግ እንዲመርጡ የተፈቀዱባቸው ሁኔታዎች በአፋር እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ተስተውለዋል። በተመሳሳይም በአፋር እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች በሕጉ በተቀመጠው መሰረት ማንነታቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ወይንም በምስክር ያልመረጡባቸው ሁኔታዎች እንደነበሩ ለመታዘብ ተችሏል።

## ድህረ ምርጫ

በአጠቃላይ የድህረ ምርጫ ሂደቱ ሰላማዊ የነበረ ሲሆን በአንዳንድ ሚዲያዎች ላይ የተጋነነ እና የሃሰት መረጃ ሲሰራጭ እንደነበር ሪፖርት ተደርጓል። የምርጫ ሕጉ በተጻረረ መልኩ በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ ከንቲባ ውጤት በቦርዱ ከመገለጹ ቀድሞ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ለህዝብ ይፋ አድርገዋል።

## ዋና ዋና ምክረ ሃሳቦች

1. በገጠር እና የተገለሉ ማህበረሰቦች የሚኖሩ ዜጎች ስለ መብቶቻቸው እና ስለምርጫ ሂደቶች በቂ መረጃ ባለማግኘታቸው በመራጮች ትምህርት ላይ ከፍተኛ ክፍተቶች መኖራቸውን መረዳት ይቻላል። መረጃ ያላቸው መራጮችን ለማዳበር፣ ኀብረት ለምርጫ የመራጮች ትምህርትን በባለብዙ መንገዶች የሚሰጥበት አካሄድን ይመክራል። የረዥም ጊዜ የመራጮች ትምህርት ፕሮግራሞችን በመንደፍ፣ ጥሩ የገንዘብ ድጋፍ ያለው የመራጮች ትምህርት ፕሮግራሞችን በማቋቋም፣ በመንደር ደረጃ የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ ቡድኖችን በማብቃት፣ የመራጮች ትምህርትን ከመደበኛው የሥርዓተ ትምህርት ጋር በማጣመር፣ የማህበረሰብ ሬዲዮዎችን በመጠቀም፣ የተለያዩ የሚዲያ መድረኮችን በመጠቀም እና ከሀገር ውስጥ እና ከአለም አቀፍ አጋሮች የማያቋርጥ የገንዘብ ድጋፍ የሚገኝበት መንገዶችን በማመቻቸት የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ የሚሻሻሉበትን መንገዶችን ኀብረት ለምርጫ ይመክራል።

2. ሲካሄዱ የነበሩ ቅስቀሳዎች በአጠቃላይ ንቁ የነበሩ ቢሆንም በፖለቲካ ፓርቲ እንቅስቃሴዎች ላይ ዕገዳዎች በተለይም በቦሮ ሺናሻ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ላይ ያነጣጠሩ ዕገዳዎች በዋናነት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እንዲሁም  የጥላቻ ንግግሮች እና ቀስቃሽ ንግግሮች በሶማሌ ክልል ውስጥ ተስተውለዋል። የምርጫ ቅስቀሳው ፍትሃዊ እና ሰላማዊ ሁኔታን ለማረጋገጥ፣ ምርጫ ቦርድ በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ የሚጣሉ ገደቦችን በንቃት እንዲከታተል እና መፍትሄ እንዲሰጥ ኀብረት ለምርጫ ይመክራል። የጥላቻ ንግግርን እና ቅስቀሳዎችን የሚከለክል አጠቃላይ የስነ ምግባር ደንብ መተግበር እና ከማህበራዊ ሚዲያ ድርጅቶች እና ከሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመተባበር ጎጂ የሆኑ የማህበራዊ ሚዲያ ይዘቶችን በንቃት ለመከታተል እና ሊያደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተጽዕኖ መከላከለ ይቻለል።

3. የድምጽ መስጫው ቀን በአመዛኙ ሰላማዊ የነበረ ሲሆን በድምጽ መስጫ ጣቢያ አደረጃጀት እና በምርጫ አስፈፃሚዎች ምደባ ላይ መሻሻሎች ተስተውለዋል። ነገር ግን ለመራጮች በቂ መጠለያ አለመኖሩ፣ የቅሬታ ኮሚቴዎች በስፋት አለመቋቋም እና የድምፅ አሰጣጥ ሂደቶችን በመተግበር ላይ ያሉ ክፍተቶች፣ የማይለቅ የጣት ቀለም ሳይደረግባቸው ድምጽ እንዲሰጡ የተደረጉ መራጮች መኖራቸው ተጠቃሽ ናቸው። የምርጫ ቀን ሂደቶችን ለማጠናከር ኀብረት ለምርጫ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች መጠለያን እንዲሟሉ፣ በምርጫ ሕጉ መሰረት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፣ በምርጫ ሂደቶች ላይ ለምርጫ አስፈፃሚዎች ጠንካራ ስልጠና መስጠት፣ የክትትል ዘዴዎችን መተግበር እና ለተፈጸሙ ጥሰቶች ተጠያቂነትን እንዲሰፍን ይመክራል።

4. የድህረ ምርጫው ጊዜ በአንፃራዊነት የተረጋጋ ቢሆንም የጅግጅጋ ከንቲባ ያለጊዜው የምርጫው ውጤት ምርጫ ቦርድ ይፋ ከመደረጉ በፊት ይፋ ማድረጉ ሂደቱ ለተሳሳተ መረጃ ያለውን ተጋላጭነት አጉልቶ ያሳያል። የምርጫውን ትክክለኛነት ለመጠበቅ እና የተሳሳቱ መረጃዎችን ለመከላከል የምርጫ ቦርድን በአደባባይ ውጤቱን ለማወጅ ብቸኛ ባለስልጣን መሆኑን እና ያለጊዜው በሚነገሩ መግለጫዎች ላይ እርምጃ በመውሰድ፤ በወጤት ላይ ትክክለኛ መረጃን ለማሰራጨት በምርጫ ቦርድ፣ በሚዲያ ተቋማት እና በሲቪል ማህበራት መካከል ትብብር በመፍጠር፣ የተሳሳቱ መረጃዎችን ለመለየት እና ውድቅ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ወሳኝ የአስተሳሰብ ክህሎት ዜጎችን ለማስታጠቅ የሚዲያ እውቀትን የማሳደግ ሥራዎች እንዲሰሩ ኀብረት ለምርጫ ይመክራል።

# ምዕራፍ አንድ፡ ዳራ

## የምርጫ ህግ ማዕቀፎች

### የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት

በኢትዮጵያ የ1987 ዓ.ም ሕገ-መንግስት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ስድስት ጠቅላላ ምርጫዎች ተካሂደዋል። እነዚህ ምርጫዎች የተካሄዱት የአብላጫ ድምፅ የምርጫ ስርዓትን በመከተል ነው። የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የፓርላሜንታዊ ሥርዓትን በመቅረጽ የፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶችን ዋና የሕግ አውጪ አካላት አድርጎ ሰይሟል።[1] በሕገ-መንግስቱ መግቢያ ላይ እንደተቀመጠው የሁሉንም ግለሰቦች እና ማህበረሰቦች መሰረታዊ ነጻነቶች እና መብቶች ለማስከበር ቁርጠኛ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መመስረት አስፈላጊ መሆኑን ይገልፃል።[2] የህገ መንግስቱ አንቀጽ 38 እንደሚደነግገው ዜጎች የመምረጥ፣ የመመረጥ እና በራሳቸው ጉዳዮች ላይ በቀጥታም ሆነ በመረጧቸው ተወካዮች አማካኝነት የመሳተፍ መብቶቻቸው መረጋገጥ የዲሞክራሲ ባህልን ለማስፋፋት እና ለማዳበር ጠቃሚ መሆኑን ይገልፃል። ይሄው ተመሳሳይ ድንጋጌ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በመረጡት የፖለቲካ ፓርቲ፣ የሠራተኛ ማኅበራት፣ የንግድ ድርጅቶች እና የሌሎች ቡድኖች አባል የመሆን መብት እንዳላቸው ያረጋግጣል።[3] በተጨማሪም ድንጋጌው የሚከናወኑ ምርጫዎች ሁሉን አቀፍ፣ በየጊዜው በሚካሄዱ፣ በእኩልነት መርህ ላይ የተመሰረቱ እንዲሁም በሚስጥራዊ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት መከናወን እንዳለባቸው ያስቀምጣል።[4]

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት የምርጫ አስፈፃሚ አካልን አስፈላጊነት በማመን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን (ቦርዱ) በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫን የማካሄድ ስልጣን ያለው ገለልተኛ አካል አድርጎ አቋቁሟል። በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 102 በፌዴራል እና በክልሎች ደረጃ የሚደረጉ ምርጫዎችን ነጻ እና ፍትሃዊ እንዲሆኑ እንዲሁም ገለልተኛ በሆነ መንገድ እንዲካሄዱ ከማንኛውም ተፅዕኖ ነጻ የሆነ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መቋቋም እንዳለበት ተደንግጓል። በተጨማሪም ይህ ድንጋጌ የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚሾሙ ይደነግጋል።

### የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 1133/2019)

ፍትሃዊ እና ግልፅ የሆነ የምርጫ ሂደት እንዲኖር ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚ አካል መኖሩ አስፈላጊ ነው። የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ2011 ዓ.ም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1133/2011 መሰረት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ እንደገና አቋቁሟል። ይህ አዋጅ ለምርጫ ቦርድ የተሰጠውን ሰፊ ስልጣን እና ተግባር የሚዘረዝር ሲሆን ከእነዚህ መካከልም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ምዝገባ መስጠት ፣ ህጉን መሰረት ባደረገ መልኩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እና በህገ መንግስቱ እና በምርጫ ህጉ መሰረት የሚደረጉ ምርጫዎችን ወይም ህዝበ ውሳኔዎችን በገለልተኝነት ማከናወን እና መከታተል ይገኙበታል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶችን ፈቃድ የመስጠት፣ የመቆጣጠር እና ክትትል የማድረግ፤ እንዲሁም በእነዚህ ድርጅቶች የሚሰማሩ የምርጫ ታዛቢዎችን የመከታተል ሥልጣን በአዋጁ መሰረት ተሰቶታል።[5] ቦርዱ የተሰጠውን ተልዕኮና ሃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችለው መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን አዋጁ ሰጥቶታል።

### የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ 1162/2019

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ የሚካሄዱ አምስት የምርጫ ዓይነቶችን በዝርዝር የሚያስቀምጥ ሲሆን ከነዚህም አንዱ የሆነው ድጋሚ ምርጫ ነው።[6] በአዋጁ መሰረት ቦርዱ በማንኛውም የምርጫ ሂደት ወቅት ከፍተኛ የሆነ የሕግ ጥሰት ተፈጽሟል ብሎ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ወቅት ወይንም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በቀረበ ክስ ላይ ምርጫ እንዲደገም የሚያደርግ ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት ድጋሚ ምርጫዎች እንደሚከናወኑ ተደንግጓል።[7] እንደዚህ አይነት ሁኔታዎች ሲከሰቱና ትክክለኛነታቸው በቦርዱ ምርመራ ሲረጋገጥ የድጋሜ ምርጫ በቦርዱ አልያም በፍርዴት ውሳኔ ይከናወናል።.

---

1 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣ አዋጅ ቁጥር 1 (1987)፣ ኅዳር 1987 ላይ የወጣ እና ነሐሴ 15 ቀን 1987 በሥራ ላይ የዋለ
2 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መግቢያ አንቀፅ 1, 2 and 5
3 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት፣ አዋጅ ቁጥር 1 (1987)፣ አንቀፅ 38
4 ዝኒ ከማሁ
5 የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ 1162/2019፣ አንቀፅ 7(2)
6 የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ 1162/2019፣ አንቀፅ 6
7 የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ 1162/2019

## የሃገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች እውቅና፣ የስራ ሂደት እና የስነምግባር መመሪያ(መመሪያ ቁጥር 5/2020)

"የሃገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች እውቅና፣ የስራ ሂደት እና የስነ-ምግባር መመሪያ (መመሪያ ቁጥር 5/2020)" የሃገር ውስጥ ታዛቢዎችን እውቅና የሚሰጥባቸውን መመሪያዎችን ያወጣል፣ የስራ አካሄዳቸውን በዝርዝር በመግለጽ እና መከተል ያለባቸውን የስነምግባር መርሆዎች በዝርዝር ያስቀምጣል። ይህ መመሪያ የምርጫውን ሂደት ግልፅነትና ታማኝነት በማስጠበቅ የምርጫ ክትትል ሂደት ገለልተኛ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ መካሄዱን ለማረጋገጥ ያስችላል።[8] መመሪያው በመግቢያው የመመሪያው ግቦች እና አላማዎች ተዘርዝረዋል። ምዕራፍ አንድ የመመሪያውን አጠቃላይ ይዘት እና የቁልፍ ቃላት ትርጓሜዎችን ይዟል። ምዕራፍ ሁለት የሃገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች የዕውቅና አሰጣጣጥ ሂደት እና በታዛቢነት ለመመዝገብ ምን ማሟልት እንዳለባቸውና እንዴት ማመልከት እንደሚቻል በዝርዝር ይገልጻል። ምዕራፍ ሶስት የሀገር ውስጥ ታዛቢዎችን መብቶች እና ግዴታዎች  ዝርዝር ያሥቀምጣል። ምዕራፍ አራት የምርጫ ታዛቢዎች መከተል ያለባቸውን የስነ-ምግባር ደንቦችና ሂደቶች ይዘረዝራል። የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ አንድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት የተሰጠው ዕውቅና ሊሰረዝ ወይም ሊታገድ የሚችልበትን ምክንያቶች ያብራራል።[9]

# ፖለቲካዊ አውድ

በ2010 ዓ.ም የመጣው የፖለቲካ ማሻሻያ ሂደትን ተከትሎ በርካታ የሕግ እና ተቋማዊ ማሻሻዎች ተደርገዋል። ከተደረጉት ማሻሻዎች መካከል በምርጫ ሕጉ ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን እንደገና ማቋቋም እና በምርጫው ምኅዳር ላይ የተካሄደውን ለውጥ ያካትታሉ። እንደአዲስ የተቋቋመው ብሄራዊ ምርጫ ቦርድም በ2012 ዓ.ም የሲዳማ ህዝበ ውሳኔን እንዲሁም በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም ላይ በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተካሄደውን ስድስተኛውን ጠቅላላ ምርጫ አካሂዷል።

ሆኖም ግን በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም የተካሄደው ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ በተለዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ተከስተው በነበሩ ግጭቶች፣ ቦርዱ ምርጫውን በሚያስፈጽምበት ወቅት ባጋጠሙት የሎጂስቲክስ ችግሮች እንዲሁም በኮቪድ 19 ወረርሺኝ ምክኛት የተለያዩ ተግዳሮቶች ገጥመውት ነበር። በአንዳንድ ክልሎች በተለይም በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና በአፋር ተከስተው የነበሩት ግጭቶች ምክንያት አገራዊ ጠቅላላ ምርጫ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረው አልፈዋል። እነዚህ ግጭቶች ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር ተዳምረው የፈጠሩት መሰል የጸጥታ ችግሮች ጋር በምርጫ ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል። እነዚህ ሁኔታዎች በተለያዩ ክልሎች ምርጫው እንዲራዘም እና እንደገና እንዲደራጅ ምክንያት ሆነዋል። በተለይም ምርጫው ሁሉን-አቀፍ እና ፉክክር በተሞላበት መልኩ እንዳይካሄድና በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ጉዞ ላይም  እንቅፋት የነበረና ኢትዮጵያ በወቅቱ ወደ ዲሞክራሲ በምታደርገው ግስጋሴ  ላይ ካጋጠሟት  ፈተናዎች መካከል አንዱ  ማሳያ ሆኖ አልፏል።

በመስከረም 2014 ዓ.ም በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም የተካሄደው ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ባልተካሄድባቸው አንዳንድ ምርጫ ክልሎች እንዲሁም የድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ውሳኔ በተሰጠባቸው ምርጫ ክልሎች ምርጫዎች ተደርገዋል። ከነዚህም መካከል በአሁኑ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በሚገኙት የመስቃን እና የማረቆ ምርጫ ክልሎች የተካሄዱ የምርጫ ሂደቶች ከፍተኛ ማስፈራሪያ እና ህገወጥ ድርጊቶችን አስተናግዋል። ለአብነት ያክል የታጠቁ አካላት (ሚሊሻዎች) በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት፣ መራጮችን ማስገደድና ማስፈራራት እና በጣቢያዎች የመራጮች ቁጥር አለመጣጣም  ችግሮች እንደነበሩ ቦርዱ ማረጋገጡን ሪፖርት አድርጓል። እድሜያቸው ያልደረሰ መምረጥ የማይችሉ ልጆች ሆን ተብሎ እንዲመርጡ ተደርገዋል፤  በምርጫ ጣቢያዎች  የነበሩ ታዛቢዎችም ዛቻ እና ማስፈራሪያ ደርሶባቸዋል። እነዚህን ጉዳዮች  ካረጋገጠ በኋላ ቦርዱ በሁለቱ የምርጫ ክልሎች የተሰጠው ድምፅ ተሰርዞ ምርጫው በድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ወስኗል።[10]

በተመሳሳይ ሁኔታ በሶማሌ ክልል ሙሎሙልቄ ምርጫ ክልል (የክልል ምክር ቤት) በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች ላይ በመዝገብ ላይ የፈረሙ መራጮች እና በሳጥን ውስጥ በተገኙ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች እና ወድቀው በተገኙ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች መካከል፣ እንዲሁም ለምርጫ ክልሉ በደረሰው አጠቃላይ የድምጽ መስጫ ወረቀት እና በድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ እና ከሳጥን ውጪ ካለው ጋር ሲነጻጸር ሊታለፍ (tolerate ሊደረግ) የማይችል የቁጥር ልዩነት በመገኘቱ፣ የድጋሚ ቆጠራ እንዲከናወን የወሰነ ሲሆን በምርጫ ክልሉ የተወዳደሩ ፓርቲዎች እና የግል እጩዎች በድጋሚ ቆጠራውን የሚታዘቡ ወኪሎች እንዲልኩ ጥሪ ተደርጎላቸዋል።[11]

በተጨማሪም በጅጅጋ ከተማ የምርጫ ክልል (የክልል ምክር ቤት) 26 ምርጫ ጣቢያዎች ላይ ለአንድ ፓርቲ ድምጽ እንዲሰጥ ተደርጓል የሚለው በብዙ ምስክሮች በመረጋገጡ፣ 13 የምርጫ ጣቢያዎች ታዛቢዎች መታዘብ አለመቻላቸው በመረጋገጡ ይህም ከውጤቱ ድምር ጋር ሲታይ ውጤት የሚቀይር መሆኑ ስለታመነበት ቦርዱ የድጋሚ ምርጫ እንዲከናወን ወስኗል።[12] ለዚህም ነበር በመጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ምርጫ ቦርድ ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ በጸጥታ እና በሎጅቲክስ ምክንያቶች ምርጫ ሳያሄድባቸው በቀሩ እንዲሁም በከፍተኛ የህግ ጥሰት ምክንያት  ድጋሚ ምርጫ  እንዲደረግ በተወሰኑባቸው ቦታዎች ቀሪ እና ድጋሚ ምርጫዎችን እንደሚያካሂድ ያሳወቀው።

---

8  የሃገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች እውቅና፣ የስራ ሂደት እና የስነምግባር መመሪያ (መመሪያ ቁጥር 5/2020)

9 ዝኒ ከማሁ

10 መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም ድምጽ አሰጣጥ ተከናውኖባቸው በአቤቱታ ምክንያት ይፋ ያልተደረጉ የምርጫ ክልሎችን አስመልክቶ የተሰጠ መረጃ | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ. (n.d.). https://nebe.org.et/am/node/671

11 ዝኒ ከማሁ

12 ዝኒ ከማሁ

በመጀመሪያ እነዚህ ምርጫዎችን ለማካሄድ የተያዘው ቀነ-ቀጠሮ ሰኔ 06 ቀን 2016 ዓ.ም ቢሆንም ይህ ቀን የኢድ አል አድሃ ወይም አረፋ በዓል ጋር በተመሳሳይ ቀን ላይ በመዋሉ ምክንያት እንዲራዘም ተደርጓል። ቦርዱ የድምጽ መስጫውን ቀን በመጀመሪያ ወደ ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም ኋላ ደግሞ ወደ ሰኔ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ቀይሯል።

ምርጫ ቦርድ በአጠቃላይ 1,261 የምርጫ ጣቢያዎችን በአራት ክልሎች ማለትም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በአፋር፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና በሶማሌ ክልል ለማደራጀት እቅድ አወጥቶ ነበር። ቦርዱ ባወጣው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የጅግጅጋ ምርጫ ክልል ቁጥር ሁለትን ሳይጨምር የመራጮች ምዝገባ ከሚያዝያ 29 እስከ ግንቦት 13 ቀን 2024 ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን፤ የእጩዎች ምዝገባ ደግሞ ከሚያዚያ 29 እስከ ግንቦት 8 ቀን 2024 ዓ.ም ድረስ ለማድረግ ቦርዱ የጊዜ ሰሌዳ አውጥቶ ነበር። ሆኖም አንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች በህዝባዊ እና ሃይማኖታዊ በዓላት ምክንያት ክፍት ባለመሆናቸው ምክንያት የመራጮች ምዝገባ እስከ ግንቦት 20 ቀን 2024 ዓ.ም ድረስ ቦርዱ ያራዘመ ሲሆን፤ የዕጩዎች ምዝገባ ደግሞ እስከ ግንቦት 14 ቀን 2024 ዓ.ም እንዲራዘም ተደርጓል።

በጅግጅጋ ምርጫ ክልልም ተከስተው በነበሩት በርካታ ችግሮች ምክንያት የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ መስጫ ቀን በተመሳሳይ ቀን ሆነው እስከ ሰኔ 16 ቀን 2024 ዓ.ም እንዲራዘም ተደርጓል። በወቅቱ የነበረውን በአንድ የምርጫ ጣቢያ የመራጮች ብዛት/ ጫና ለመቀነስ ሲባልም 52 ተጨማሪ የምርጫ ጣቢያዎች የተቋቋሙ ሲሆን ይህም አጠቃላይ የምርጫ ጣቢያዎች ድምር ወደ 1313 ከፍ እንዲል እንዲሁም በአንድ የምርጫ ጣቢያ ድምፅ የሚሰጡት የመራጮች ከፍተኛ ቁጥር ከ750 እንዳይበልጥ ተደርጎ ነበር።

ሠንጠረዥ 1: የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት በክልል

| **ክልል** | **የምርጫ ክልል ብዛት** | **የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት** | **የመራጮች ብዛት በአንድ የምርጫ ጣቢያ** |
|---|---|---|---|
| አፋር | 9 | 388 | ≤1,500 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 18 | 578 | ≤1,500 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 1 | 172 | ≤1,500 |
| ሶማሌ | 1 | 123 | ≤ 750 |
| የጣቢያዎች ድምር | 29 | 1,261 | |

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በአፋር፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በመካከለኛው ኢትዮጵያ (መስቃን እና ማረቆ) እና በሶማሌ (ጅግጅጋ) ለመራጮች ምዝገባና የምርጫ ቀን የምርጫ አስፈፃሚዎችን በመመልመል አሰልጥኖ አሰማርቷል። የማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና የሶማሌ ክልሎች የምርጫ አስፈፃሚዎች ከአዲስ አበባ ተመልምለው የተላኩ ሲሆን። አጠቃላይ የምልመላ እና የስምሪት ሂደቱ ሃያ ዘጠኝ (29) የምርጫ ክልሎችን እና 1261 የምርጫ ጣቢያዎችን ያካተተ ነበር። ለአፋር ክልል አንድ የዞን አስተባባሪ ለዞን አምስት፣ ሰማንያ ዘጠኝ (89) የምርጫ ክልል ኃላፊዎች (3 በምርጫ ክልል እና 4 ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ሶማሌ ክልሎች ) እና 1,261 የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች (5 በአንድ ምርጫ ጣቢያ) እንዲመደቡ ተደርጓል። በአጠቃላይ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር 491,681 ሲሆን ከእነዚህም መካከል 280,972 (57.14%) ወንድ መራጮች እና 210,709 (42.9%) ሴት መራጮች ነበሩ።



በአጠቃላይ በሁሉም ክልሎች የተመዘገቡ እጩ ተወዳዳሪዎች ቁጥርን በተመለከተ 12 የግል እጩዎች እና 348 የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎችን ያካተተ ሲሆን በአጠቃላይ 360 እጩዎች ለውድድር ቀርበው ነበር። ከእነዚህ ዕጩ ተወዳዳሪዎች መካከልም 23 እጩዎች (6.39%) ሴቶች ሲሆኑ፤ 337 (93.61%) ዕጩዎች ደግሞ ወንዶች ነበሩ።

የመራጮች ምዝገባን በተመለከተ ቦርዱ ሶስት የምዝገባ ሥርዓቶችን ተከትሏል። በዚህም መሰረት የመጀመሪያ የምዝገባ ሥርዓት "በጅግጅጋ 2" ምርጫ ክልል በሚገኙ 123 የምርጫ ጣቢያዎች በድምጽ መስጫ ቀን የተከናወነ የመራጮች ምዝገባ ነው። ሁለተኛው የምዝገባ አሰራር የመራጮች ምዝገባን እንደአዲስ ከሚያዚያ እስከ ግንቦት ወር መጨረሻ በአፋር፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች በተቋቋሙ 643 የምዝገባ ጣቢያዎች ተከናውኗል። በዚህም መሰረት 491,681 አዲስ መራጮች የተመዘገቡ ሲሆን ከነዚህም መካከል 280,972 (57.14%) ወንድ እና 210,709 (42.9%) ሴት መራጮች ተመዝግበዋል። ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫ የተወዳደሩ ዕጩዎች ብዛት በድምሩ 28 የነበረ ሲሆን፤ ከነዚህም መካከል 5 (17.86%) ሴት እና 23 (82.14%) ወንድ ዕጩዎች ለውድድር ቀርበዋል። ለክልል ምክር ቤቶች መቀመጫዎች የተወዳደሩ ዕጩዎች ብዛት በድምሩ 348 የነበረ ሲሆን ከነዚህ መካከል 71 (20.43%) ሴት እና 277 (79.57%) ወንድ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ነበሩ።

ሠንጠረዥ 2: ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተወዳደሩ ዕጩዎች ድምር እና የጾታ ስብጥር

| ክልል | የግል ዕጩዎች | የፓርቲ ዕጩዎች ድምር | ወንድ ዕጩዎች | ሴት ዕጩዎች |
|---|---|---|---|---|
| አፋር | 0 | 5 | 3 | 2 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 0 | 20 | 17 | 3 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 3 | 6 | 6 | 0 |
| ሶማሌ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| አጠቃላይ የዕጩዎች ድምር | 3 | 25 | 26 | 5 |

ሠንጠረዥ 3: ለክልል ምክር ቤቶች የተወዳደሩ ዕጩዎች ድምር እና የጾታ ስብጥር

| ክልል | የግል ዕጩዎች | የፓርቲ ዕጩዎች ድምር | ወንድ ዕጩዎች | ሴት ዕጩዎች |
|---|---|---|---|---|
| አፋር | 0 | 90 | 73 | 17 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 0 | 223 | 178 | 49 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 3 | 13 | 10 | 3 |
| ሶማሌ | 3 | 22 | 20 | 2 |
| አጠቃላይ የዕጩዎች ድምር | 6 | 348 | 281 | 71 |

# ምዕራፍ ሁለት፡ የትዝብት ዘዴ

ይህ ክፍል የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) የምርጫውን ሂደት ለመከታተልና ለመታዘብ የተጠቀምበትን ዘዴ ይዘረዝራል። የስነ-ዘዴው አቀራረብ አጠቃላይ  የምርጫውን ሂደት እና ነባራዊ ሂደቱን  ለመታዘብ እና ለማረጋገጥ ያስችል ዘንድ የረጅም ጊዜ እና የምርጫ ቀን የትዝብት ዘዴዎችን የያዘ ነው። ይህ የትዝብት ዘዴ የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያት ዘዴው  መሬት ላይ ያለውን የፖለቲካዊ ኑባሬዎች (ሁነቶችን)፣ የምርጫ ሂደቶች አፈፃፀም እና አጠቃላይ የምርጫውን ትክክለኛነት እና ታማኝነት በጥልቀት ለመረዳት ስለሚያስችል ነው።

## የረዥም ጊዜ የትዝብት ዘዴ

የኅብረት ለምርጫ የረዥም ጊዜ የትዝብት ዘዴ የምርጫውን ሂደት ከቅድመ-ምርጫ እስከ ድህረ-ምርጫ ምዕራፍ ድረስ በሚገባ ለመታዘብ የተነደፈ ሁሉን አቀፍ እና ስልታዊ አካሄድ ነበር። ዋና ዋና ዓላማዎቹም የፖለቲካ ምህዳሩን፣ የምርጫውን ሂደት አስተዳደር እና የዜጎችን ተሳትፎና የተሳትፎ ደረጃ መገምገም ነበር።

ኅብረት ለምርጫ 13 የረጅም ጊዜ ታዛቢዎችን ከአባል ድርጅቶቹ መልምሎ ምርጫው በተካሄደባቸው አራቱ ክልሎች  አሰማርቶ ነበር። እነዚህ ታዛቢዎች የምርጫ ህጎችን፣ የምርጫ ትዝብት ዘዴዎች፣ የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን እና የመታዘቢያ ቅጾችን (Observation Checklists) አጠቃቀም  ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰቷቸዋል። እነዚህ ታዛቢዎች ምርጫው  በሚካሄድባቸው ቦታዎችን ሁሉን አቀፍ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ በሚያስችል  ዘዴ ስልታዊ መልኩ በሁሉም ክልሎች ተሰማርተዋል።

ሠንጠረዥ 3: የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ስምሪት በክልል

| ክልል | የታዛቢዎች ብዛት |
|---|---|
| አፋር | 9 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 2 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 1 |
| ሶማሌ | 1 |
| ድምር | 13 |

የታዛቢዎች የቦታ ሥምሪት ዘዴ ተመጣጣኝ የትዝብት ዘዴን (Proportional Observation Methodology) የተከተለ ሲሆን ይህም ማለት ብዙ የምርጫ ጣቢያዎች  ላላቸው እንዲሁም ከፍተኛ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላሉባቸው አካባቢዎች በቂ ትኩረት እንዲያገኙ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነው። የምርጫ ታዛቢዎች ክትትል ካደረጉባቸው ጉዳዮች መካከል በቅድመ ምርጫው ወቅት ማለትም የምርጫ ቅስቀሳ እንቅስቃሴዎችን፣ የመራጮች ትምህርት እና አጠቃላይ የፀጥታ ሁኔታ ይገኙበታል።

በቅድመ ምርጫ የትዝብት ሂደት በድምሩ 32 ሪፖርቶች የተሰበሰቡ ሲሆን ይህም በፖለቲካው እና በምርጫ ምህዳር ላይ ስለነበረው ሁኔታ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ፈጥሯል። ታዛቢዎች በተለያዩ የምርጫ ሂደቶች ላይ የሚታዘቧቸውን የተለያዩ ክስተቶችን ማለትም በምርጫው ሂደት ላይ የሚሥተዋሉ ሁከቶችን፣ ዛቻ (ማስፈራራትን) ወይም ሌሎች ግድፈቶችን በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብና ለመመዝገብ የሚያስችሉ ደረጃቸውን የጠበቁ የመታዘቢያ እና የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችን ተጠቅመዋል። እነዚህ ሪፖርቶች ወቅታቸውን ጠብቀው እና ትክክለኛ የመረጃ ፍሰትን ተከተለው ለኅብረቱ የመረጃ ማዕከል ለትንተና ገብተዋል።

በድህረ ምርጫው ወቅት ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው ክልሎች የድምፅ ቆጠራውን እና ውጤቱን ይፋ የማድረግ ሂደቶችን ታዝበዋል። በድህረ ምርጫ ወቅት የተነሱ አለመግባባቶችን፤ ጉደለቶችን  እና ተያያዥ ክስተቶችንም ሪፖርት አድርገዋል። በዚህ የምርጫ ምዕራፍ ከታዛቢዎች በአጠቃላይ 11 ሪፖርቶች የተሰበሰቡ ሲሆን በድህረ ምርጫው ሂደት የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራትን፣  ቁልፍ የሆኑና መፍትሄ  የሚሹ አሳሳቢ ኩነቶችን በመለየት  አትተዋል።

## የድምጽ መስጫ ቀን ትዝብት

ኅብረት ለምርጫ በሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም የተካሄደውን የድምጽ መስጫ ቀን ዋና ዋና ሂደቶች ላይ አጠቃላይ ትዝብት አካሂዷል። የትዝብቱ ትኩረትም ከምርጫ ጣቢያዎች መከፈት ጀምሮ እስከ ድምፅ ቆጠራና የውጤት ማዳመር ድረስ  ያሉትን የምርጫ እንቅስቃሴ ሂደቶች የሸፈነ ነበር። ኅብረት ለምርጫ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል እና ካማሺ ዞኖች ከእንቅስቃሴ እና ከሎጅስቲክስ ጋር በተያያዙ ችግሮች ምክንያት ታዛቢዎችን ማሰማራት  አልቻለም ነበር። በዚህም ምክንያት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል እና ካማሺ ዞኖች የነበሩ የድምጽ መስጫ ቀን ሂደቶችን ለመታዘብ አልቻለም ነበር።

በድምጽ መስጫ ቀን ኅብረት ለምርጫ በአንድ የድምጽ መስጫ ጣቢያ ሙሉ ቀን ተቀምጠው የሚቀመጡ በአጠቃላይ 77 ቋሚ ታዛቢዎችን በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ሶማሌ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች አሰማርቶ ነበር። የታዛቢዎች ስምሪት ድልድልም እንደሚከተለው ነበር።

ሠንጠረዥ 4: ለምርጫ ቀን ምልከታ ተሰማርተው የነበሩ ታዛቢዎች ስምሪት በክልል

| ክልል | የታዛቢዎች ብዛት |
|---|---|
| አፋር | 20 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 37 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | 12 |
| ሶማሌ | 8 |
| ድምር | 77 |

የቋሚ ታዛቢዎች ስብጥር በፆታ




## የታዛቢዎች ስምሪት እና የድምጽ መስጫ ቀን ትዝብት ዝርዝር መረጃ

1. ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፡ ኅብረት ለምርጫ 21 ቋሚ ታዛቢዎችን በቤንሻንጉል ጉሙዝ በአሶሳ ዞን አሰማርቶ ነበር። ስምሪቱ አመችነትን መሰረት ያደረገ የስምሪት ዘዴን (Convenient deployment methodology) የተከተለ ሲሆን የዚህ የትዝብት ስነ ዘዴ ግብም ተደራሽ የሆኑ ቦታዎች ላይ በማተኮር፣ የትዝብቱን ተደራሽነት ከፍ ማድረግ ነው። ይህ የትዝብት ዘዴ የሎጂስቲክስ፣ የጸጥታ እና የእንቅስቃሴ ተግዳሮቶች ላሉባቸው አካባቢዎች የሚመከር የትዝብት ዘዴ ነው።

2. አፋር ክልል፡ በአፋር ክልል በሚገኙ 37 የምርጫ ጣቢያዎች በአጠቃላይ 37 ታዛቢዎች ተሰማርተው ነበር። ይህ ስምሪት በየወረዳው ከተቋቋሙት የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ታዛቢዎች እንዲሰማሩ በማድረግ የተመጣጣኝ ስምሪት ዘዴን (proportional deployment methodology) የተከተለ ነው።

3. የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፡ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በመስቃን እና በማሬቆ ወረዳዎች በሚገኙ 12 የምርጫ ጣቢያዎች 12 የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ተሰማርተዋል። የስምሪት ሂደቱም በሁለቱም ወረዳዎች ውስጥ ካሉት የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት ጋር በተመጣጣኝ ሁኔታ ታዛቢዎች እንዲሰማሩ በማድረግ የተመጣጣኝ ስምሪት ዘዴን (proportional deployment methodology) የተከተለ ነው።

4. ሶማሌ ክልል፡ ኅብረት ለምርጫ በሶማሌ ክልል በሚገኙ 8 የምርጫ ጣቢያዎች 8 ቋሚ ታዛቢዎችን አሰማርቶ ነበር። የታዛቢዎቹ ስምሪት ሂደትም አመቺነትን መሰረት ያደረገ የስምሪት ዘዴን (Convenient deployment methodology) የተከወነ ሲሆን፣ ተደራሽ እና ወሳኝ በሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ያተኮረ ነበር።

## የሪፖርት እና የመረጃ አሰባሰብ ሂደት

ኅብረት ለምርጫ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ያሰማራቸውን ታዛቢዎች የምርጫውን ቀን አጠቃላይ ሂደት እንዲታዘቡና በሰባት ቁልፍ ክንውኖች ላይ ሪፖርት እንዲያደርጉ አድርጓል። እነዚህ ክንውኖችም፡- ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስን፣ የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀትን፣ የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን፣ የምርጫ ጣቢያዎችን የአዘጋግ ሂደት እና የውጤት ቆጠራ እና የማዳመር ሂደት ናቸው። በዚህም መሰረት ታዛቢዎች በእነዚህ ተግባራት ላይ ቀኑን ሙሉ በጣቢያዎች ተገኝተው የታዘቡ እና ሪፖርቶችን ያቀረቡ ሲሆን በአጠቃላይ እያንዳንዱ ታዛቢ 85 የትዝብት ግኝቶችን ለኅብረቱ ሪፖርት አድርገዋል። በአጠቃላይ 595 ሪፖርቶች ወደ ኅብረቱ የመረጃ ማዕከል በድምጽ መስጫ ቀን ገብተዋል።

## የኅብረት ለምርጫ የመረጃ ማዕከል

ከታዛቢዎች ሪፖርት የሚደረጉለትን መረጃዎች በአንድ ቋት አሰባስቦ ትክክለኛነታቸውን እና ጥራታቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ሕብረት ለምርጫ አዲስ አበባ በሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤቱ የመረጃ ማዕከል አቋቁሞ ነበር። የመረጃ ማእከሉ 13 የመረጃ የመረጃ ባለሙያዎች የነበሩትሲሆን፤ ዋና ዋና ተግባራቸውም የሚከተሉት ነበሩ።

- ከታዛቢዎች የሚላኩትን ሪፖርቶች ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ
- ያልተሟሉ ወይም የተጓደሉ መረጃዎች ካሉ መለየትና መከታተል
- በምርጫ ቀን በታዛቢዎች ሪፖርት የተደረጉ አሳሳቢ ኩነቶችን ለመቀበል

የመረጃ ማዕከሉ የትዝብት ሂደቱን ተአማኒነት በማስጠበቅ፣ ሁሉም ሪፖርት የተደረጉ መረጃዎች በትክክል እንዲሰነዱ እና እንዲተነተኑ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

# ምዕራፍ ሦስት፡ የትዝብት ግኝቶች

## የቅድመ-ምርጫ ትዝብት ግኝቶች

የሚከተሉት ግኝቶች ከሰኔ 1 ቀን 2024 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2024 ዓ.ም ድረስ ሕብረት ለምርጫ አሰማርቷቸው ከነበሩ ታዛቢዎች በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። የኅብረቱ ታዛቢዎች በቅድመ-ምርጫ የፖለቲካ ምህዳር ላይ ሪፖርት አድርገዋል። በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ በቅድመ-ምርጫ ወቅት የነበረውን የፖለቲካ ምህዳር ላይ ያተኮሩ 32 ሪፖርቶችን ተቀብሏል።

## የመራጮች ትምህርት

በኢትዮጵያ የመራጮች ትምህርትን ተደራሽ የማድረግ ሃላፊነት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጠ ነው። በአዋጅ ቁጥር 1133/2019 አንቀፅ 7(2) እንደተገለፀው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ፍቃድ የመስጠት፣ የመከታተል እና የመቆጣጠር ስልጣን አለው። በተጨማሪም አዋጁ ቦርዱ የስነ-ዜጋ እና የመራጮች ትምህርት ለሚሰጡ የሲቪል ማህበር ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል። በቅድመ ምርጫ አጠቃላይ የፖለቲካ ምህዳር ትዝብት የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ፣ ተደራሽነት እና በሂደቱ ላይ ያገጠሙ ዋና ተግዳሮቶች ላይ ሪፖርት አድርገዋል። ከታች ያለው ማጠቃለያ በ32 የታዛቢዎች ሪፖርቶች ላይ የተመሰረተ ነው።

### 1. የመራጮች ትምህርት መኖርን በተመለከተ

የመራጮች ትምህርት ዜጎች ስለምርጫ ያላቸውን ግንዛቤ እና በምርጫ ላይ የሚኖራቸውን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ከፍ እንደሚያደርግ እሙን ነው። የመራጮች ትምህርት ዜጎች በመረጃ ላይ የተመሰረተ ምርጫ እንዲያደርጉ ይረዳል፣ በምርጫ ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ይጨምራል፣ በምርጫ ሂደት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ማጭበርበሮች እንዲቀንሱ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም የዜጎችን የዴሞክራሲ ባህል እንዲጎለብትና በዲሞክራሲያዊ ሂደት ላይ እምነት እንዲጥሉ ያደርጋል። ይህ ተሳትፎም ዜጎች በዲሞክራሲ ግንባታ ውስጥ ወሳኝ ሚና እንዲጫወቱ ያደርጋል። ይህንን በተመለከተም 21 (66%) የሚሆኑት የትዝብት ግኙቶች እንደሚያሳዩት የመራጮች ትምህርት በምርጫ ቦርድ እና በሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ተሰጥቶ ነበር። ከዚህ መካከልም በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የተሰጠው የመራጮች ትምህርት ብዛት 4 (12%) ብቻ መሆኑን ፤ 2 (6%) ደግሞ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አማካኝነት መሰጠቱን ሪፖርቶች ያመለክታሉ። በአንፃሩ 5(16%) የሚሆኑት የሪፖርቶች ግኙቶች እንደሚያመለክትቱት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ዞን ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት አልተሰጠም።

በመራጮች ትምህርት መስጠት ላይ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት ድርሻ




### 2. የመራጮች ትምህርት ተደራሽነትን/ ድግግሞሽን በተመለከተ

ተከታታይነት እና ቀጣይነት ያለው የመራጮች ትምህርት መሰጠት ዜጎች ስለምርጫ የሚኖራቸውን አጠቃላይ እውቀትና ግዛቤ ከፍ እንዲል ለማድረግ፣ ዜጎች በምርጫ ሂደቶች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ ለማጎልበት እና ፍላጎቶቻቸውዎችን እውን ለማድረግ አይነተኛ ሚና ይጫወታል። ይህንን በተመለከተም የሕብረት ለምርጫ የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች (LTOs) በተለያዩ አካላት ሲሰጡ የነበሩትን የመራጮች ትምህርት ተደራሽነትን ታዘበዋል። በዚህም መሰረት 13 (41%) የታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት የመራጮች ትምህርት በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ሲሰጥ ነበር። በተጨማሪም 2(6%) የሚሆኑት የትዝብት ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት በየቀኑ ሲሰጥ የነበረ መሆኑን ሲያመልክቱ፤ 12 (38%) የሚሆኑት የሪፖርቶቹ ግኙቶች ደግሞ የመራጮች ትምህርት አንድ ጊዜ ብቻ መሰጠቱን ያሳያሉ። አምስት (16%) ያህሉ የሪፖርቶቹ ግኙቶች ደግሞ ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት እንዳልተሰጠ ያሳያሉ፡፡

የመራጮች ትምህርት ተደራሽነትን/ድግግሞሽን የሚያሳይ ግራፍ




## 3. የመራጮች ትምህርት አካታችነትን በተመለከተ

አካታችነት ማለትም ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች (ሴተቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የተለየያየ ባህል፣ እምነትነና አስተሳሰብ ያላቸውን ግለሰቦች) ታሳቢና ተሳትፎ ማረጋገጥ የሁሉን-አቀፍ የመራጮች ትምህርት መለያ ገጽታ ነው። ይህንን በተመለከተም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የትዝብት ትኩረትም የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሂደት የተለያዩ የ ህብረተሰብ ክፍሎችን አካታችነት ላይ ያተኮረ ነበር። በዚህም መሰረት 18(56%) የትዝብት ግኝቶች የመራጮች ትምህርት በሁለቱም ፆታዎች፣ የሃገር ውስጥ ተፈናቃዮችን እና አካል ጉዳተኞችን ማካተቱን ሲያመለክት። ዘጠኝ (28%) ሪፖርቶች ደግሞ የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሂደቱ ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኛ ግለሰቦችን (PWDs) እና የውስጥ ተፈናቃዮችን (IDPs) ያላካተተ እንደነበር ያሳያሉ። አምስት (16%) የሪፖርት ግኝቶች ደግሞ ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት እንዳልተሰጠ ያሳያሉ፡፡.

የመራጮች ትምህርትን በመስጠት ረገድ የነበረው ከሰጪዎቹ ወገን ያለውን አካታችነት በተመለከተ 19(59%) የሚሆኑት የትዝብት ግኝቶች እንደሚያሳዩት የመራጮች ትምህርት ሲሰጥ የነበረው በሁለቱም ጾታ (ሴቶች እና ወንዶች)፣ በውስጥ ተፈናቃዮች(IDPs) እና አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች (PWDs) እንደነበር ያሳያሉ። በአንጻሩ 8 (25%) የሚሆኑት የትዝብት ግኝቶች ደግሞ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች የመራጮች ትምህርትን በመስጠት ላይ ተሳትፎ እንዳልነበራቸው ያሳያሉ። በሌላ በኩል 5 (16%) ያህሉ የትዝብት ግኝቶች ደግሞ ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት እንዳልተሰጠ ያሳያሉ።

## 4. የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ዘዴን በተመለከተ

የመራጮች ትምህርት የሚሰጥበት ዘዴ ወይም ተደራሽ የሚደረግበት መንገድ በመራጮች ትምህርት ተደራሽነት ላይ ወሳኝ ሚና አለው። ይህንን በተመለከተም ሕብረት ለምርጫ ባካሄደው ትዝብት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎችን መጠቀማቸውን ያሳያል፡፡ ከእነዚህም መካከል የፊት ለፊት መስተጋብርን (Face to face interactions) ጨምሮ የማስታወቂያ ሰሌዳዎችን፣ የህትመት ሚዲያዎችን፣ የጎዳና ላይ ትርኢቶችን፣ የሀገር ውስጥ ሚዲያ (ራዲዮ ወይም ቴሌቪዥን)፣ ማህበራዊ ሚዲያ ትስስሮችን (Social Media Networks) እና ሌሎች የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመራጮችን ትምህርት ተደራሽ ሲያደርጉ እንደነበር የህብረቱ የትዝብት ግኝቶች ያሳያሉ ።

ኅብረት ለምርጫ በደረሰው ዝርዝር ሪፖርት መሰረትም 18 (56%) የሚሆኑት ሪፖርቶች ባለድርሻ አካላት በመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ በርካታ ዘዴዎችን መጠቀማቸውን ያሳያሉ። በዚህም መሰረት 3 (9%) የሚሆኑት ሪፖርቶች ባለድርሻ አካላት የሃገር ውስጥ ሚዲያዎችን (ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን) ሲጠቀሙ የነበረ ሲሆን፣ ሌሎች 3 (9%) ሪፖርቶች ደግሞ የታተሙ ቁሳቁሶች እና የማስታወቂያ ሰሌዳዎችን መጠቀማቸውን አመላክተዋል፡፡ የጎዳና ላይ ትርኢቶችን ለማስተማሪያነት የተጠቀሙ መኖራቸውን 3(9%) ሪፖርቶች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ በተቃራኒ 5 (16%) የሚሆኑት ግኝቶች ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት አለመሰጠቱን ያሳያሉ፡፡

የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ዘዴን(ተደራሽ ማድረጊያ መንገዶችን) በተመለከተ የሚያሳይ ግራፍ




## 5. የመራጮች ትምህርት ይዘትን በተመለከተ

የመራጮች ትምህርት ይዘት ስለሚደረገው ምርጫ ምንነት/አይነት፣ አስፈላጊነት፣ሂደት እና ስለ የምርጫው ቁልፍ ገጽታዎች መራጮችን ለማሳወቅ እና ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረጉ ረገድ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። ስለሆነም ሕብረት ለምርጫ ለመራጮች ሲሰጥ የነበረውን የመራጮች ትምህርት ይዘትንም ገምግሟል።

በዚህም መሰረት 25 (78%) የሚሆኑት የትዝብት ግኝቶች የመራጮች ትምህርት የይዘት ትኩረት ምርጫው መቼ እንደሚካሄድ ማለትም ስለምርጫው ቀን ለመራጮች መረጃ ሲሰጡ እንደነበር ያሳያሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ 2 (6%) ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት ይዘት ስለምርጫው ቀን ለመራጮች መረጃ አለማድረሳቸውን ያሳያሉ፡፡ በተጨማሪም 25 (78%) ሪፖርቶች የመራጮች ትምህርት ይዘት መራጮች ለመራጭነት ምዝገባ ሲሄዱ እና በድምጽ መስጫ ቀን ይዘው መገኘት ስላለባቸው አስፈላጊ ሰነዶችን ዝርዝር ማካተታቸውን አመላክተዋል። ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ 2 (6%) ሪፖርቶች ሲሰጥ የነበረው የመራጮች ትምህርት ይዘት እንደዚህ አይነት ዝርዝር መረጃዎችን የተካተቱበት እንዳልነበር አመላክተዋል፡፡ አምስት (16%) የሚሆኑት የሪፖርቶች ግኝቶች ደግሞ ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት አለመሰተጠቱን ያሳያሉ፡፡

## 6. በመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

በመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ማናቸውም ተግዳሮቶች በሂደቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩና ሂደቱ ውጤታማ ወይም ስኬታማ እንዳይሆን የሚያደርጉ ናቸው። በዚህም መሰረት የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የመራጮች ትምህርት ተደራሽ በማድረግ ሂደት ላይ የነበሩ ተግዳሮቶችን ለይተው ሪፖርት አድርገዋል።

በዚህም መሰረት 10 (31%) የሚሆኑት ሪፖርቶች እንደሚያላክቱት የመራጮች ትምህርት ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለሌሎች ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተደራሽነት ላይ ውስንነት እንደነበር አመላክተዋል። አስር (31%) የሪፖርቶች ግኝቶች እንደሚያሳዩት በቂ የገንዘብ ድጋፍ አለማግኘት የመራጮች ትምህርትን በተፈለገው ልክ ተደራሽ ለማድረግ ፈተና እንደነበር ያሳያል። በተጨማሪም የቋንቋ እና የባህል ልዩነት መኖር በመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ ተግዳሮት ፈጥሮ እንደነበር 7 (22%) ሪፖርቶች አሳይተዋል፡፡ አምስት (16%) የሪፖርቶች ግኝቶች ደግሞ ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት እንዳልተሰጠ ያሳያሉ፡፡

በመራጮች ትምህርት አሰጣጣ ሂደት ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን የሚያሳይ ግራፍ



## የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች እና ክርክሮች

የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎችን እና ክርክሮችን መታዘብ አንደኛው የቅድመ-ምርጫ ትዝብት አካል ነው፡፡ የሕብረት ለምርጫ የታዛቢዎች ሲካሄዱ የነበሩትን የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻወች እና የክርክር መድረኮችን ተከታትለዋል፡፡ ትዝብቱ በዋናነት ትኩረት ያደረገው የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን፣ ለቅስቀሳ ዘመቻው ጥቅም ላይ የዋሉ ዘዴዎችን (የቅስቀሳ መንገዶችን)፣ በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻና ክርክር መድረኮች የተነሱ ጉዳዮችን (ይዘቶች)፣ ክርክሮች የተደራጁበትን መንገድ፣ የክርክሮችን ጥራት (Quality of Discourse)፣ እና የሚዲያ ሽፋንን የተመለከተ ነበር፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መሰረት በማድረግም ሕብረት ለምርጫ ስለተደረጉት የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች እና የክርክር መድረኮችን ታዝቧል። ከታች ያለው ማጠቃለያ ከ32 የታዛቢ ሪፖርቶች የተሰበሰበ ነው።

## 1. የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ተደራሽነት በተመለከተ

የሕብረት ለምርጫ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻን የትዝብት ቡድን የምልከታ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት 30 (94%) የሚሆኑት ሪፖርቶች የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ሂደቶች ሰፋ ያለ ተደራሽነት እንደነበራቸውና የፖለቲካ ፓርቲዎችም በንቃት እና በሰፊው የተሳተፉበት እንደነበር ያሳያሉ። ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ 2(6%) የሪፖርት እንደሚገልፁት ምንም አይነት የዘመቻ እንቅስቃሴ እንዳልነበረ አመላክተዋል። እንደታዛቢዎች ሪፖርትከሆነ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በሚገኙ በመስቃን እና ማረቆ ወረዳዎች እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአሶሳ ዞን ምንም አይነት የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ እንቅስቃሴ አልነበረም።

በሌላ በኩል 28 (88%) የሪፖርቶች ደግሞ ከምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች ጋር የተያያዙ ምንም አይነት ገደቦችን ወይም ክልከላዎች ያልታየባቸው እንደነበሩ ያመለከታሉ። በአንፃሩ ደግሞ በመተከል ዞን ወረዳ ዶቤን ቀበሌ የቦሮ ሺናሻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ በቀበሌ አዳራሽ ያዘጋጀውን ስብሰባ የቀበሌው አስተዳዳሪ የከለከሉበት ሁኔታ መከሰቱን አንድ የታዛቢዎች ሪፖርት አመልክቷል። እንደሪፖርቱ ገለጻ የቀበሌ አስተዳዳሪው የቦሮ ሺናሻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲን ለምርጫ ቅስቀሳ ስራዎች ያዘጋጃቸውን የማስታወቂያ ሰሌዳዎችን ጨምሮ ሌሎች ቁሳቁሶችን አውድሞበታል፡፡ ይህም ፓርቲው የቅስቀሳ ስራዎቹን እንዳይሰራ እና ውጤታማ የቅስቀሳ ስራዎችን ለመስራት እንዳይችል መሰናከል መፍጠሩን ሪፖርቱ አመላክቷል።

በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻው ሂደት የተላለፉ ቁልፍ መልእክቶችን በተመለከተ ፓርቲዎች የሚከተሉትን ርዕዮትና ፖሊሲ ለመራጮቻቸው ተደራሽ ማድረግና እና ለመራጮች ቃል በመግባት ላይ ያተኮሩ ነበሩ። በዚህ ረገድ 24 (75%) የሚሆኑት የትዝብት ሪፖርቶች የፖለቲካ ፓርቲዎች በዘመቻዎቻቸው በርካታ ጉዳዮችን አንስተው እንደነበር ሲያመለክቱ። አራት (12%) የሚሆኑት የሪፖርት ግኝቶች ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዘመቻዎቻቸው ወቅት ልዩ ልዩ እና ተጨማሪ ጉዳዮችን አጉልተው ሲያነሱ እንደነበር ያሳያሉ። 1(3%) ሪፖርት ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዘመቻዎቻቸው ወቅት ከደህንነት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ያነሱ መሆኑን ያሳያሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሁለት (6%) የሪፖርት ግኝቶች ምንም አይነት ምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ እንቅስቃሴ እንዳልነበረ አሳይተዋል።

## 2. የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ዘዴዎችን በተመለከተ

የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎቻቸው ወቅት ለመራጮች ተደራሽ ይሆኑ ዘንድ የተለያዩ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ዘዴዎችን ተጠቅመዋል። በዚህም መሰረት 18(56%) ሪፖርቶች የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅስቀሳዎችን ያካሄዱት ከአንድ በላይ ዘዴዎችን እና የተለያየ የአቀራረብ ስልቶችን በመጠቀም እንደነበር ያሳያሉ። ስድስት (19%) ሪፖርቶች ደግሞ ፓርቲዎች ከመራጮች ጋራ የአደባባይ ሰልፎችን በማድረግ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ሲያደርጉ እንደነበር አመልክተዋል። ሌሎች 5 (16%) ሪፖርቶች ደግሞ ፓርቲዎች ከመራጮች ጋር የአዳራሽ ስብሰባዎችንና የውይይት መድረክን በማዘጋጀት የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ሲያደርጉ እንደነበር አሳይተዋል፡፡ አንድ (3%) ሪፖርት ደግሞ ፓርቲዎች ማህበራዊ ሚዲያ ትስስሮችን (Social Medias Networks) በመጠቀም የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ሲያደርጉ እንደነበር ያመለከተ ሲሆን፤ 2(6%) ሪፖርቶችደግሞ ምንም አይነት የምርጫ ቅስቀሳ የዘመቻ እንቅስቃሴ እንዳልነበረ ያሳያሉ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ዘመቻዎቻቸው ሲጠቀሙባቸው የነበሩ የምርጫ ቅስቀሳ ዘዴዎችን/ስልቶችን የሚያሳይ ግራፍ



## 3. ግጭት ቀስቃሽ ወይም ከፋፋይ መልእክቶችን በተመለከተ

የሕብረት ለምርጫ የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ የታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት በአንዳንድ የቅስቀሳ መልእክቶች ይዘት እና አንድምታ ላይ ግጭት ቀስቃሽ እና በሌሎች ላይ ስጋቶችን የሚያጭሩ መልእክቶች በምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻው ወቅት ተስተውለዋል። ስድስት (19%) የሚሆኑት የትዝብት ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ቅስቀሳዎቻቸው ወቅት ግጭት ቀስቃሽ ፣ ከፋፋይ፣ አሳሳች መረጃ የያዙ እና የጥላቻ ንግግር ያዘሉ መለክቶችን ሲያስተላልፉ እንደነበር አሳይተዋል። ለ አብነትም የቦሮ ሺናሻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ በመተከል ዞን ባደረገው ዘመቻ የጥላቻ ንግግሮችንና ግጭት ቀስቃሽ የሆኑ መልዕክቶችን ሲያተላልፍ እደነበር ተስተውሏል። እነዚህን መሰል አደገኛ መልእክቶችም ሲተላለፉ የነበሩት በቀጥታ (ፊት ለፊት ሲደረጉ በነበረ መድረኮች) እና በተዘዋዋሪ ማለትም በድረ-ገፅ (በኦንላይን) መሰራጨታቸውን ሪፖርቶች አመልክተዋል። በተለይም በዘመቻው ወቅት የተገለገሉባቸው ቁሳቁሶች እና ንግግሮች ሌሎች ብሄረሰቦችን የሚያንቋሽሹ መልዕክቶችን እና አስተያየቶችን ያዘሉ ሲሆን ዓላማቸውም በአካባቢው ህዝብ መካከል ፍርሃትና አለመተማመንን ለመፍጠር እንደነበር ተስተውሏል ነው የተባለው።

በተጨማሪም በመተከል ዞን ቡለን ወረዳ በቦሮ ሺናሻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ እና ብልፅግና ፓርቲ መካከል ከፍተኛ ውጥረት ተፈጥሮ ነበር። ውጥረቱ በውንጀላ እና በግጭት ቀስቃሽ መልእክቶች የታጀበ ነበር። የቦሮ ሺናሻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲም ሆነ የብልፅግና ፓርቲ ደጋፊዎች እርስበርስ ግጭት ቀስቃሽ መግለጫዎችን ሲሰጡ ተስተውለዋል። ሁለቱም ወገኖች በማህበራዊ ሚዲያ የሀሰት መረጃ ሰያሠራጩ እና ዘመቻ ሲያካሂዱ እንደነበር፤ አንዱ በሌላው ፖሊሲ እና አላማ ላይ የሃሰት ወሬዎችን ሲያሰራጩ ተስተውሏል። በሌላ አጋጣሚም ሁለቱም ወገኖች የጥላቻ ንግግሮችን የሚያዘምቱ ጽሁፎችን በመያዝ በአደባባይ መውጣታቸውን የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ሪፖርቶች አረጋግጠዋል፡፡

በሌላ በኩል በጅግጅጋ ግጭት ቀስቃሽ እና ከፋፋይ የሆኑ መልዕክቶች የተስተዋሉ ሲሆን በተለያዩ ጎሳዎች መካከል ውጥረት አስከትሎ ነበር። የምርጫ ሂደቱም በጎሳዎች መካከል ውጥረት ያጠላበት ነበር። ከተስተዋሉ ግጭት ቀስቃሽ ቅስቀሳዎች ለአብነት፡ "እጩዎች የሚመረጡት በጎሳቸው ነው፤ እንዴት ከሌላ አካባቢ(ጎሳ) የመጣ ሰው እዚህ ይወዳደራል? መሬቱ የኛ ነው!" ("Candidates are selected by tribe; how can a person from another area compete here? The land is ours!") የሚል ይዘት ያላቸው ግጭት ቀስቃሽና ከፋፋይ መልዕክቶች ተላልፈዋል፡፡ የዚህ አይነት አነጋገር ዋና ዓላማም አንዱ ጎሳ ከሌላ ጎሳ የሚመጡ እጩዎችን ከመጡበት ጎሳ ጋር በማቆራኘት ለማግለልና እንዳይወዳደሩ ለማድረግ ነው።

ሌላው የሕብረተ ለምርጫ የረጅም ግዜ ታዛቢወች ሪፖርቶች እንደየሚያሳዩት በመተከል ዞን የማህበራዊ ሚዲያ ትስስሮች ገፆችን (Social Media Networks) ለጥላቻ ንግግሮችን እና ግጭት ቀስቃሽ ፅሁፎችን ለማሰራጨት ዋነኛ መሳሪያ ነበሩ። ሁለቱም ወገኖች በተለይም ደግሞ የብልጽግና ፓርቲ እና የቦሮ ሺናሻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ እነዚህን የማህበራዊ ሚዲያ ትስስሮች ገፆችን ተጠቅመው አፀያፊ መልዕክቶችን በማሰራጨት ውጥረት የበዛበት የፖለቲካ ከባቢን ፈጥረዋል። ምንም እንኳን እነዚህን መሰል የትዝብቶች ቢኖሩም፣ 23 (72%) ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት ግጭት ቀስቃሽ ዘመቻዎችን እንዳልታዘቡ እና መሰል ክስተቶች በሁሉም አካባቢዎች እንዳልነበሩ ያሳያሉ። እንዲሁም 2 (6%) የሚሆኑት ሪፖርቶች ደግሞ ምንም አይነት የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ እንደሌለ አረጋግጠዋል።

## 4. የምርጫ ክርክሮችን በተመለከተ

የህብረቱ የትዝብት ሪፖርት እንደሚያሳየው ዕጩ ተወዳዳሪዎች በፖሊሲዎቻቸው ላይ እንዲከራከሩና እንዲወያዩ የሚያስችል መድረክ ተፍጥሮ ነበር፡፡ መድረኩን ያመቻቹት ተቋማትም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ፣ የተለያዩ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች እና የትምህርት ተቋማት ነበሩ። ይሁን እንጂ እነዚህን የምርጫ ክርክሮች በማካሄድ ረገድ ውስንነት ተስተውሎ ነበር፡፡ የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት 3 (9%) ሪፖርቶች የምርጫ ክርክር መድረኮች መዘጋጀታቸውን ሲገልጹ፤ ከእነዚህ የምርጫ ክርክር መድረኮች መካከልም ጥቂቶቹ ክርክራቸውን በራዲዮ ማካሄዳቸውን ሪፖረቶች ይገልፃሉ፡፡ በአንፃሩ 29 (91%) የሚሆኑት የሪፖርቶች ደግሞ ምንም አይነት የተደራጀ የምርጫ ክርክሮች እንዳልተደረጉ ይጠቁማሉ። በእነዚህ የክርክር ሄደቶችም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ትኩረት ያተኮረው በክርክሩ ፍትሃዊነት እና ግልጽነት እንዲሁም የክርክሩን ይዘት/ጥራት( quality of debates) እንዲከታተሉ እና ሪፖርት እንዲያቀርቡ ነበር። በዚህም መሰረት 3 (9%) የሚሆኑት ሪፖርቶች ሁሉም ተፎካካሪዎች በእኩል ደረጃ ሃሳባቸውን የሚገልፁበት እድሎች ማግኘታቸውን እንዲሁም አወያዮችም በገልልተኝነት የክርክር መድረኮችን ሲመሩ እንደነበር ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል 29 (91%) ሪፖርቶች ደግሞ ምንም አይነት የተደራጁ የምርጫ ክርክሮች እንዳልተደረጉ ይጠቁማሉ።

የተካሄዱትን የምርጫ ክርክሮች ይዘትን በተመለከተም የክርክር ሂደቱ በአብዛኛው ተጨባጭ ውይም ፍሬ-አዘል ሃሳቦችን ከማንሳትና በእነሱ ላይ ከመከራከር ይልቅ እርስ በርስ መተቻቸት ወይም መነቃቀፍ ላይ ያተኮሩ እንደነበር 3 (9%) የሚሆኑት ሪፖርቶች ያሳያሉ። በሌላ በኩል ደግሞ 29 (91%) ሪፖርቶች ምንም አይነት የተደራጁ የምርጫ ክርክሮች እንዳልተደረጉ ይጠቁማሉ።

## የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ተሳትፎን በተመለከተ

ምርጫ ሲካሄድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ ሚዲያዎችን እና ጋዜጠኞችን እንዲታዘቡና እንዲከታተሉ ማድረግ እና ተሳትፏቸውን ከፍ ለማድረግ ምቹ የሆነ የሲቪክ ምህዳር መፍጠር የምርጫ ሂደቱ በግልጽና ታማኝ በሆነ መልኩ እንዲካሄድ ለማድረግ ወሳኝ ሚና አለው። በዚህም መሰረት የሕብረት ለምርጫ የምርጫ ታዛቢዎች ዋነኛ ትኩረት የነበረው የቅድመ ምርጫ ትዝብት ምልከታ በነዚህ ወሳኝ ባለድርሻ አካላት ላይ ማናቸውንም ተገቢ ያልሆኑ ገደቦችን እና ክልከላዎች መደረጉን ወይም አለመደረጉን መከታተልና መገምገም ነበር። ይህንን በተለመከተም የሕብረት ለምርጫ ከታዛቢዎቹ ያገኛቸውን ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ያቀርባል።

ሁሉም 32(100%) ሪፖርቶች እንደሚያመላክቱት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምንም አይነት ክልከላ ወይም ገደብ እንዳልነበረባቸው ያመላክታሉ። ጋዜጠኞች ወይም ሚዲያዎች ስለ ምርጫው ሂደት በነጻነት እንዳይዘግቡ ለማድረግ ያነጣጠሩ ጫናዎች፣ ገደቦች፣ እስራት እና ግድያዎች እንዳልነበሩ ሪፖርቶች ያሳያሉ። በተጨማሪም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በነጻነት እንዳይንቀሳቀሱ ለማድረግ ያነጣጠሩ ጫናዎች፣ ገደቦች፣ እስራት እና ግድያዎች አልነበሩም። ሪፖርቶቹ በቅድመ-ምርጫ ወቅት ማንነትን መሰረት ያደረጉ ማግለሎች፣ ጥቃቶች እና ማስፈራራቶች እንዳልነበሩ አትተዋል። ተያይዞም የምርጫው ሂደት አካታችነት እና መቻቻል የሰፈነበት እንደነበር ሪፖርቶቹ ይጠቁማሉ። ከዚህ በተጨማሪም ሪፖርቶቹ እስከ ድምፅ መስጫው ቀን ድረስ በሴቶች ላይ ምንም ዓይነት ትንኮሳ ወይም እንግልት እንዳልነበር በመግለፅ በምርጫ ሒደቱ ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል አስተማማኝ ሁኔታን እንደነበር ያሳያሉ።

## 1. የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴን በተመለከተ

የፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ አንድ ፍትሃዊ የምርጫ ሂደት መሰረታዊ አካል ነው። የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ትዝብታቸውን ለኅብረቱ ሪፖርት አድርገዋል። በዚህም መሰረት 3 (9%) የሚሆኑት ሪፖርቶች የፖለቲካ ፓርቲዎች በነጻነት እንዳይንቀሳቀሱ እና ስራቸውን እንዳይሰሩ የሚያደርጉ ጫናዎች፣ እገዳዎች ወይም ክልከላዎች እና እስራቶች እንደነበሩ ያሳያሉ። ከዚህ በተቃራኒ 29 (91%) የሚሆኑት ሪፖርቶች ደግሞ ፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እንደነበርና ምንም አይነት ገደብ ወይም ክልከላ እንዳልነበር ያሳያሉ። ከተከሰቱት ጫናዎች፣ እገዳዎች ወይም ክልከላዎች እና እስራቶች መካከልም የሚከተሉት ይገባቸዋል፡

- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ድባጤ ወረዳ ፡ የቦሮ ሺናሻ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ አባል የሆኑት አቶ ዘለቀ አብዲሳ በክልሉ ፖሊስ ታስረው የነበረ ሲሆን፤ የታሰሩበት ምክንያት ግልፅ አልተደረገም።
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ግልገል በለስ ከተማ፡ ሁለት የቦሮ ሺናሻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ወኪሎች የሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ለጊዜው ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ተደርጓል።
- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን ጉባ ወረዳ፡ የቦሮ ሺናሻ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ የሆኑ ለምርጫ በመወዳደራቸው ምክንያት ከሚሰሩበት የክልል የመንግስት በስሪያ ቤት ከስራቸው በጊዚያዊነት ታግደው ነበር። ይህም በስራ ላይ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ስጋት ፈጥሮ ነበር።

## 2. የምርጫ ቦርድ አሰራርን በተመለከተ

ፍትሃዊ፣ ግልፅ እና ተአማኒ የሆነ የምርጫ ሂደት እንዲኖር ነፃና ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚ አካል መኖሩ አስፈላጊ ነው። ይህም ማለት አስፈጻሚው አካል በነፃነትና ገለልተኛ በሆነ መልኩ በመንቀሳቀስ ውጤታማ የሆነ ስራ እንዲሰራና የምርጫው ሂደት ደግሞ ትክክለኛ እና ተአማኒ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህንን አስመልክቶም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የትዝብት ሪፖርቶችን አጠናቅረዋል። በዚህም መሰረት 31 (97%) የሚሆኑት ሪፖርቶች እንደሚያመላክቱት በምርጫ ቦርዱ የቅድመ-ምርጫ እንቅስቃሴ ሂደት ላይ ያጋጠሙ መሰናክሎች/ችግሮች እንዳልነበሩ ጠቁመዋል። በአንፃሩ ደግሞ 1 (3%) ሪፖርት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል ዞን ላይ የሎጂስቲክስ እጥረት ተፈጥሮ ነበር።

## 3. የሙስና/ ጉቦ የመስጠት/ ሙከራዎች በተመለከተ

ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ሃቀኛና ታማኝ ምርጫ ማካሄድ ከምንም በላይ አሳሳቢና ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ የሕብረት ለምርጫ የታዛቢ ቡድን ትዝብት አካሂደዋል። በዚህም መሰረት 30 (94%) ሪፖርቶች የሙስና ድርጊቶች ወይም ሙከራዎች እንዳልተስተዋሉ አመልክተዋል። ከዚህ በተቃራኒ 2 (6%) የሚሆኑት ሪፖርቶች ደግሞ በቅድመ ምርጫ ወቅት እጩ ተወዳዳሪዎች መራጮችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በጥቅማጥቅሞች በመደለል ድምፅ እንዲሰጧቸው ሙከራ ሲያደርጉ እንደነበር አመላክተዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞም በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ ከተማ የመንግስት ሰራተኛ ለብልጽግና ፓርቲ ድምፃቸውን እንዲሰጡ መልዕክት ሲተላለፍ ነበር። መልዕክቱ የተላለፈው በመንግስት ሰራተኞች የዋትስአፕ ቻናል (Whatsapp channel) ሲሆን መልዕክቱም ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ለብልፅግና ፓርቲ ድምፅ መስጠት ግዴታው እንደሆነ የሚገልፅ ሲሆን በምርጫ እለትም ሰራተኞቹ የምርጫ ወረቀታቸውን ፎቶግራፍ እንዲያነሱና እንዲያሳዩ የሚገልጽ እንደነበር ሪፖርቱ ያመለከታል።

# የድምፅ መስጫ ቀን የትዝብት ግኝቶች

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል

በድምፅ መስጫ ቀን ትዝብት በሎጅስቲክስ እና በበጀት ችግሮች ምክንያት የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በአሶሳ ዞን ብቻ እንዲሰማሩ የተደረገ ሲሆን በተለይም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል እና ካማሺ ዞኖች ምንም አይነት ታዛቢ ኅብረቱ አላሰማራም ነበር። ስለዚህ ይህ ሪፖርት የተጠናቀረው የአመችነት ዘዴን (Convenient Deployment Method) በመከተል በ20 የምርጫ ጣቢያዎች ተሰማርተው ከነበሩ 20 ተቀማጭ ታዛቢዎች (Stationary Observers) በተሰበሰበ መረጃ ላይ በመመስረት ሲሆን፤ እነዚህ ታዛቢዎች አጠቃላይ የምርጫውን ቀን ሂደት ሪፖርት አድርገዋል። ይህ ሪፖርት ወደ ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መድረስን፣ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን አከፋፈት፣ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት፣ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት፣የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አዘጋግ፣ የድምፅ ቆጠራ ሂደት እና የውጤት ማዳመር የተመለከቱ መረጃዎችን ይዟል። ለእነዚህ ቁልፍ ተግባራትም ሕበረት ለምርጫ 10 ታዛቢዎችን በከተማ፣ 8 ታዛቢዎችን ከፊል ከተማ እና 2 ታዛቢዎችን በገጠር በተቋቋሙ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች አሰማርቷል።

## ወደ ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መድረስን በተመለከተ

1. በድምጽ መስጫ ዕለት ከሚጠበቁ ወሳኝ ኹነቶች መካከል የምርጫ አስፈፃሚዎች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መድረስ አንዱ ነው። የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ልክ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ሲሆን ለማስጀመር እንዲቻል፤ የምርጫ ቦርድ አመራሮች እና ሰራተኞች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምፅ ለመስጠት መዘጋጀታቸውን ለማረጋገጥ የምርጫ ሰዓቱ ከመድረሱ በፊት ቀድመው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እንዲገኙ ይጠበቃል። ይህንን አስመልክቶም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች እንዳረጋገጡት በ18 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የምርጫ ሰራተኞች 12፡00 ሰዓት ከመሆኑ በፊት 11፡30 ላይ እንደተገኙ አረጋግጠዋል።

2. በሁሉም የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ማለትም 20 (100%) የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ወደ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ያለምንም ክልከላ ገብተው የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል።

3. በምርጫ ህጉ መሰረት ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ከ12፡00 ሰዓት በፊት መከፈት እንዳለባቸውና ከጥዋቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ ድምፅ መስጠት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ከታዛቢዎች የተገኘው የሪፖርት ግኝት እንደሚያመለክተው በ18 ምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ልክ ከጥዋቱ 12፡00 ሰዓት የተጀመረ ሲሆን፤ በ2 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ከጥዋቱ 1፡00 ሰዓት እስከ 3፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ የድምጽ መስጠት ሂደቱ መጀመሩን ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።

4. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት እንደ ወታደራዊ ካምፖች፣ የግል መኖሪያ ቤቶች፣ የፖሊስ ጣቢያዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የጤና ተቋማት፣ የመዝናኛ ማዕከላት እና የፖለቲካ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ላይ የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም ይከለክላል። ይህንን በተመለከተም የሕብረት ለምረጫ ታዛቢ ቡድን ምልከታ አድርጓል። በዚህም መሰረት በሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ህጉ ያልተከለከሉ ቦታዎች ላይ የተዘጋጁና የምርጫ ህጉን መሰረት እንደነበሩ ተመላክቷል።

5. በድምፅ መስጫ ቀን የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ የምርጫ ህጉ ከምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትሮች ባለ ርቀት ውስጥ ወይም ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ምንም አይነት የምረጡኝ ቅስቀሳ ዘመቻ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ እንደማይቻል የምርጫ ህጉ በግልጽ ይከለክላል። ከዚሁ ጋር ተያይዞም የሕብረት ለምረጫ ታዛቢ ቡድን እንዳረጋገጡት በሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች ሪፖርት የተደረገ ምንም አይነት የምርጫ ቅስቀሳ እንቅስቃሴ አልነበረም።

## የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን አደረጃጀት በተመለከተ

1. የምርጫ ጣቢያዎችን አደረጃጀት በተመለከተ 14 የምርጫ ጣቢያዎች በድንኳን የተሰሩ(የተዘጋጁ)፣ 4 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ህንፃ ላይ የተደረጉ/የተደራጁ ሲሆን 2 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ በዛፍ ጥላ ስር የተደረጉ/የተደራጁ የነበሩ መሆናቸውን የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች አረጋጋጠዋል።

2. ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሃይ የሚከላከል/ የሚያስጠልል መጠለያ መኖሩ በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ውስጥ ወሳኝ አካል ተደርጎ ይወሰዳል። በዚህም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ባደረጉት ምልከታ 7 የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች የነበሯቸው ሲሆን፣ 13 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሃይ የሚከላከሉበት መጠለያ እንዳልነበራቸው አረጋግጠዋል።

3. መራጮች በቀላሉ ድምጻቸውን ለመስጠት እንዲችሉ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ በሆኑ አካባቢዎች ሊቋቋሙ ይገባል። የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ለአካል ጉዳተኞች (persons with disabilities-(PWDs))፣ ለነፍሰ ጡር እናቶች፣ ሕፃናት ለያዙ ሴቶች እና አረጋውያን ወይም ለአቅመ-ደካማ መራጮች ተደራሽነትን ግምት ውስጥ ያሰገባ መሆን አለበት። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ግኝቶች እንደሚያሳዩት 14 የምርጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለነፍሰ ጡር እናቶች፣ ሕፃናት ለያዙ ሴቶች እና አረጋውያን ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገው የተደራጁ ሲሆኑ፣ 6 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ግን ይህንን ታሳቢ ያላደረጉና ተደራሽ አልነበሩም።

4. የድምጽ መስጫ ቁሳቁስ አቅርቦት መሟላት ለድምጽ አሰጣጥ ሂደት እጅግ ወሳኝነት አላቸው። ከድምጽ መስጫ ዕለት አስቀድሞ ሁሉም መራጮች ድምጽ መስጠት እንዲችሉ የምርጫ ቁሳቁሶች በእያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ጣቢያ ማሟላቱን ማረጋገጥ የጣቢያ ሃላፊው ይጠበቅበታ፡፡ የምርጫ ህጉ መሰረትም የእነዚህ ቁሳቁስ መሟላት ወሳኝነት እንዳለው ይገልፃል። ከእነዚህ ወሳኝ ቁሳቁሶች መካከልም፡ - የድምፅ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ የምርጫ ቦርድ ኦፊሴላዊ ማህተም፣ የማዳመሪያ ቅፅ፣ የውጤት መሳወቂያ እና የማመሳከሪያ ቅፆች፣ የማይፋቅ/የማይለቅ ቀለም፣ የድምፅ መስጫ ሳጥን (Ballot Box)፣ መከፈቱ የሚያስታውቅ ቁለፍ እና የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች ይገኙበታል። ይህንን አስመልክቶም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ባደረጉት ምልከታ በሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች እነዚህ ወሳኝ ቁሳቁሶች መሟላታቸውን ተረጋግጧል።

5. በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያ መሰረት የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የምርጫ ጣቢያው ኃላፊው የድምፅ መስጫ ሳጥኖች (Ballot Boxes) ባዶ መሆናቸውን ለታዛቢዎችና ለፓርቲ ተወካዮች እንዲያሳይ ያስገድዳል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ባደረጉት ምልከታ በሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያው ኃላፊው የምርጫውን ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን ለታዛቢዎችና ለፓርቲ ተወካዮች አሳይተዋል።

6. በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ህግ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለማስጀመር ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈፃሚዎች መገኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል። የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በታዘቡባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ከጀመሩ በፊት በአማካይ 5 የምርጫ አስፈፃሚዎች እንደነበሩ ለመታዘብ ተችሏል። ከእነዚህ ውስጥ በአማካይ ሁለት የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ሴቶች ነበሩ። የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የሥርዓተ-ፆታ ውክልና በሚመለከት በሶስት የምርጫ ጣቢያዎች ኃላፊዎቹ ሴቶች ሲሆኑ፤ በ17 ምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ወንድ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ነበሯቸው። በተጨማሪም በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ከምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች መካከል አካል ጉዳተኞች አልነበሩም።

7. እንደ ምርጫ ህጉ ድንጋጌ አንድ የምርጫ ጣቢያ ቢያንስ ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊኖረው ይገባል። በዚህም መሰረት ሕብረቱ በታዘበባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ሁለት ምርጫ ጣቢያዎች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የተቋቋሙ ሲሆን በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ኮሚቴዎች የተቋቋሙት ከምርጫ ህጉ በተቃራኒ ሲሆን በአብዛኛዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ምንም አይነት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ያልተቋቋሙ መሆኑን የሕብረቱ ታዛቢዎች ዘግበዋል።

8. የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በምርጫ ጣቢያዎች መኖራቸውን በተመለከተ በ18 የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች መኖራቸውን የሕብረቱ ታዛቢዎች ገልጸዋል።

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን በተመከለተ

1. የድምጽ-መስጫ ጣቢያዎች ከተከፈቱ እና ከተደራጁ በኋላ ቀጣዩ ተግባር የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ነው። በዚህም መሰረት ሕብረት ለምርጫ በድምጽ መስጠት ሂደት ላይ ከታዛቢዎቹ የሰበሰባቸውን ግኝቶች እንደሚከተለው አቅርቧዋል፡፡

2. በሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች የሕብረቱ ለምርጫ የታዛቢዎች በድምጽ መስጫ ሂደት ውስጥ ከምርጫ ጣቢያዎቹ እንዲወጡ አልተጠየቁም/ አልተደረገም።

3. የሕብረቱ ታዛቢዎች እንዳረጋገጡት በ19 የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ አቅመ ደካሞች፣ ነፍሰ ጡር እናቶች እና ሕፃናትን/ልጆች ለያዙ ወላጆች ቅድሚያ በመስጠት እንዲመርጡ አድርገዋል። በአንፃሩ ደግሞ በአንድ የምርጫ ጣቢያ የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ አቅመ ደካሞች፣ ነፍሰ ጡር እናቶች እና ሕፃናትን/ልጆች ለያዙ ወላጆች ቅድሚያ እንልሰጡ የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት ያረጋግጣል።

4. አካል ጉዳተኛ የሆኑ ግለሰቦችን (Persons with disabilities) በተመለከተም በ 10 የምርጫ ጣቢያዎች አካል ጉዳተኞች ራሳቸው በመረጡት የግል ረዳቶቻቸው እገዛ መሰረት እንዲመርጡ የተደረገ ሲሆን ፣ በ10 ምርጫ የምርጫ ጣቢያዎች ግን አካል ጉዳተኞች በሚመርጡበት ወቅት ምንም አይነት እገዛ እንዳልተደረገላቸው ሪፖርቶች ያሳያሉ።

5. በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ መሰረት መራጮች ለመመዝገብ እና/ወይም ድምጽ ለመስጠት በሚሄዱበት ወቅት የመኖሪያ እና የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያ እንዲያሳዩ ይገደዳሉ። ማንነታቸውን እና የመኖሪያ ቦታቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ ማቅረብ የማይችሉ ግለሰቦች በመራጭነት መመዝገብ የማይችሉ እና በድምጽ መስጫው ሂደትም ድምፅ መስጠት እንደማይችሉ ህጉ ይደነግጋል፡፡ ይህ እንዳለ ሁኖ የማንነት እና የመኖሪያ ቦታቸውን ማረጋገጫ መረጃ ማቅረብ የማይችሉ ግለሰቦች እና እንደዚህ ባሉ አጋጣሚዎች ሲከሰቱ መራጮች ምስክር በማቅረብ ድምጽ መስጠት እንደሚችሉ ህጉ ይሪፖርቶች በ14 የምርጫ ጣቢያዎች የማንነት ማረጋገጫ እና/ወይም የመኖሪያ ነዋሪነት ማረጋገጫ መረጃ ያላመጡ መራጮች ምስክር በማቅረብ ድምጽ እንዲሰጡ የተፈቀደላቸው መሆኑን ያሳያሉ። በሌላ በኩል በ6 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ሁሉም መራጮች ማንነታቸውን እና የመኖሪያ ቦታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይዘው በመቅረብ ድምፅ የሰጡ መሆኑን የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት አድረገዋል።

6. ከዚህ በላይ ከተመለከቱት የትዝብት ግኝቶች በተቃራኒ በሁለት  የምርጫ ጣቢያዎች ማለትም በአሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03  ሀ 2 እና በአሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ሀ 2ሀ የምርጫ ጣቢያ ላይ መራጮች የማንነት ማረጋገጫ እና የመኖሪያ ቦታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ቢያቀርቡም  እንዳይመርጡ ተደርገዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘም በእነዚህ የምርጫ ጣቢያዎች አንዳንድ መራጮች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ አልተገኘም ወይም አልሰፈረም በሚል ምክንያት ድምጽ እንዳይሰጡ ተደርገዋል። ይህ ድርጊት የዜጎችን የፖለቲካ መብቶች የሚጋፋ በመሆኑ አሳሳቢ ነው። በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያ መሰረት የድምጽ መስጫ ጊዜ ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ ያበቃል። የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ሁሉም መራጮች ድምጻቸውን እንዲሰጡ ለማስቻል እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ድረስ ለመራጮች ክፍት መሆን እንዳለባቸው  ይኸው መመሪያ የሚደነግግ ሲሆን፣ በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ደግሞ ቦርዱ የድምፅ መስጫ ሰዓቱን ሊያራዝም እንደሚችል ህጉ ያስቀምጣል። ይህንን አስመልክቶም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምረጫ ቦርድ በአሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03 ሀ 2 እና  በአሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ሀ 2ሀ ላይ የደምፅ መሰጫ ሰዓቱን እስከ ምሽቱ 2፡00 ያራዘመ ቢሆንም ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ላይ የደረሱ ስድስት መራጮች እንዳይመርጡ  መከልከላቸውን የህብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት አድረገዋል። ይህም ሁኔታ የዜጎችን የመምረጥ መብት የሚጋፋ ከመሆኑ አንፃር አሳሳቢ ነው።

7. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ  አንድ መራጭ ከመምረጡ በፊት(እንደመረጠ)  በጣቱ ላይ የማይጠፋ ቀለም መቀባት እንዳለበት ያስገድዳል። ይህንን አስመልክቶም የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች እንዳረጋገጡት በ19 የምርጫ ጣቢያዎች  መራጮች ከመምረጣቸው በፊት ጣታቸው ላይ የማይለቅ ቀለም ምልክት የተደረገባቸው ሲሆን በአንድ ምርጫ ጣቢያ  ማለትም በአሶሳ 02 ምርጫ ጣቢያ 02 02 ሀ 1ሀ ላይ መራጮች ልክ እንደመረጡ የማይጠፋ/ የማይለቅ ቀለም ምልክት አልተደረገባቸውም።

8. በኢትዮጵያ የምርጫ አዋጅ መሰረት በድምጽ መስጫ ቀን በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው የተገኙ መራጮች  መምረጥ የሚችሉት ለመራጭነት በተመዘገቡበት ጣቢያ ብቻ  እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ በምርጫ አዋጁ መሰረት የመራጮች ስም በመራጭ መዝገብ ውስጥ መገኘቱን የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ የምርጫ ህግ ድንጋጌ በተቀራኒ በአሶሳ 03 የምርጫ ጣቢያ 03 03 ሀ 2 አንድ ሰው እና ቡልደግሉ 01 የምርጫ ጣቢያ ቡልዷጋሉ ከተማ 01 ተብለው በተሰየሙት ሁለት የምርጫ ጣቢያዎች ስድስት ግለሰቦች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ሳይኖር/ሣይገኝ አካል ጉዳተኞች ወይም አዛውንቶች ናቸው በሚል ምክንያት ብቻ እንዲመርጡ እ የተደረገ መሆኑን የኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች ያመላክታሉ ።

9. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች  የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ለመራጮች ከመሰጠታቸው በፊት ማህተም ሊደረግባቸው  ይገባል። ይህንን አስመልክቶም በሁሉም ማለትም በ20ዎቹ ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎች በሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች  ላይ  ማህተም እያደረጉ ለመራጮች ሲሰጡ እንደነበር የኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች ያመላክታሉ።

10. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት ማንኛውም የድምፅ  መስጠት ሂደቱ ምስጢራዊነቱን የጠበቀ መሆን አለበት። በዚህ ጉዳይም የኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያመላክተው ከሆነ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ሲደረግ የነበረው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ሚስጥራዊነታቸውን የጠበቁ እንደነበር ያመላክታሉ።

11. በሁሉም 20 የምርጫ ጣቢያዎች ግልፅ የሆነ የአካል ጉዳት የሌላቸው እና አረጋውያን ያልሆኑ መራጮች  በሚመርጡበት ወቅት እገዛ ወይም እርዳታ አልተደረገላቸውም፡፡

12. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ  መሰረት በድምፅ መስጫ እለት ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መገኘት የለባቸውም። ይህንን በተመለከተም የኅብረት ለምርጫ  ታዛቢዎች በሁሉም ጣቢያዎች ማለትም በ20ዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች በድምፅ  በሚሰጥበት ወቅት ያልተፈቀደላቸው ሰዎች  በጣቢያዎች ውስጥ እንዳልተገኙ ያመላክታሉ።

13. የምርጫ ህጉ መራጮች፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እንዲሁም ሴቶች ማንኛውም  አይነት ተፅዕኖ እና/ወይም ግፊት እና ጥቃት ሰለባ መሆን እንደሌለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይህንን አስመልክቶም ሕብረቱ በታዘባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ላይ  በምርጫ አሴት መራጮች፣ የፓርቲ ውኪሎች፤ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈጻሚወች የደረሰ ማስፈራራት ወይም  ጥቃት አልነበረም።

14. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ  መሰረት በድምፅ መስጫ እለት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ያለምንም መቆራረጥ ቀኑን ሙሉ  መካሄድ አለበት። ይህንን በተመለከተም የሕብረቱ  ታዛቢዎች በሁሉም (በ20ዎቹ) የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ያለምንም መቆራረጥ መካሄዱን ሪፖርት አድርገዋል።

15. የምርጫ አዋጁ በይፋ የምርጫ ጣቢያዎች ህጋዊ የመዝጊያ ሰዓት ከቀኑ 12፡00 ሰዓት እንደሆነ ይደነግጋል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሰኔ 23 ቀን 2023 በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ  መሰረት የምርጫ ጣቢያዎችን የመዝጊያ ጊዜ ለተጨማሪ ሁለት ሰዓታት ማለትም እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት ድረስ መራዘሙን አስታውቋል። በዚህም መሰረት የህብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያመላክተው 17 የምርጫ ጣቢያዎች ከቀኑ 12፡00 ሰአት የተዘጉ ሲሆን 3 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ከምሽቱ 2፡00 ሰአት ተዘግተዋል።

16. ምንም እንኳን የምርጫ አዋጁ የምርጫ ጣቢያዎች ህጋዊ የመዝጊያ ሰዓት ከቀኑ 12፡00 ሰዓት እንደሆነ በይፋ ቢደነግግም ከቀኑ 12፡00 ሰዓት በፊት ሰልፍ ይዘው የሚጠባበቁ መራጮች ካሉ የምርጫ ጣቢያው ሃላፊው ሰልፍ የያዙ ሁሉም መራጮች ድምፅ መስጠታቸውን ካረጋገጠ በኋላ የምርጫ ጣቢያውን በር መዝጋት እንዳለበት ህጉ ያስቀምጣል። ከዚህ አኳያም የኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች በምርጫ ጣቢያው መዝጊያ በር ላይ የነበሩ ሁሉም መራጮች በህጉ መሰረት እንዲመርጡ የተደረገ ሲሆን፤ በ2 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ከ12፡ ሰዓት በኋላ ድምጽ እንዲሰጡ መፈቀዱን አመልክተዋል።

## የድምጽ ቆጠራ ሂደት

በድምጽ መስጫ ቀን ካሉት ሂደቶች መካከል የድምጽ ቆጠራ አንዱና የመጨረሻው ነው። በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ጣቢያው እንዲዘጋ ያደርጋል። ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዘጋት በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ታዛቢዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች በተገኙበት ሁሉም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የምርጫ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት የድምፅ ቆጠራው ይከናወናል። እንዲሁም በሕግ የተቀመጡ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ደግሞ የድምጽ ቆጠራው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ አለመከናወኑን የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። ይህንን አስመልክቶም የሕብረቱ ታዛቢዎች በድምጽ ቆጠራ ሂደቱ ላይ የሰበሰቡትን የሪፖርት ግኝቶች እንደሚከተለው አቅርበዋል።

1. በምርጫ ህጉ መሰረት የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ታዛቢዎች በተገኙበት መካሄድ አለበት። በዚህ መሰረትም የኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያመላክተው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች በቆጠራው ወቅት የህብረቱ ታዛቢዎች ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጡ አልተጠየቁም ወይም አልተገደዱም።

2. የምርጫ ህጉ የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ በድምፅ መስጫው ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እንደሚካሄድ ይደነግጋል። እናም እንደህብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ በድምጽ መስጫ ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ተካሂዷል።

3. የቆጠራው ሂደቱ በ4 ምርጫ ጣቢያዎች ተቋርጦ ነበር፡፡ ተቋርጦ የነበረውም በአሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03 03-ሀ-2፣ አሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ሀ 2-ሀ፣ አሶሳ 02 ምርጫ ጣቢያ 02 02 ሀ 1-ለ እና አሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ለ-2 ፊንቲግራራ ምርጫ ጣቢያ ጓሊ ሲሆን የተቋረጠበት ዋና ምክንያትም ምርጫ ቦርድ ምርጫው እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት እንዲራዘም ያሥተላለፈው ውሳኔ ዘግይቶ በመድረሱ ምክንያት ነበር።

4. የምርጫ ህጉ የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ያለምንም ጣልቃገብነት፣ ወከባ እና/ወይም ማስፈራሪያ እንዲካሄድ ይደነግጋል፡፡ ይህንን በተመለከተም የሕብረቱ ሪፖርት እንደሚያሳየው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት ጣልቃገብነት፣ ትንኮሳ እና/ወይም ማስፈራራት አልነበረም።

5. እንደምርጫ አዋጁ ድንጋጌ በድምፅ ቆጠራው ሂደት ውስጥ ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ለታዛቢዎችና ለፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርግቶ ማሳየት ይኖርበታል፡፡ እናም የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያመላክቱት በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ ሃላፊወች በድምጽ ቆጠራው ወቅት የምርጫ ወረቀቶቹን በግልፅ አሳይተዋል።

6. የምርጫ ቦርዱ መመሪያ የምርጫ ጣቢያ ጣቢያ ሃላፊዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸወን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ያሥችል ዘንድ ተመሳሳይ መስፈርቶችን መከተል እና መተግበር እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል። ይህንን ተከትሎም በአንድ የምርጫ ጣቢያ የጣቢያው ሃላፊ ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸወን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ተመሳሳይ መስፈርቶችን አለመተግበራቸውን የትዝብት ሪፖርቱ ያሳያል። ይህ ክስተት አሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03 03 ሀ 2 በምርጫ ጣቢያ ሲሆን የጣቢያው ሃላፊ ውድቅ መሆን የነበረባቸውን የምርጫ ካርዶች ዋጋ ያላቸው አድርገው ሲያረጋግጡ ተስተውለዋል።

7. ምንም አንኳ ታዛቢዎች ዜጎች ቅሬታቸውን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሲገልጹ ሰምተናል ቢሉም በምርጫ ጣቢያ ለተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የቀረቡ መደበኛ ቅሬታዎች አልነበሩም ።

## አፋር ክልል

ይህ ሪፖርት የተመጣጠነ የስምሪት ዘዴን/proportional deployment methodology/ በመጠቀም በምርጫው/ድምፅ መስጫው እለት በ37 የምርጫ ጣቢያዎች በተሰማሩ 37 የህብረቱ ቋሚ ታዛቢዎች(Stationary Observers) አማካኝነት ተሰብስቦ ሪፖርት በተደረገ መረጃ ላይ የተመሰረት ነው። የሪፖርቱ ዋና ትኩረትም የምርጫ አስፈጻሚዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስን፣ የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀትን፣ የድምጽ መሰጫ ጣቢያዎች አከፋፈትን፣ የድምጽ አሰጣጥ ሂድትን፣ የድምጽ መሰጫ ጣቢያ አዘጋግን/ አዘጋጋ ስርዓትን፣ የድምፅ ቆጠራ እና የውጤት ማዳመርን የሚምለከቱ መረጃዎች ላይ ነው፡፡ ምልከታው የተካሄደው በአንድ ከተማ፣ በ17 ከፊል ከተማዎች እና በ8 የገጠር አካባቢዎች በተደራጁ የምርጫ ጣቢያዎች ሲሆን፤ የሪፖርቱ ዝርዝር ይዘት እንሚከተለው ቀርቧል፡፡

## ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መድረስን በተመለከተ

1. በድምጽ መስጫ ዕለት ከሚጠበቁ ወሳኝ ኹነቶች መካከል የምርጫ አስፈፃሚዎች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መድረስ አንዱ ነው፡፡ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ከጠዋቱ 12 ሰዓት ለመጀመር እንዲያስችል፤ የምርጫ ቦርድ አመራሮች እና ሰራተኞች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምፅ ለመስጠት መዘጋጀታቸውን ለማረጋገጥ የምርጫ ሰዓቱ ከመድረሱ በፊት ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ቀድመው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እንዲገኙ ይጠበቃል። ይህንን አስመልክቶም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች እንዳረጋገጡት በ34(92%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚውች 12፡00 ከመሆኑ በፊት ማለትም ከማለዳው 11፡30 በምርጫ ጣቢያዎች ተገኝተዋል።

2. በሁሉም የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ማለትም 37(100%) የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ወደ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ገብተው የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል።

3. የምርጫ ህጉ ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች 12፡00 ሰዓት ከመሆኑ በፊት መከፈት እንዲሁም ልክ ከጥዋቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ ድምፅ መስጠት ማስጀመር እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ሕብረት ለምርጫ ከታዛቢዎች ያገኘው ሪፖርት እንደሚያመለክተው በ37ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱን በህጉ መሰረት አስጀምረዋል።

4. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት እንደ ወታደራዊ ካምፖች፣ የግል መኖሪያ ቤቶች፣ የፖሊስ ጣቢያዎች፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ የጤና ተቋማት፣ የመዝናኛ ማዕከላት እና የፖለቲካ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ባሉ ቦታዎች የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋምን ይከለክላል። ይህንን በተመለከተም የኅብረቱ ታዛቢዎች በሁሉም ማለትም በ37ቱ (100%) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ሕጉ ባልተከለከሉ ቦታዎች መቋቋማቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

5. በምርጫ ቀን የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ የምርጫ ህጉ ከምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትሮች ርቀት ላይ ወይም ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ምንም አይነት የምረጡኝ ቅስቀሳ ዘመቻ እንቅስቃሴዎችን ማድረግን የምርጫ ህጉ በግልጽ ይከለክላል። ከዚህ ጋር በተያያም ታዛቢውች በ37ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት የምርጫ ዘመቻ/ቅስቀሳ አለመደረጉን ሪፖርት አድርገዋል።

## የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀትን በተመለከተ

1. የምርጫ ጣቢያዎች የሚቋቋሙበት ቦታ ለዜጎች ያላቸው ተደራሽነት በምርጫ ሂደቱ ላይ ዜጎች በሚኖራቸው ተሳትፎ ላይ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ በዚህ ረገድ 23 ( 62%) የምርጫ ጣቢያወች በድንኳን ውስጥ የተቋቋሙ ሲሆን፤ 4 (11%) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ መደራጀታቸውን አስር (27%) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ በዛፍ ጥላ ስር፣ በሳር እና በሸራ በተሠሩ መጠለያዎች ውስጥ መቋቋማቸወን በኅብረቱ ታዛቢውች ሪፖርት ተደርጓል።

2. ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሃይ ለመከላከል የሚያስችል መጠለያ መኖሩ በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ውስጥ ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ይወሰዳል። በዚህ ረገድ የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች በ12 (32%) የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች የነበሯቸው ሲሆን፤ በ25 (68%) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሐይ የሚከላከሉ መጠለያዎች አልነበሯቸውም።

3. መራጮች በቀላሉ ድምጻቸውን ለመስጠት እንዲችሉ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ በሆኑ አካባቢዎች ሊቋቋሙ ይገባል። የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ለአካል ጉዳተኞች (persons with disabilities-(PWDs))፣ ለነፍሰ ጡር እናቶች፣ ሕፃናት ለያዙ ሴቶች እና አረጋውያን ወይም ለአቅመ-ደካማ እና የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች ተደራሽነትን ግምት ውስጥ ያሰገባ መሆን አለበት። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ግኝቶች እንደሚያሳዩት 24 (65%) የምርጫ ጣቢያዎች ይህን ጉዳይ ግምት ውስጥ ያስገቡና ተደራሽ ሲሆኑ፤ 35% (13) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ይህን ጉዳይ ግምት ውስጥ ያላሰገቡና ተደራሽ አልነበሩም።

4. የድምጽ መስጫ ቁሳቁስ አቅርቦት መሟላት ለድምጽ አሰጣጥ ሂደት እጅግ ወሳኝ ነው። ከድምጽ መስጫ ዕለት አስቀድሞ ሁሉም መራጮች ድምጽ መስጠት እንዲችሉ የምርጫ ቁሳቁሶች በእያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ጣቢያ መሟላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በምርጫ ህጉ አንፃርም የምርጫ ጣቢያዎችን በተሟላ መንገድ ለማዘጋጀት የምርጫ ቁሳቁሶች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኘት አስፈላጊ ነገር ነው። ከእነዚህ ወሳኝ ቁሳቁሶች መካከልም:- የድምፅ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ የምርጫ ቦርድ አፊሴላዊ ማህተም፣ የማዳመሪያ ቅፅ፣ የውጤት መሳወቂያ እና የማመሳከሪያ ቅፆች፣ የማይፋቅ/የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምፅ መስጫ ሳጥን (Ballot Box)፣ መከፈቱ የሚያስታውቅ ቁለፍ እና የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች ይገኙበታል። እነዚህን ወሳኝ ቁሳቁሶች ተሟልተዋል ወይም አልተሟሉም በሚለው ዙሪያ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ኅብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በ37ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኘታቸውን ሪፖርተ አድርገዋል።

5. የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የድምፅ መስጫ ሳጥኖች (Ballot Boxes) ባዶ መሆናቸውን ለታዛቢዎችና ለፓርቲ ተወካዮች እንዲያሳዩ ያስገድዳል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ግኝት በ37ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊወች የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን አሳይተዋል።

6. የምርጫ ህጉ  የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለማስጀመር ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈፃሚዎች መገኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል። የሕብረት ለምርጫ  ታዛቢዎች በታዘቡባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ከመመጀመሩ በፊት በአማካይ 5 የምርጫ አስፈፃሚዎች እንደነበሩ ለመታዘብ ተችሏል። ኅብረቱ  ያሰማራቸው ታዛቢዎች ግኝት እንደሚያሳየው በምርጫ ጣቢያዎች በአማካይ 5 የምርጫ አስፈጻሚዎች የነበሩ ሲሆን፤ በ6  (16  %)  የምርጫ ጣቢያዎች ሴቶች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች  እንደነበሩ በ31 (  84% )  የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ወንድ  የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች እንደነብሩ ታዛቢዎች ሪፖርት  አድርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ በሁሉም የምርጫ  ጣቢያዎች  ከምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች  መካከል  አካል  ጉዳተኞች አለመኖራቸው በታዛቢወች ሪፖርት ተደርጓል።

7. የምርጫ ህጉ ድንጋጌ   የምርጫ ጣቢያዎች ቢያንስ ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን እንደሚያቋቁሙ ይገልፃል። በዚህም መሰረት የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያሳየው በ14 (38%) የምርጫ ጣቢያዎች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተቋቁመው የነበረ ሲሆን፤ በ23 (62%) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ምንም አይነት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አለመቋቋማቸውን ሪፖርቱ ያመልክታል።

8. የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት እንዳለባቸው የምርጫ ህጉ ይደነግጋል። በዚህ ረገድ የሕብረቱ የምርጫ ታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያሳየው በ29(78%) የምርጫ ጣቢያወች የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች የተገኙ ሲሆን ፣ በ8 (22%)  የምርጫ ጣቢያዎች ግን የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች አለምገኘታችወን ታዛቢዎች ገልጸዋል።

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን በተመለከተ

የድምጽ-መስጫ ጣቢያዎች ከተከፈቱ እና ከተደራጁ በኋላ ቀጣዩ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ነው። በዚህም መሰረት ኅብረት ለምርጫ  አፋር ክልል የነበረውን የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ  ከታዛቢዎቹ የሰበሰባቸውን ግኝቶች እንደሚከተለው አቅርቧዋል።

1. በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ማለትም በ37ቱም (100 %) የድምጽ መስጫ ጣቢያወች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለመታዘብ የተሰማሩ የኅብረቱ ታዛቢዎች ጣቢያውን ለቀው እንዲወጡ አለመጠየቃቸውን ወይም አለመገደዳቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

2. የምርጫ ህጉ  አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ አቅመ ደካሞች ወይም የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው ሰዎች፣ ነፍሰ ጡር እናቶች እና ሕፃናትን/ልጆችን ለያዙ ወላጆች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው መምረጥ እንዳለባቸው ያዛል። ይህንን በተመለከተም የኅብረቱ ታዛቢዎች እንዳረጋገጡት በ36 (97%) የምርጫ ጣቢያዎች  የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን፣ አቅመ ደካሞች፣ ነፍሰ ጡር እናቶች እና ሕፃናትን/ልጆች ለያዙ ወላጆች ቅድሚያ በመስጠት እንዲመርጡ አድርገዋል። በአንፃሩ ደግሞ  በ1 (3%) የምርጫ ጣቢያ ለእነዚህ ትኩረት ለሚሹ ወይም ቅድሚያ መሰጠት ለነበረባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ቅድሚያ እንዳልተሰጣቸው ታዛቢወች ሪፖርት አእድርገዋል።

3. የምርጫ ህጉ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ግለሰቦች (Persons with disabilities) ራሳቸው በመረጡት የግል ረዳቶቻቸው እገዛ እንዲመርጡ መደረግ እንዳለበት ህጉ ያዝዛል። በዚህ ረገድም የኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንዳደረጉት ከሆነ በ32 (86%) የምርጫ ጣቢያዎች አካል ጉዳተኞች በራሳቸው ኢጋዥ አማካኝነት መመረጣቸውን ፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ ፊንቲግራራ ምርጫ ጣቢያ ጉለሊ ተብሎ በሚጠራ የድምጽ መስጫ ጣቢያ  አንድ ግለሰብ  ለአካል ጉዳተኞችና  ረዳት ለሚሹ  ግለሰቦች በተደጋጋሚ እገዛ/ እርዳታ ሲያደርግልቸው ተስተውሏል። በአንፃሩ ደግሞ በ5 (14%) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች እርዳታ/እገዛ ለሚሹ  ግለሰቦች እገዛ/ እርዳታ አለመደረጉን የታዛቦዎች ሪፖርት ያመላክታል።

4. የምርጫ ህጉ  መራጮች ለመመዝገብ እና/ወይም ድምጽ ለመስጠት ወደ ጣቢያዎች በሚሄዱበት ጊዜ የነዋሪነት  እና ማንነታቸውን የሚገልፅ  ማረጋገጫ እንዲያሳዩ ያስገድዳል። ማንነታቸውን እና  የመኖሪያ ቦታቸውን ማረጋገጥ ያልቻሉ መራጮች በድምጽ አሰጣጡ ሂደት  እንዲሳተፉ ህጉ አይፈቀድም። ነገር ግን የምርጫ ህጉ እንደዚህ አይነት  አጋጣሚዎች ሲክስቱ መራጮች ማንነታችወን በምስክሮች እንዲያረጋግጡ ህጉ  ይፈቅዳል። ከዚህ የህግ ድንጋጌ በተቃራኒ በአንድ  የምርጫ ጣቢያ  ማለትም ገዋኔ  01 የምርጫ ጣቢያ ጋልኤብ ሀ ላይ የማንነት ማረጋገጫ እና/ወይም የነዋሪነት ማርጋገጫ ማቅረብ ያልቻሉ መራጮች ሳያስመሰከሩ እንዲመርጡ የተደረገ መሆኑን የሕብረቱ ታዛቢዎች አረጋግጠዋል።  በአንፃሩ ደግሞ በ36ቱ (97 %) የምርጫ ጣቢያዎች የማንነት እና የነዋሪነት ማርጋገጫ ያቀረቡ  መራጮች በሙሉ ድምጽ  ያለምንም ክልከላ ድምፅ እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል።

5. በምርጫ ህጉ መሰረት የተመዘገቡ እና የማንነት እና የነዋሪነት ማረጋገጫ ያቀርቡ  መራጮች ድምጽ የመስጠት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተም የሕብረቱ ታዛቦዎች ሪፖርት እንደሚያሳየው  በሁሉም ማለትም  በ37ቱ (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ  መራጮች እንዲመርጡ ተደርጓል።

6. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት አንድ መራጭ ከመምረጡ በፊት የማይጠፋ/ የማይለቅ ቀለም ጣቱ ላይ በመቀባት ምልክት መደረግ እንዳለበት ያስገድዳል፡፡ ይህንን አስመልክቶም የሕብረት ለምረጫ ታዛቢዎች እንዳረጋገጡት ከሆነ በ34 (92%) የምርጫ ጣቢያዎች ድምፃቸውን በሰጡ በሁሉም መራጮች ጣት ላይ  የማይለቅ ቀለም የተደረገባቸው ሲሆን፤ በእንጻሩ  በሶስት  የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ በጣታቸው ላይ የማይለቅ ቀለም ሳይደረግ  ድምጽ እንዲሰጡ ተደርጓል።  ይህ ክስተት የተከሰተውም አዋሬ ና ለምለምነን ምርጫ ጣቢያ ደንገባዲስ, ሃዶና ቢዳሪ ምርጫ ጣቢያ ሃዶ   እና ከልዋን  01 ምርጫ ጣቢያ ከልዋን ከተማ   የምርጫ ጣቢያዎች ላይ አንደየቅደም ተከተላቸው 11 ፣ 8 እና 6 ግለሰቦች በጣቶቻቸው ላይ የማይለቅ ቀለም ምልክት ሳይደረግባቸው ድምጽ ሰጥተዋል።

7. በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያ መሰረት በድምጽ መስጫ ቀን በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው የተገኙ መራጮች መምረጥ የሚችሉት ለመራጭነት በተመዘገቡበት ጣቢያ ብቻ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም የመራጮች ስም በመራጮች መዝገብ ውስጥ መገኘቱን የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህ የህግ ድንጋጌ በተቃራኒ በአንድ የምርጫ ጣቢያ በተለይም "ገዋኔ 01 ምርጫ ጣቢያ ገልኤብ-ሀ_1" ላይ አምስት ግለሰቦች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ሳይገኝ እንዲመርጡ የተደረገ መሆኑን የሕብረቱ ታዛቦዎች ሪፖርት ያመላክታል።

8. በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ህግ መሰረት የምርጫ ጣቢያ ሀላፊ ሁሉንም የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ለመራጮች ከመስጠታቸው በፊት ማህተም ማድረግ እንዳለበት ያስገድዳል። ይህንን አስመልከቶም የሕብረቱ ታዛቢዎች በሁሉም ማለትም በ37ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎች በሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ማህተም እያደረጉ ለመራጮች ሲሰጡ እንደነበር ሪፖርቶቹ ያመላክታሉ።

9. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት ማንኛውም የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ምስጢራዊነቱን የጠበቀ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። በዚህ ጉዳይም የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያመላክተው በሁሉም ማለትም በ37ቱ (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ሲደረግ የነበረው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ሚስጥራዊነታቸውን የጠበቁ ነበሩ።

10. በሁሉም ማለትም በ37ቱ (100) የምርጫ ጣቢያዎች የሚታይ የአካል ጉዳት የሌላባቸው እና አረጋውያን ያልሆኑ መራጮች ድጋፍ አልተደረገላቸውም።

11. በምርጫ ህጉ መሰረት በድምፅ መስጫ እለት ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መገኘት የለባቸውም። የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያመላክተው በ36ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ወስጥ ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች በጣቢያዎች ውስጥ አልተገኙም፡፡ ከዚህ የህግ ድንጋጌ በተቃራኒ ደግሞ "ገዋንኔ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ጋልኤብ-ለ" በተባለ አንድ የምርጫ ጣቢያ ውስጥ በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ወቅት ያልተፈቀለደለት ሰው ማለም የቀበሌ አመራር የሆነ ግለሰብ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተገኝቶ ነበር።

12. በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያ መሰረት መራጮች፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እንዲሁም ሴቶች ማንኛውም አይነት ተፅዕኖ እና/ወይም ግፊት እና ጥቃት ሰለባ መሆን እንደሌለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይህንን አስመልከቶም ሕብረቱ በታዘባቸው በሁሉም 37(100%) የምርጫ ጣቢያዎች ላይ በምርጫ አስፈፃሚዎች ላይ ማስፈራራት እና እንግልት ያልደረሰ ሲሆን፤ በተለይም ድሞ ሴት መራጮች፣ የፓርቲ ውኪሎች፤ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈጻሚወች የጥቃት ሰለባዎች አልነበሩም። ኅብረቱ በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የማስፈራራት እና እንግልት በአጠቃላይ በተለይም ደግሞ ሴት መራጮች፣ የፓርቲ ውኪሎችን፤፣ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈጻሚወች የጥቃት ሰለባዎች አልነበሩም።

13. የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ በድምፅ መስጫ እለት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ያለምንም መቆራረጥ ቀኑን ሙሉ መካሄድ እንዳለበት ያስገድዳል፡ ፡ ይህንን በተመለከተም የኅብረቱ ታዛቢዎች በሁሉም ማለትም በ37ቱ (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ቀኑን ሙሉ አለመቋረጡን ሪፖርት አድርገዋል።

14. በምርጫ ህጉ ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው የምርጫ ጣቢያዎች ህጋዊ የመዝጊያ ጊዜ ከቀኑ 12፡00 ሰዓት ነው። ከዚህ አኳያም በምርጫ ህጉ መሰረት ሁሉም ማለትም 37ቱ (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ከቀኑ 12፡00 ሰአት ላይ የተዘጉ መሆኑን የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት ያሳያል።

15. ምንም እንኳን የምርጫ ህጉ በይፋ የሚደነግገው የምርጫ ጣቢያዎች ህጋዊ የመዝጊያ ሰዓት ከቀኑ 12፡00 ሰዓት ቢሆንም ከቀኑ 12፡00 ሰዓት በፊት ሰልፍ ይዘው የሚጠባበቁ መራጮች ካሉ የምርጫ ጣቢያው ሃላፊው ሰልፍ የያዙት ሁሉም መራጮች ድምፅ መስጠታቸውን ካረጋገጠ በኋላ የምርጫ ጣቢያውን በር መዝጋት እንዳለበት ህጉ ያሥቀምጣል። በዚህ ጉዳይ የታዛቦዎች ሪፖረት እንደሚያሳየው በ18 (35%) የምርጫ ጣቢያወች ሰልፍ ይዘው የነበሩ መራጮች እንዲመርጡ የተደረገ ሲሆን፤ በ24 (65%) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ በምርጫ ጣቢያ የመዝጊያ ሰዓት ላይ ሰልፍ ይዘው የሚጠብቁ መራጮች አልነበሩም።

## የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን በተመለከተ

የድምጽ-መስጫ ጣቢያዎች ከተከፈቱ እና ከተደራጁ በኋላ ቀጣዩ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ነው። በድምጽ መስጫ ቀን ካሉት ሂደቶች መካከል የድምጽ ቆጠራ አንዱና የመጨረሻው ሂደት ነው። በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ከጠናቀቀ በኋላ የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ጣቢያውን ይዘጋል። ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዘጋት በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ታዛቢዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች በተገኙበት ሁሉም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የምርጫ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት የድምፅ ቆጠራው ይከናወናል። በሕግ የተቀመጡ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ደግሞ የድምጽ ቆጠራው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ አለመከናወኑን የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። ይህንን አስመልከቶም ሕብረት ለምርጫ በድምጽ ቆጠራ ሂደቱ ላይ የሰባቸውን ግኝቶች እንደሚከተለው አቅርቧዋል።

1. የምርጫ ህጉ የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ታዛቢዎች በተገኙበት እንዲካሄድ ያስገድዳል። በዚህ መሰረትም የኅብረቱ ታዛቢዎች በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ማለትም በ37ቱም (100 %) የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለመታዘብ የሄዱ የኅብረቱ ታዛቢዎች በድምጽ ቆጠራው ወቅት ጣቢያዎቹን ለቀው እንዲወጡ አለመጠየቃቸውን ወይም አለመገደዳቸውን ታዛቢወች ሪፖርት አድርገዋል።

2. የምርጫ ህጉ የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ በድምፅ መስጫው ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ መካሄድ እንዳለበት ይደነግጋል። የኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ በ37ቱም (100%)) የምርጫ ጣቢያዎች ቆጠራው በድምጽ መስጫ ቀን በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ውሥጥ ተካሂዋል።

3. በ37ቱም (100% ) የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ አልተቋረጠም ነበር።

4. የምርጫ ህጉ የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ያለምንም ጣልቃገብነት፣ ወከባ እና/ወይም ማስፈራሪያ መካሄድ እንዳለበት ይደነግጋል። የኅብረቱ ሪፖረት እንደሚያሳየው በሁሉም ማለትም በ37ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት ጣልቃገብነት፣ ትንኮሳ እና/ወይም ማስፈራራት አልነበረም።

5. እንደምርጫ ህጉ ድንጋጌ በድምፅ ቆጠራው ሂደት ውስጥ ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ለታዛቢዎችና ለፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች ዘርግቶ ማሳየት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ኅብረቱ ያሰማራቸው የታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያመላክቱት በሁሉም ማለትም በ37ቱ (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ ሃላፊወች በድምጽ ቆጠራው ወቅት የምርጫ ወረቀቶቹን በግልፅ አሳይተዋል።

6. የምርጫ ህጉ የምርጫ ጣቢያ ጣቢያ ሃላፊዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላችወን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ያሥችል ዘንድ ተመሳሳይ መስፈርቶችን መከተል እና መተግበር እንደሚያስፈልግ ይገልፃል፡፡ ከዚህ አኳያም የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በ37ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላችወን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ተመሳሳይወይም /ወጥ መመዘኛዎችን ሲጠቀሙ እንደነበር ሪፖርቶች አሳይተዋል፡

7. ምንም እንኳን ለተቋቋመው መደበኛ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበ ምንም አይነት ቅሬታ እንዳልነበረ ታዛቢዎች ቢናገሩም መራጮች ቅሬታቸውን ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሲገልጹ ሰምተናል ብለዋል።

## ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል (መስቃን እና ማረቆ የምርጫ ክልል)

ይህ የትዝብት ሪፖርት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መስቃን እና ማረቆ በተባሉ ሁለት ወረዳዎችና የምርጫ ክልሎች በ12 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ተሰማርተው ቀኑን ሙሉ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ሲታዘቡ በነበሩ 12 ቋሚ/ ተቀማጭ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች አማካኝነት በተሰበሰበው መረጃን መሰረት አድርጎ የተዘጋጅ ነው። ኅብረቱ ታዛቢዎችን ለማስማራት ተመጣጣኝ ስምሪት ዘዴን (proportional deployment method) ተጠቅሟል። የሪፖርቱ ዋና ትኩረትም የምርጫ አስፈጻሚዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስን፤ የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀትን፤ የድምጽ መሰጫ ጣቢያዎች አከፋፈትን ፤ የድምጽ አሰጣጥ ሂድትን ፤ የድምጽ መስጫ ጣቢያ አዘጋግን/ አዘጋግ ስርዓትን፣ የድምፅ ቆጠራ እና የውጤት ማዳመርን የሚመለከቱ መረጃዎች ላይ ነው። መረጃው የተሰበሰበው በ7 በከተማ ውስጥ ከሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች፣ 2 በከፊል ከተማ ከሚገኙ ጣቢያዎች እና 3 በገጠር አካባቢዎች ተደራጅተው ከነበሩ ጣቢያዎች ሲሆን፤ የሪፖርቱ ዝርዝር ይዘት እንሚከተለው ቀርቧል።

## ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መድረስን በተመለከተ

1. በድምጽ መስጫ ዕለት ከሚጠበቁ ወሳኝ ኹነቶች መካከል የምርጫ አስፈፃሚዎች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መድረስ አንዱ ነው። የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ከጠዋቱ 12 ሰዓት ለመጀመር እንዲያስችል፤ የምርጫ ቦርድ አመራሮች እና ሰራተኞች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምፅ ለማስጠት ዝግጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የምርጫ ሰዓቱ ከመድረሱ በፊት ቀድመው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እንዲገኙ ይጠበቃል። ይህንን አስመልክቶም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች እንዳረጋገጡት 12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚውች አስራ ሁለት ከመሆኑ በፊት ማለትም ከማለዳው 11፡30 በምርጫ ጣቢያዎች ተገኝተዋል።

2. በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የተሰማሩት የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለመታዘብ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተገኝተው እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል።

3. በምርጫ ህጉ መሰረት ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች 12፡00 ሰዓት ከመሆኑ በፊት መከፈት እንዳለባቸውና ልክ ከጥዋቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ ድምፅ መስጠት ማስጀመር እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ከታዛቢዎች የተገኘው የሪፖርት ግኝት እንደሚያመለክተው በ11 (92%) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ህጉ መሰረት ከጠዋቱ 12፡00 ሰአት ጀምሮ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ መጀመሩን አመልክተዋል። በሌላ በኩል በአንድ የምርጫ ጣቢያ ማለትም ምርጫ ጣቢያ ቆሼ 32ኛ ክ/ጦር ብርጌድ 2 ተብሎ በሚጠራው የምርጫ ጣቢያ ከጥዋቱቱ 12፡ ሰዓት ከመሆኑ በፊት ቀድሞ የድመጽ መስጠት ሂደቱ ተጀምሮ ነበር።

4. የምርጫ ህጉ በወታደራዊ ካምፖች፣ በግል መኖሪያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ የኀይማኖት ተቋማት ህንጻዎች፣ የጤና ተቋማት፣ የመዝናኛ ማዕከላት እና የፖለቲካ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ያሉ ቦታዎች ውስጥ የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋምን ይከለክላል። ይህንን በተመለከተም የሕብረት ለምረጫ ታዛቢ ቡድን ምልከታ አድርጓል፡፡ በዚህ መሠረት የኅብረቱ ታዛቢዎች በታዘቧቸው በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ሕጉ ባልተከለከሉ ቦታዎች መቋቋማቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

5. በምርጫ ቀን የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ፣ የምርጫ ህጉ በምርጫ ጣቢያው ውስጥም ሆን ከምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ላይ ወይም ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ማንኛውንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎችን በግልፅ ይከለክላል። ከዚህ ጋር በተያያዝ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች ሪፖርት አልተደረገም።

## የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት በተመለከተ

1. የምርጫ ጣቢያዎች የሚቋቋሙበት ቦታ ለዜጎች ያላቸው ተደራሽነት ዜጎች በምርጫ ሂደቱ በሚኖራቸው ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ አለው። በዚህ ረገድ የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያሣዩት 10 (83%) የምርጫ ጣቢያዎች በድንኳን ውስጥ የተቋቋሙ/ የተደራጁ መሆኑን፤ አንድ ( 8%) የምርጫ ጣቢያ ህንፃ ላይ/ውስጥ መቋቋሙን፤ ሌላ አንድ (8%) የምርጫ ጣቢያ ደግሞ በቆርቆሮ ወይም በዛፍ ጥላ ስር እንደነበሩ ሪፖርት ተደርጓል።

2. ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሃይ ለመከላከል የሚያስችል መጠለያ መኖሩ በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ውስጥ አንዱ አስፈላጊ ነገር ነው። ከዚህ አንፃርም 3 (25%) የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች የነበሯቸው ሲሆን ፤ 9 (75 %) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሃይ የሚከላከሉ መጠለያዎች እንዳልነበሯቸው የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።

3. በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ጣቢያዎች ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ነው፡፡ መራጮች በቀላሉ ድምጻቸውን ለመስጠት እንዲችሉ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ በሆኑ አካባቢዎች ሊቋቋሙ ይገባል። የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ለአካል ጉዳተኞች (persons with disabilities-(PWDs))፣ ለነፍሰ ጡር እናቶች፣ ሕፃናት ለያዙ ሴቶች እና አረጋውያን ወይም ለአቅመ-ደካማ እና የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች ተደራሽነትን ግምት ውስጥ ያሰገባ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አኳያም የሕብረቱ ታዛቢዎቹን ባስማራባቸው 12 ጣቢያዎች ሁሉም (100 %) የምርጫ ጣቢያዎች ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የህብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ ያደረጉና ተደራሽ ነበሩ።

4. የድምጽ መስጫ ቁሳቁስ አቅርቦት መሟላት ለድምጽ አሰጣጥ ሂደት እጅግ ወሳኝ ነው። እናም ከድምጽ መስጫ ዕለት አስቀድሞ ሁሉም መራጮች ድምጽ መስጠት እንዲችሉ የምርጫ ቁሳቁሶች በእያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ጣቢያ ማሟላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎችን በተሟላ መንገድ ለማዘጋጀት የምርጫ ቁሳቁሶች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኘት አስፈላጊ ነገር ነው። ከእነዚህ ወሳኝ ቁሳቁሶች መካከልም:- የድምፅ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ የምርጫ ቦርድ ኦፊሴላዊ ማህተም፣ የማዳመሪያ ቅፅ፣ የውጤት መሳወቂያ እና የማመሳከሪያ ቅፆች፣ የማይፋቅ/የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምፅ መስጫ ሳጥን (Ballot Box)፣ መከፈቱ የሚያስታውቅ ቁለፍ እና የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች ይገኙበታል። እነዚህን ወሳኝ ቁሳቁሶች ተሟልተዋል ወይም አልተሟሉም በሚለው ዙሪያ ኅብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኘታቸውን ሪፖርተ አድርገዋል።

5. በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የምርጫ ጣቢያው ኃላፊው የድምፅ መስጫ ሳጥኖች (Ballot Boxes) ባዶ መሆናቸውን ለታዛቢዎችና ለፓርቲ ተወካዮች እንዲያሳዩ ያስገድዳል። በመሆኑም በ 12ቱም ጣቢያዎች ተሰማርተው የነበሩ የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንዳደረጉት በሁሉም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ የጣቢያ ኃላፊዎች የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ ምሆናችወን አሳይተዋል።

6. የምርጫ ህጉ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለማስጀመር ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈፃሚዎች መገኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይህንን በተመለከተም ኅብረቱ ያሰማራቸው የታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያመላክተው በምርጫ ጣቢያዎች በአማካይ አምስት የምርጫ አስፈጻሚዎች መገኘታቸውን ከነዚህም መካከል በአማካይ ሁለት የምርጫ አስፈጻሚዎች ሴቶች እንደነበሩ ሪፖርት አድርገዋል። የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎችን የሥርዓተ-ፆታ ውክልናን/ድርሻ/ በተመለከተ በ4 (33 %) የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎቹ ሴቶች ሲሆኑ፤ በቀሪዎቹ 8 (67%) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎቹ ወንዶች እንደነበሩ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ ኅብረቱ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች አንድም አካል ጉዳተኛ የምርጫ አስፈጻሚ አለመኖሩን አረጋግጠዋል።

7. የምርጫ ህጉ የምርጫ ጣቢያዎች ቢያንስ ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን እንደሚያቋቁሙ ህጉ ይደነግጋል። ይህንን በተመለከተም 3(25%) የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አቋቁሙው የነበረ ሲሆን፤ በ9 (75 %) የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ምንም አይነት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያላቋቋሙ እንደነበሩ የታዛቢዎች ሪፖርት ያሳያል።

8. የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት እንዳለባቸው የምርጫ ህጉ ይደነግጋል፡ ፡ የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያዎች መገኘታቸውን በተመለከተ፣ በ8 (67%) የምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ውኪሎች መግኘታቸውን ታዛቢዎች የገለጹ ሲሆን በ4 (33%) የምርጫ  ጣቢያዎች ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች አለመገኘታችውን የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን በተመለከተ

የድምጽ-መስጫ ጣቢያዎች ከተከፈቱ እና ከተደራጁ//በኋላ ቀጣዩ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ነው። በዚህም መሰረት ሕብረት ለምርጫ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የነበረውን የድምጽ አሰጣጥ ሂደት  ከታዛቢዎቹ የሰበሰባቸውን የትዝብት ግኝቶች እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

1. በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ማለትም በ12ቱም (100 %) የድምጽ መስጫ ጣቢያወች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለመታዘብ የሄዱ የሕብረቱ ታዛቢዎች ጣቢያዎቹን ለቀው እንዲወጡ አለመጠየቃቸውን  ወይም አለመገደዳቸውን ታዛቢወች ሪፖርት አድርገዋል፡፡

2. የምርጫ ህጉ አካል ጉዳተኞች (PWDs)፣ አረጋውያን፣ አቅመ ደካሞች ወይም የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው ሰዎች፣ ነፍሰ ጡር እናቶች እና ሕፃናትን/ልጆችን የያዙ ወላጆች ቅድሚያ መሰጠት ተሰጥቷቸው መምረጥ እንዳለባቸው  ያዝዛል። ከዚህ አንፃርም በ12ቱም (100%) የምርጫ  ጣቢያዎች  አካል  ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ አቅመ  ደካሞችን፣ እርጉዝ ሴቶች፣ እና ህጻናትን የያዙ ወላጆች በምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች  ቅድሚያ የተሰጣቸው መሆኑን   ታዛቢዎች ገልጸዋል።

3. አካል ጉዳተኛ የሆኑ ግለሰቦች (Persons with disabilities) ራሳቸው በመረጡት የግል ረዳቶቻቸው እገዛ መምረጥ እንዳለባቸው ህጉ ያዛል። ከዚህ አንፃርም  በ 8(67%)የምርጫ ጣቢያዎች አካል  ጉዳተኞች በመረጡት የግል ረዳት  እግዛ  እንዲደረግላችው የተፈቀደላቸው ሲሆን፤ በ 4 (33 %)  የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ የትኛውም መራጭ እርዳታ አላስፈለገውም ነበር። በተጨማሪም እርዳታ የሚሹ መራጮችን በተደጋጋሚ የረዱ መራጮች አልነበሩም።

4. የምርጫ ህጉ  መራጮች ለመመዝገብ እና/ወይም ድምጽ ለመስጠት የነዋሪነት  እና የማንነት ማረጋገጫ እንዲያሳዩ ያስገድዳል። ማንነታቸውን እና  የመኖሪያ ቦታቸውን ማረጋገጥ ያለቻሉ መራጮች በድምጽ አሰጣጡ  ሂደት  እንዲሳተፉ ሀጉ አይፈቀድም። ነገር ግን የምርጫ ህጉ እንደዚህ አይነት  አጋጣሚዎች ሲከሰቱ መራጮች ማንነታችወን  በምስክሮች እንዲያረጋግጡ እና እንዲመርጡ ህጉ ይፈቅዳል።  በዚሁ  መሰረት በምርጫ ጣቢያዎች የማንነት እና/ወይም የነዋሪነት ማረጋገጫ ማቅረብ ያልቻሉ መራጮች  ማንነታቸውን የሚያረጋግጡ ምስክሮችን በማቅረብ ድምጽ እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል።

5. የምርጫ ህጉ  የተመዘገቡ እና ለመምረጥ የነዋሪነት  እና የማንነት ማረጋገጫ ማቅረብ የቻሉ  መራጮች ድምጽ የመስጠት መብት እንዳላቸው የደነገጋል። ከዚህ ጋር በተያየዝ በ10 (83%) የምርጫ ጣቢያዎች የነዋሪነት እና የማንነት ማረጋገጫ ያቀረቡ መራጮች ድምጻቸውን እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል። በተቀሩት 2 (16%)  ጣቢያዎች ደግሞ አንዳንድ ግለሰቦች መታወቂያ ቢያቀርቡም ያቀረቧቸው መታወቂያዎች ከስድስት ወር ባነሰ ጊዜ የተሰጡ  በመሆናቸው እንዳይመዘገቡ እና እንዳይመርጡ ተደርጓል።

6. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት አንድ መራጭ ከመምረጡ በፊት የማይጠፋ/ የማይለቅ ቀለም ጣቱ ላይ በመቀባት ምልክት መደረግ እንዳለበት ያስገድዳል። ይህንን በተመለከተም በ 12ቱም  (100%)  የምርጫ ጣቢያዎች  በሁሉም መራጮች ጣት  ላይ  የማይለቅ ቀለም እንደተደረገባቸው ሪፖርት ተደርጓል።

7. የምርጫ ህጉ በድምጽ መስጫ ቀን በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸው የተገኘ መራጮች መምረጥ የሚችሉት ለመራጭነት በተመዘገቡበት ጣቢያ ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል። በተጨማሪም የመራጮች ስም በመራጮች መዝገብ ውስጥ መገኘቱን የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። በዚሁ መሰረት በሁሉም ማለትም በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የመረጡ መራጮች በሙሉ ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ የተገኘ መሆኑን ሕብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች ሪፖርት ያሳያል።

8. የምርጫ ጣቢያ ሀላፊ በሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ለመራጮች ከመሰጠታቸው በፊት ማህተም ማድረግ እንዳለበት የምርጫ ህጉ ያስገድዳል። በዚህም መሰረት በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች፣ የምርጫ አስፈጻሚወች በሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ማህተም ማድረጋቸውን የኅብረቱ ታዛቢውች ሪፖርት አድርገዋል።

9. ማንኛውም የድምፅ  አሰጣጥ ሂደት ምስጢራዊነቱን የጠበቀ መሆን እንዳለበት  የምርጫ ህጉ ይደነግጋል። በዚህ ጉዳይም የሕብረቱ ታዛቢዎች  ሪፖርት እንደሚያመላክተው በሁሉም ማለትም በ12ቱ (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ሲደረግ የነበረው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ሚስጥራዊነታቸውን የጠበቁ እንደነበሩ ሪፖርቶች ያሳያሉ።

10. በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የሚታይ የአካል ጉዳት የሌላባቸው ወይም አረጋውያን ያልሆኑ መራጮች  በሚመርጡበት ወቅት ደጋፍ አልተደረገላቸውም።

11. በድምፅ መስጫ እለት ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መገኘት እንደሌለባቸው የምርጫ ህጉ ይደነግጋል። እናም በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ያልተፈቀደላቸው ሰዎች በጣቢያዎች ውስጥ አልተገኙም።

12. በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መመሪያ መሰረት መራጮች፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እንዲሁም ሴቶች ማንኛውም አይነት ተፅዕኖ እና/ወይም ግፊት እና ጥቃት ሰለባ መሆን እንደሌለባቸው ይደነግጋል። በዚህ ረገድ ሁሉም የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንዳደረጉት በ12ቱም (100 %) የምርጫ ጣቢያዎች በአጠቃላይ የማስፈራራት እና እንግልት በተለይም ሴት መራጮች፣ የፓርቲ ወኪሎች፤ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈጻሚዎች የጥቃት ሰለባዎች አልነበሩም።

13. የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ በድምፅ መስጫ እለት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ያለምንም መቋራረጥ ቀኑን ሙሉ መካሄድ እንዳለበት ይደነግጋል። እናም በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ አንድም ጊዜ አልተቋረጠም።

14. በምርጫ ህጉ ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው የምርጫ ጣቢያዎች ህጋዊ የመዝጊያ ጊዜ ከቀኑ 12፡00 ሰዓት ነው። ስለሆነም ሁሉም (100 % ) የምርጫ ጣቢያዎች በሕጉ በተደነገገው መሰረት መዘጋታቸውን ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።

## የድምፅ ቆጠራ ሂደቱን በተመከለተ

የድምጽ-መስጫ ጣቢያዎች ከተከፈቱ በኋላ ቀጣዩ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ነው። በድምጽ መስጫ ቀን ካሉት ሂደቶች መካከል የድምጽ ቆጠራ አንዱና የመጨረሻው ሂደት ነው። በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ከጠናቀቀ በኋላ የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ጣቢያውን ይዘጋል። ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዘጋት በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ታዛቢዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች በተገኙበት ሁሉም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የምርጫ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት የድምፅ ቆጠራው ይከናወናል። ይህንን አስመልክቶም ኅብረት ለምርጫ በድምጽ ቆጠራ ሂደቱ ላይ ከታዛቢዎቹ የሰበሰባቸውን የሪፖርት ግኝቶች እንደሚከተለው አቅርቧዋል።

1. የምርጫ ህጉ የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ታዛቢዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በተገኙበት እንዲካሄድ ያስገድዳል። በዚህም መሰረት የኅብረቱ ታዛቢዎች ያቀረቧቸው የምልከታ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት በድምጽ ቆጠራ ወቅት በ12ቱም (100 %) የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የነበሩ ታዛቢዎች ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጡ አልተጠየቁም።

2. የምርጫ ህጉ የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ በድምፅ መስጫው ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ እንደሚካሄድ ይገልፃል። እናም በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ ቆጠራው ሂደት በድምጽ መስጫ ቀን በጣቢያዎቹ ውስጥ ተካሂዷል።

3. የድምጽ ቆጠራው በ12ቱም (100 %) የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አልተቋረጠም ነበር።

4. የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ያለምንም ጣልቃ ገብነት፣ ወከባ እና/ወይም ማስፈራሪያ እንዲካሄድ የምርጫ ህጉ ይደነግጋል፡፡ ይህንን በተመለከተም የሕብረቱ የምልከታ ሪፖረት እንደሚያሳየው በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ ቆጠራው ሂደት ያለምንም አይነት ጣልቃገብነት፣ ትንኮሳ እና/ወይም ማስፈራራት በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ተከናውኗል።

5. በምርጫ ህጉ ድንጋጌ መሰረት በድምፅ ቆጠራው ሂደት ውስጥ ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ለታዛቢዎችና ለፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርግቶ በግልፅ ማሳየት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ ኅብረቱ ያሰማራቸው የታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት በ12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ ሃላፊዎች በድምጽ ቆጠራው ወቅት የምርጫ ወረቀቶቹን በግልፅ አሳይተዋል።

6. የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸወን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ያሥችል ዘንድ ተመሳሳይ መስፈርቶችን መከተል እና መተግበር እንደሚያስፈልግ የምርጫ ህጉ ይገልፃል። ከዚህ አንፃርም በ 12ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን የሚያስችሉ ወጥ የሆኑ መስፈርቶችን መከተላቸውንና መተግበራቸውን የትዝብት ሪፖርቶች ያሳያሉ።

7. ምንም አንኳ ታዛቢዎች ዜጎች ቅሬታቸውን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሲገልጹ ሰምተናል ቢሉም በምርጫ ጣቢያ ለተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ግን የቀረቡ መደበኛ ቅሬታዎች አልነበሩም ።

## ሶማሌ ክልል (ጅግጅጋ የምርጫ ክልል)

ይህ የምልከታ ሪፖርት በሶማሌ ክልል በጅግጅጋ ምርጫ ክልል በ8 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ተሰማርተው ቀኑን ሙሉ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ሲታዘቡ በነበሩ 8 ቋሚ/ ተቀማጭ ታዛቢዎች(Stationary Observers) የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች አማካኝነት በተሰበሰበው መረጃላይ ተመስርቶ የተዘጋጅ ሲሆን፤ ኅብረቱ ታዛቢዎችን ያሰማራበት መንገድም አመቺነትን መሰረት ያደረገ የስምሪት ዘዴን (Convenient deployment method) በመጠቀም ነበር። የሪፖርቱ ዋና ትኩረትም የምርጫ አስፈጻሚወች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስን፤ የምርጫ ጣቢያዎችን አደረጃጀትን፤ የድምጽ መሰጫ ጣቢያዎች አከፋፈትን ፤ የድምጽ አሰጣጥ ሂድትን ፤ ፤የድምጽ መሰጫ ጣቢያ አዘጋግ ስርዓትን፣ የድምፅ ቆጠራ እና የውጤት ማዳመርን የሚመለከቱ መረጃዎች ላይ ነው። መረጃው በጅግጅጋ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ 8 የከተማ የምርጫ ጣቢያዎች የተሰበሰበ ነው። የሪፖርቱ ዝርዝር ይዘት እንሚከተለው ቀርቧል።

## ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መድረስን በተመለከተ

1. በድምጽ መስጫው ዕለት ከሚጠበቁ ወሳኝ ኹነቶች መካከል የምርጫ አስፈፃሚዎች በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ መድረስ አንዱ ነው። የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ከጠዋቱ 12 ሰዓት ለመጀመር እንዲያስችል፤ የምርጫ ቦርድ አመራሮች እና ሰራተኞች የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ድምፅ ለመስጠት መዘጋጀታቸውን ለማረጋገጥ የምርጫ ሰዓቱ ከመድረሱ በፊት ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ቀድመው በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እንዲገኙ ይጠበቃል። ይህንን አስመልክቶም የኅብረት የምርጫ ታዛቢዎች እንዳረጋገጡት በ8ቱም (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚውች ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ከመሆኑ በፊት ማለትም ከማለዳው 11፡30 በምርጫ ጣቢያዎች ተገኝተዋል።
2. በሁሉም(8) የምርጫ ጣቢያዎች የተሰማሩ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለመታዘብ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተገኝተው እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል።
3. በምርጫ ህጉ መሰረት ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች 12፡00 ሰዓት ከመሆኑ በፊት መከፈት እንዳለባቸውና ልክ ከጥዋቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ ድምፅ መስጠት ማስጀመር አለባቸው፡፡ ይህንን በተመለከተም የኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት እንደሚያሳየው በሁሉም(8) የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ልክ ከጥዋቱ 12፡00 ሰዓት ላይ ተጀምሯል።
4. የምርጫ ህጉ በወታደራዊ ካምፖች፣ በግል መኖሪያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በኀይማኖት ተቋማት፣ በጤና ተቋማት፣ በመዝናኛ ማዕከላት እና በፖለቲካ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ውስጥ የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም ይከለክላል። በዚህ መሠረት የኅብረቱ ታዛቢዎች በታዘቧቸው በሁሉም(8) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ሕጉ ባልተከለከሉ ቦታዎች የተደራጁ እንደነበር ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።
5. በምርጫ ቀን የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ፣ የምርጫ ህጉ በምርጫ ጣቢያው ውስጥም ሆነ ከምርጫ ጣቢያ በ200 ሜትር ርቀት ላይ ማንኛውንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች መደረግ እንደሌለባቸው በግልፅ ይከለክላል። ከዚህ ጋር በተያያዝ በ7ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች እንዳልተካሄዱ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። ከዚህ በተቃራኒ በአንድ የምርጫ ጣቢያ ልዩ ስሙ "ጅ 09 ምርጫ ጣቢያ ዞን-3/ሐ" በተባለ የምርጫ ጣቢያ በ20 ሜትር ውስጥ አንዳንድ ግለሰቦች መራጮች የብልጽግና ፓርቲን እንዲመርጡ ምራጮችን ሲቀቀቅስ እንደነበር ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል።በተጨማሪም ከሶማሌ ክልል የተመለመሉ የምርጫ አስፈጻሚውች ሊመረጡ ወደ ጣቢያው የሚሄዱ መራጮችነ በድምጽ መስጫ ወረቀቶች ላይ ካሉት ከ3 እስከ 9 ያሉትን ዕጩዎች ብቻ እንዲመርጡ ሲነግሯቸው እንደነበር ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። ይህም በምርጫ ሂደቱ ላይ ጣልቃገብነት የነበረ መሆኑን ከማመላከት ባሻገር በአንዳንድ የምርጫ አሰፈፃሚዎች ላይ የገለልተኝነት ችግር እንደነበር ያሳያል።

## የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አደረጃጀትን በተመለከተ

1. የምርጫ ጣቢያዎች የሚቋቋሙበት ቦታ ጣቢያዎቹ ለዜጎች ያላቸውን ተደራሽነት ዜጎች በምርጫ ሂደቱ በሚኖራቸው ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ አለው። በዚህ ረግድ 6 የምርጫ ጣቢያዎች በድንኳን ውስጥ ተቋቁመው/ተደራጅተው የነበረ ሲሆን፤ 2 ጣቢያዎች ደግሞ በህንፃዎች ውስጥ የነበሩ መሆናቸውን በኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት ተደርጓል።
2. ወረፋ ይዘው የሚጠብቁ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሐይ ለመከላከል ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መጠለያ መኖሩ በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት አስፈላጊ ነገር ነው። ከዚህ አኳያም 6 የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች የነበሯቸው ሲሆን ፤ በአንፃሩ 2 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሃይ የሚከላከሉ መጠለያዎች አልነበሯቸውም።
3. በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ጣቢያዎች ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለው ነው። መራጮች በቀላሉ ድምጻቸውን ለመስጠት እንዲችሉ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ በሆኑ አካባቢዎች ሊቋቋሙ ይገባል። የምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት በተለይም ለአካል ጉዳተኞች ፣ ለነፍሰ ጡር እናቶች፣ ሕፃናት ለያዙ ሴቶች እና አረጋውያን ወይም ለአቅመ-ደካማ እና የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች ተደራሽነትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡ በዚህ መሰረት 5 የምርጫ ጣቢያዎች ከዚህ በላይ ለተዘረዘሩት የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርገው የተደራጁ የነበረ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ 3ቱ የምርጫ ጣቢዎች ደግሞ ይህንን ጉዳይ ተሳቢ ያላደረጉና ተደራሽ እንዳልነበሩ የታዛቢዎች ሪፖርት ያሳያል።
4. የድምጽ መስጫ ቁሳቁስ አቅርቦት መሟላት ለድምጽ አሰጣጥ ሂደት እጅግ ወሳኝ ነው። እናም ከድምጽ መስጫ ዕለት አስቀድሞ ሁሉም መራጮች ድምጽ መስጠት እንዲችሉ የምርጫ ቁሳቁሶች በእያንዳንዱ የድምጽ መስጫ ጣቢያ መሟላታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎችን በተሟላ መንገድ ለማዘጋጀት የምርጫ ቁሳቁሶች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኘት አስፈላጊ ነገር ነው። ከእነዚህ ወሳኝ ቁሳቁሶች መካከልም፡ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ የምርጫ ቦርድ ኦፊሴላዊ ማህተም፣ የማዳመሪያ ቅፅ፣ የውጤት መሳወቂያ እና የማመሳከሪያ ቅፆች፣ የማይፋቅ/የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምፅ መስጫ ሳጥን (Ballot Box)፣ መከፈቱ የሚያስታውቅ ቁለፍ እና የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች ይገኙበታል፡፡

ይህንን በተመለከተም እነዚህ ወሳኝ ቁሳቁሶች በምርጫ ጣቢያዎች ተሟልተው ይገኙ እንደሆነ የተጠየቁት ኅብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በታዘቧቸው በ7ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም አስፈላጊ የምርጫ ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘታቸውን ሪፖርት አድርገዋል። ይህ እንዳለ ሁኖ በአንድ የምርጫ ጣቢያ ጅ 06 ምርጫ ጣቢያ 02 የሚባል የምርጫ ጣቢያ የቅሬታ ሰሚ ቅጽ የተጓደለ ሲሆን ሌሎች ቁሳቁሶች ግን ተሟልተው እንደነበር የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች ያሳያሉ።

5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ድምፅ የመስጠት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች (Ballot Boxes) ባዶ መሆናቸውን ለታዛቢዎችና ለፓርቲ ተወካዮች እንዲያሳይ የምርጫ ህጉ ያስገድዳል። ከዚህ አኳያም በሁሉም (8) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ድምፅ የመስጠት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ ምሆናችወን አሳይተዋል።

6. የምርጫ ህጉ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለማስጀመር ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈፃሚዎች መገኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል። እናም ኅብረቱ ያሰማራቸው የታዛቢዎች ሪፖርቶች እነደሚያሳዩት በምርጫ ጣቢያዎች በአማካይ 4 የምርጫ አስፈጻሚዎች መገኘታቸውን ሲገልፁ፤ ከነዚህም መካከል በአማካይ 2 የምርጫ አስፈጻሚዎች ሴቶች እንደነበሩ ሪፖርት አድርገዋል። የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎችን የሥርዓተ-ፆታ ውክልና (ድርሻ) በተመለከተ በ2 የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎቹ ሴቶች ሲሆኑ በቀሪዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎቹ ወንዶች እንደነበሩ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ ኅብረቱ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች አንድም አካል ጉዳተኛ የምርጫ አስፈጻሚ አለመኖሩን አረጋግጠዋል።

7. የምርጫ ህጉ ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በምርጫ ጣቢያዎች እንደሚያቋቁም ይደነግጋል። በዚሁ መሰረት ጅ -06 ምርጫ ጣቢያ 02 እና ጅ -04 ምርጫ ጣቢያ 03 በተባሉ ሁለት የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተቋቁመው የነበረ ሲሆን፤ በአንፃሩ ደግሞ በሌሎች ስድስት የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ኮሚቴዎች አልተቋቋሙም ነበር።

8. የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያዎች መገኘታቸውን በተመለከተ፣ በ6 የምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ውኪሎች መገኘታቸውን ታዛቢዎች የገለፁ ሲሆን፤ በሁለት የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች እንዳልነበሩ ተዛቢዎች አመላክተዋል።

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን በተመለከተ

1. የድምጽ-መስጫ ጣቢያዎች ከተከፈ በኋላ ቀጣዩ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ነው። በዚህም መሰረት ሕብረት ለምርጫ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የነበረውን የድምጽ መስጠት ሂደት ከታዛቢዎቹ የሰበሰባቸውን የሪፖርት ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

2. በሁሉም (8) ትዝብት በተደረገባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን የታዘቡ የኅብረቱ ታዛቢዎች የምርጫ ጣቢያዎቹን ለቀው እንዲወጡ አለመጠየቃቸውን ወይም አለመገደዳቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

3. የምርጫ ህጉ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ አቅመ ደካሞች ወይም የመንቀሳቀስ ችግር ያለባቸው ሰዎች፣ ነፍሰ ጡር እናቶች እና ሕፃናትን የያዙ ወላጆች ቅድሚያ መሰጠት እንዳለባቸው እና መምረጥ እንዳለባቸው ያዝዛል፡፡ ከዚህ አንፃርም በ8ቱም የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች ለአካል ጉዳተኞችን አረጋውያን፣ ለአቅመ ደካሞች፣ ለእርጉዝ ሴቶች፣ እና ህጻናትን ለያዙ ወላጆች ቅድሚያ የሰጧቸው መሆኑን ታዛቢዎች ገልጸዋል።

4. አካል ጉዳተኛ የሆኑ ግለሰቦች (Persons with disabilities) ራሳቸው በመረጡት የግል ረዳቶቻቸው እገዛ እንዲመርጡ የምርጫ ህጉ ያዝዛል። ስለሆነም ምልከታ በተደረገባቸው ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች አካል ጉዳተኞች በመረጡት የግል ረዳት እግዛ እንዲደረግላችው ተፈቅዶላቸው የመረጡ መሆኑን ሪፖርቶች ያሳያሉ።

5. የምርጫ ህጉ መራጮች ለመመዝገብ እና/ወይም ድምጽ ለመስጠት የነዋሪነት እና የማንነት ማረጋገጫ እንዲያሳዩ ያስገድዳል። ማንነታቸውን እና የመኖሪያ ቦታቸውን ማረጋገጥ ያለቻሉ መራጮች በድምጽ አሰጣጡ ሂደት እንዲሳተፉ ህጉ አይፈቀድም። ነገር ግን የምርጫ ህጉ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ሲክስቱ መራጮች ማንነታችወን በምስክሮች እንዲያረጋግጡ እና እንዲመርጡ ህጉ ይፈቅዳል። በዚሁ መሰረት ምርጫ ጣቢያዎች የማንነት ማረጋገጫ እና/ወይም የነዋሪነት ማረጋገጫ ያላቀረቡ መራጮች አስመስክረው ድምጽ እንዲሰጡ የተደረገ መሆኑን ሪፖርቶች ያሳያሉ።

6. በምርጫ ህጉ መሰረት የተመዘገቡ እና ለመምረጥ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ማቅረብ የቻሉ መራጮች ድምጽ የመስጠት መብት እንዳላቸው ህጉ ይደነግጋል። ከዚህ ጋር በተገናኘ በሁሉም(8) ምልከታ በተደረገባሰንዶጣቢያዎች አስፈላጊ የሆኑ ሰንዶችን ያሟሉ መራጮች ድምጻቸውን እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል።

7. በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት አንድ መራጭ ከመምረጡ በፊት የማይጠፋ/ የማይለቅ ቀለም ጣቱ ላይ በመቀባት ምልክት መደረግ እንዳለበት ያስገድዳል። ትዝብት በተደረገባቸው ሁሉም (8) የምርጫ ጣቢያዎች በሁሉም የመራጮች ጣት ላይ የማይለቅ ቀለም እንደተደረገባቸው ሪፖርት ተደርጓል።

8. በምርጫ ህጉ  መሰረት የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የመራጮች ስም በመራጮች መዝገብ ውስጥ  መገኘቱን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። በዚሁ መሰረት በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የመረጡ መራጮች በሙሉ ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ተገኝቷል።

9. የምርጫ ህጉ  የምርጫ  ጣቢያ ሃላፊዎች   የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ለመራጮች ከመስጠታቸው በፊት በሁሉም የድምጽ  መስጫ ወርቀቶች ማህተም እንዲያደርጉ ያስገድዳል። በዚሁ መሰረት ትዝብት  በተደረገባቸው ሁሉም (8) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ሃለፊዎች በሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ማህተም ማድረጋቸውን የሕብረቱ ታዛቢዎች ግኝት ያመላክታል።

10. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ህግ  ማንኛውም የድምፅ  መስጠት ሂደት ምስጢራዊነቱን የጠበቀ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። ስለሆነም በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ምስጢራዊነት ቀኑን ሙሉ ተከብሮ ነበር።

11. በሶስት የምርጫ ጣቢያዎች ግልፅ የሆነ አካል ጉዳት የሌለባቸው እና አረጋውያን ያልሆኑ መራጮች እርዳታ/ድጋፍ ተደርጎላቸው እንዲመርጡ ተደርጓል።

12. የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ በድምፅ መስጫ እለት ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች  መገኘት እንደሌለባቸው ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አኳያም በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች  በድምጽ አሰጣጥ  ሂደት ያልተፈቀደላቸው ሰዎች በምርጫ ጣቢያዎቹ ውስጥ አልተገኙም ነበር።

13. በኢትዮጵያ የምርጫ መመሪያ መሰረት መራጮች፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እንዲሁም ሴቶች ማንኛውም አይነት ተፅዕኖ እና/ወይም ግፊት እና ጥቃት ሰለባ መሆን እንደሌለባቸው ይደነግጋል። በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የማስፈራራት እና  እንግልት  በተለይ ሴት መራጮች፣ የፓርቲ  ወኪሎች፤ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈጻሚዎች የጥቃት ሰለባዎች አልነበሩም።

14. በድምፅ መስጫ እለት የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ያለምንም መቆራረጥ ቀኑን ሙሉ  መካሄድ እንዳለበት የምርጫ ህጉ ያስገድዳል። እናም በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ያለምንም መቆራረጥ ቀኑን ሙሉ ሲካሄድ እንደነበር ሪፖርቶቹ ያሳያሉ።

15. ምንም እንኳን የምርጫ ህጉ በይፋ የሚደነግገው የምርጫ ጣቢያዎች ህጋዊ የመዝጊያ ሰዓት ከቀኑ 12፡00 ሰዓት እንደሆነ ቢያስቀምጥም ከቀኑ 12፡00 ሰዓት  በፊት ሰልፍ ይዘው የሚጣባበቁ መራጮች ካሉ  የምርጫ ጣቢያው ሃላፊው ሰልፍ የያዙት ሁሉም መራጮች ድምፅ መስጠታቸውን ካረጋገጠ በኋላ የምርጫ ጣቢያውን በር መዝጋት እንዳለበት ህጉ ያሥቀምጣል፡፡ ከዚህ አኳያም ከቀኑ 12፡00 ሰዓት ላይ በምርጫ ጣቢያው በር  ላይ ሰልፍ ይዘው ሲጠብቁ  የነበሩ መራጮች በምርጫ በበህጉ መሰረት በአምስት  የምርጫ ጣቢያዎች ድምጽ እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል። በሌላ በኩል በሶስት የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ በጣቢያዎቹ የመዝጊያ ሰዓት ላይ ሰልፍ ይዘው የሚጠብቁ መራጮች አልነበሩም።

## የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን በተመለከተ

የድምጽ-መስጫ ጣቢያዎች ከተከፈቱ በኋላ ቀጣዩ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ነው። በድምጽ መስጫ  ቀን ካሉት ሂደቶች መካከል   የድምጽ ቆጠራ አንዱና  የመጨረሻው ሂደት ነው። በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት የድምፅ መስጠት ሂደቱ ከጠናቀቀ በኋላ የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ጣቢያውን ይዘጋል። ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መዘጋት በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ታዛቢዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች በተገኙበት  ሁሉም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የምርጫ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት የድምፅ ቆጠራው ይከናወናል። ይህንን አስመልክቶም ኅብረት ለምርጫ  በሶማሌ ክልል ጅግጅጋ የምርጫ ክልል በተከናወኑ የድምጽ ቆጠራ ሂደት ላይ  ከታዛቢዎቹ የሰበሰባቸውን የሪፖርት ግኝቶች እንደሚከተለው አቅርቧዋል።

1. በድምጽ ቆጠራ ወቅት  በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ የሕብረቱ ታዛቢዎች ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጡ አልተጠየቁም።

2. በምርጫ ህጉ መሰረት የድምፅ ቆጠራ በምርጫው ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ  መከናወን አለበት፡፡ ከዚህ አኳያም የድምጽ ቆጠራው በድምጽ መስጫ ቀን በሁሉም(8) ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች  ውስጥ ተካሂዷል።

3. የድምጽ ቆጠራው ሂደት በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች አልተቋረጠም ነበር።

4. የድምፅ ቆጠራ ሂደቱ ያለምንም አይነት ጣልቃገብነት፣ ወከባ እና/ወይም ማስፈራሪያ እንዲካሄድ የምርጫ ህጉ ይደነግጋል፡፡ በሁሉም ትዝብት  በተደረገባቸው ጣቢያዎች  በቆጠራው ሂደት  ምንም አይነት   ጣልቃገብነት፣ ትንኮሳ እና/ወይም ማስፈራራት አልነበረም።

5. እንደ ምርጫ ህጉ ድንጋጌ ከሆነ ድምፅ ቆጠራው ሂደት ውስጥ ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ለታዛቢዎችና ለፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርግቶ በግልፅ ማሳየት ይኖርበታል። ስለሆነም የኅብረቱ ታዛቢዎች ባደረጉት ትዝብት በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች በድምጽ ቆጠራው ወቅት የድምጽ መስጫ ወረቀቶቹን በግልፅ አሳይተዋል።

6. የምርጫ ጣቢያ ጣቢያ ሃላፊዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ያሥችል ዘንድ ተመሳሳይ መስፈርቶችን መከተል እና መተግበር እንደሚያስፈልግ የምርጫ ህጉ ይገልፃል። እናም በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊወች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸውን ድምጽ የተሰጠባቸውን ወረቀቶችን ለመወሰን የሚያስችሉ ወጥነት ያላቸው መስፈርቶችን መተግበራቸውን ሪፖርቶች ያሳያሉ።

7. ምንም አንኳ ታዛቢዎች ቅሬታቸውን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ዜጎች ሲገልጹ ሰምተናል ቢሉም በምርጫ ጣቢያ ለተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ግን የቀረቡ መደበኛ ቅሬታዎች አልነበሩም።

## የድህረ-ምርጫ ምልከታ ግኝቶች

በአንድ ምርጫ ሂደት የድኅረ ምርጫ ከባቢ ሁኔታ ልዩ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ስለሆነም ኅብረት ለምርጫ በድህረ-ምርጫ የነበረውን አጠቃላይ ፖለቲካዊ ምህዳር፣ የህዝብ ግብረ መልስ (አስተያየት) (public opinion)፣ እንደዚሁም የሲቪክ ምህዳሩን ለመቃኘት ያስችለው ዘንድ 11 ታዛቢዎችን አሰማርቶ ነበር። የሚከተለው መረጃ የተጠናቀረው ከ11 ታዛቢዎች በተሰበሰበ መረጃን መሰረት በማድረግ ነው።

## በድህረ-ምርጫው የተከሰቱ ተቃውሞዎች

ሁሉም የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች 11 (100%) ከምርጫ ሂደቱ እና ከውጤቱ ጋር በተያያዙ የመንቀሳቀስ ወይም የመሰብሰብ መብቶች፣ ህዝባዊ ተቃውሞዎች እና ህዝባዊ አመፆች አልነበሩም። በተጨማሪም በመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም በፖለቲካ ፓርቲ አባላት ላይ የእስር፣ የማስፈራራት፣ የማዋከብ፣ የግድያ፣ የጥላቻ ንግግር፣ የስድብ ወይም የማስፈራሪያ ንግግሮች አልነበሩም።

## የመራጮች ግብረ መልስ (አስተያየት) በምርጫ ውጤቶች ላይ

የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ግኝቶች እንደሚያመላክቱት 8 ሪፖርቶች (73%) መራጮች በምርጫው ውጤት ላይ አዎንታዊ አመለካከቶች እንደነበራቸው ሲያሳዩ፣ አንድ (9%) ሪፖርት ደግሞ ህዝቡ በምርጫ በውጤቱ አለመደሰቱን የሚያሳዩ አሉታዊ ስሜቶች የነበሩ መሆኑን አመልክተዋል፣ ሌሎች ቀሪ ሁለት (18%) ሪፖርቶች ደግሞ ገለልተኛ አቋም እንደነበር ያሳያሉ።

- 2 (18%) ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ህዝቡን ለማረጋጋት ያለሙ መግለጫዎች ከምርጫ በኋላ ተሰጥተው ነበር። አራት (36%) ሪፖርቶች ደግሞ የምርጫ ማጭበርበር ውንጀላዎች መኖራቸውን ያመለከቱ ሲሆን ይህም በምርጫው ሂደት መሰረታዊ ስጋቶችን ወይም አለመግባባቶችን የገለፁ ነበር፡፡ አምስት (45%) ሪፖርቶች ደግሞ ይህንን በተመለከተ ከፓርቲዎች ወይም ከዕጩ ተወዳዳሪዎች የተሰጠ መግለጫ የለም ብለዋል።

- የቀረቡ ቅሬታዎችን በተመለከተ፤ 5 (45%) ሪፖርቶች መደበኛ ቅሬታዎች እንደቀረቡ ሲገልጹ፤ 6(55%) ሪፖርቶች ደግሞ ምንም ዓይነት የቀረበ መደበኛ ቅሬታ አለመኖሩን ያሳያሉ።

- የምርጫ ውጤትን በተመለከተ፤ 2 (18%) ሪፖርቶች በመገናኛ ብዙሃን ይፋ ስለተደረጉት የምርጫ ውጤቶች የተጋነኑ ወይም የተሳሳቱ መረጃዎች መኖራቸውን ያመላክታሉ፡፡ ዘጠኝ (82%) ሪፖርቶች ደግሞ እንደዚህ አይነት ጉዳዮችን ሪፖርት አላደረጉም፡፡ በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ውጤትን ይፋ የማድረግ ወይም የማወጅ ስልጣን ያለው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ብቻ ነው። ከዚህ የህግ ድንጋጌ በተቃራኒ ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም የጅግጅጋ ከተማ ከንቲባ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ክልል የውጤት ማሳወቂያ ፎርምን በፌስቡክ ድህረ ገጻቸው በመለጠፍ ብልፅግና ፓርቲ ማሸነፉን ውጤት በቦርዱ ከመገለጹ በፊት ለህዝብ ይፋ አድርገዋል። በተጨማሪም ይህ ከንቲባ የእንኳን ደስ አለን ፕሮግራም በጽህፈት ቤታቸው አዘጋጅተው ነበር።

## በሲቪክ ምህዳሩ ላይ የነበሩ ገደቦችን በተመለከተ

ሁሉም ማለትም 11 (100%) የሕብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት ከምርጫ ጋር በተያያዘ ምንም አይነት በጋዜጠኞች፣ በታዛቢዎች፣ በሲቪል ማህበረሰብ ሰራተኞች እና በዜጎች ላይ የደረሰ እስራት እንዳልነበር ያመለክታሉ፡፡ በሂደቱ ምንም አይነት አዋኪ ነገር ባለመፈጠሩ ምክንያት የፀጥታ አካላትም ሆኑ የህግ አስከባሪ አካላት ጥቃት ወይም ጥፋትን፣ የጥላቻ ንግግርን እና ሃሰተኛ መረጃን ለማስቆም እና/ወይም ለመከላከል የተደረገ የእርምት እርምጃ አልነበረም።

# ምዕራፍ አራት፡ የሪፖርት ግኝቶች ትንተና

ይህ የሪፖርት ክፍል  በቤንሻንጉል ጉሚዝ፣ አፋር፣ ሶማሌ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች የተካሄዱትን ቀሪ እና ድጋሜ ምርጫዎች በተመለከተ የሕብረት ለምርጫ  ታዛቢዎች የምልከታ ሪፖርት ግኝቶች ትንተናዎች፣ የመደምደሚያ ሃሳቦች እና በጉዳዩ ዙሪያ የተሰጡ ጠቃሚ ምክረ-ሃሳቦችን የያዘ ነው።

## ቅድመ- ምርጫ

### የመራጮች ትምህርት

ትኩረታቸውን በመራጮት ምህርት ላይ አድርገው የተፃፉ  የተለያዩ ጽሁፎች እንደሚያሳዩት የመራጮች  እና የስነ-ዜጋ ትምህርት መስጠት ዜጎች መብቶቻቸውን  እና ግዴታዎቻቸውን እንዲያውቁና በመብቶቻቸው እንዲጠቀሙ፣ ግዴታቸውን ደግሞ እንዲወጡ፣ በሃገራቸው ያለውን የፖለቲካ ሥርዓት እንዲሁም አውዱን እንዲረዱ፣ በፓርቲዎች ወይም በዕጩዎች መካከል የሚካሄዱትን ውድድሮች፣ ስለምርጫ ምንነት፣ አስፈላጊነት እና እንዴት እና የት መምረጥ አለባቸው  የመሳሰሉትን ወሳኝ ጉዳዮች እንዲገነዘቡ ለማድረግ ወሳኝ ጉዳይ ነው።[13] ይህም የሚያመላክተው ለአንድ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ መሳካት መራጮች መብቶቻቸውን እና ግዴታዎቻቸውን በመረዳት በህጋዊ መንገድ ተቀባይነት ያለውን ድምጽ ለመስጠት እና በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ትርጉም ያለው ተሳትፎ  እንዲያደርጉ ለማድረግ  ዜጎች ስለምርጫ እና ምርጫ-ነክ ጉዳዮች ግንዛቤ እና እውቀት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል።[14]

በኢትዮጵያ የመራጮች ትምህርትን የማዳረስ ቀዳሚ ኃላፊነት የተሰጠው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው። በአዋጅ ቁጥር 1162/19 አንቀጽ 124(1) በግልፅ እንደተነገገው የስነ-ዜጋና እና የመራጮች ትምህርት የመስጠት ግዴታ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ተሰጥቷል።  ከምርጫ ቦርዱ ሃላፊነት በተጨማሪም የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችም ከምርጫ ቦርዱ ፈቃድ በመውሰድ   የስነ-ዜጋና እና የመራጮች ትምህርት መስጠት እንደሚችሉ እና የራሳቸውን ሚና መጫወት እንደሚችሉ በዚህ ህግ ተደንግጓል። ለዚህ ተግባር ሲባልም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 7(2) እና በምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/19 አንቀጽ 124(2) መሰረት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶችን ፈቃድ የመስጠት፣ የመከታተል፣ የመቆጣጠር ሥልጣን ተሰጥቶታል። በዘህ የህግ አግባብ መሰረትም ሕብረት ለምርጫ ከምርጫ ቦርዱ እውቅናና ፈቃድ ወስደው በመራጮች እና ስነ-ዜጋ ትምህርት ተግባር ላይ ተሰማርተው የነበሩ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች  የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ እንቅስቃሴን የሚታዘቡ ታዛቢዎችን አሰማርቶ ነበር።

ስለሆነም ሕብረት ለምርጫ ከሰኔ 1 ቀን 2024 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2024 ድረስ  የመራጮች እና ስነ-ዜጋ ትምህርት አሰጣጥ ሂደትን የሚከታተሉ 13 የረዥም ጊዜ ታዛቢዎች (LTOs) በአራቱም ክልሎች (ቢንሻጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ እና ሶማሌ ክልሎች) ለተካሄዱት የቀሪ እና የድጋሚ ምርጫዎች ታዛቢዎችን አሰማርቶ ነበር። ተሰማርተው ከነበሩት የረዥም ጊዜ ታዛቢዎች (LTOs) ሪፖርቶች መካከል 2/3ኛው  የሪፖርት ግኝቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ የመራጮች ትምህርት እና ስነ-ዜጋ ትምህርት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድም እና የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች አማካኝነት ሲሰጥ ነበር። በአንፃሩ ደግሞ ከሪፖርቶቹ ሩብ የማይሞሉት ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት አለመሰጠቱን ያሳያሉ።

የተለያዩ የጥናት ግኝቶች እንደሚጠቁሙት  “ከፍተኛ የመራጮች ተሳትፎ በከፍተኛ የመራጮች ትምህርት ላይ የተመሰረተ ነው”። በሌላ አነጋገር በመራጮች ትምህርት ድግግሞሽ እና በመራጮች ተሳትፎ መካከል ቀጥተኛ የሆነ ትስስር አለ።  ይህ ማለትም በተደጋጋሚ የመራጮች ትምህርትን ለዜጎች ተደራሽ ማድረግ ዜጎች በምርጫ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ከፍ እንዲል ያደርገዋል ማለት ነው። የመራጮች ትምህርት ተደራሽነትን በተመለከተ ሕብረቱ ያሰማራቸው የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች (LTOs) የምልከታ ግኝቶች ከግማሽ በታች የሚሆኑት የመራጮች ትምህርት በሳምንት አንድ ጊዜ ወይም አንድ ጊዜ ብቻ መሰጠቱን ያሳያሉ። በሌላ በኩል 5(16%)  ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ዞን ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት አልተሰጠም።

የመራጮች ትምህርት የመምረጥ ዕድሜ ላሉ ሁሉም ግለሰቦች  በትክክል ተደራሽ መሆን አለበት። በመራጮች ትምህርት ላይ የሚተላለፉ መልዕክቶች ይዘት ሴቶችን፣ አካል ጉዳተኞችን (PWDs) እና የውስጥ ተፈናቃይ ማህበረሰቦችን (Internally displaced people (IDPs)) ታሳቢ ያደረጉና አካታች መሆን አለባቸው። ይህንን በተመለከተም በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሲሰጥ የነበረው የመራጮች ትምህርት ይዘት እነዚህን ትኩረት የሚሹ የማህበረስብ ክፍሎች (ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ተፈናቃዮች) አካታችነትን ታሳቢ ያደረገ መሆን ወይም አለመሆኑን፤ እንዲሁም እነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች በሂደቱ ላይ መሳተፋቸውን ወይም አለመሳተፋቸውን በተመለከተ ሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ሲከታተሉ ቆይተዋል።

13 https://www.un.org/womenwatch/osagi/wps/publication/Chapter5.htm
14 ዝኒ ከማሁ

በዚህም መሰአለመሆኑን ሲገልፁ፤ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የሪፖርት ግኝት ደግሞ የመራጮች ትምህርት አካታች እንደነበር ያሳያል። የሪፖርቱ አንድ ስድስተኛው የሚሆነው ግኝት ደግሞ ምንም አይነት የመራጮች ትምህርት አለመሰጠቱን ያሳያል። ግማሽ የሚጠጋው ግኝት ደግሞ የመራጮች ትምህርት እንዳልተሰጠ ወይም ደግሞ ቢሰጥም ሁሉን ባሳተፈ መልኩ እንዳልተሰጠ ያመለክታል። ከሪፖርቶቹ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ደግሞ የመራጮች ትምህርት በወንዶችና በሴቶች እንዲሁም በአካል ጉዳተኞች እና ተፈናቃዮች መሰጠቱን ያሳያሉ። አንድ ሶስተኛው የሚሆነው የሪፖርት ግኝት ደግሞ የመራጮች ትምህርት ጨርሶ እንዳልተሰጠ ወይም ቢሰጥም በሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች እና ተፈናቃዮች ያልተሰጠ መሆኑን ያሳያል።

መራጮች የመምረጥ መብታቸውን ለመጠቀም ያስችላቸው ዘንድ ያላቸውን መብቱንና ግዴታ ማወቅ አለባቸው። መራጮች ድምፃቸውን በተገቢው መንገድ ለመስጠት እና በምርጫው ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ለማድረግ ስለመብታቸውና ግዴታቸው በተለይም ስለምርጫውና ድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ አስፈላጊውን መረጃ እና ግንዛቤ መያዝ አለባቸው። ስለሆነም የመራጮች ትምህርት መልእክቶች ዋና ዋና ይዘቶች መራጩ ስላሉት ስለመብቶች እና ግዴታዎች እንዲሁም ለምርጫ ሂደቱ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን ማለትም የመራጮች የምዝገባ ጊዜና ምዝገባ የሚያበቃበት ጊዜ እና የድምፅ መስጫ ቀን መሆን አለባቸው። በተጨማሪም መራጮች ለመራጭነት ምዝገባ እና ድምጽ ለመስጠት የሚያስፈልጓቸውን ወይም ማሟላት ያለባቸውን መስፈርትችና ሰነዶች፣ መቼ እና የት መመዝገብና ድምፅ መስጠት እንዳለባቸው፣ ስለድምፅ አሰጣጥ ሂደቱና የድምፅ መስጫ ሳጥኖች አጠቃቀም በመራጮች ትምህርት ይዘት ውስጥ መካተት አለበት። ይህንን በተመለከተም ሕብረት ለምርጫ ያሰማራቸው አብዛኞቹ የረጅም ጊዜ ታዛቢዎች (LTOs) መረጃ እንደሚያሳየው የመራጮች ትምህርት ዋና ይዘት ስለ ምርጫው ቀን እና መራጮች ለምዝገባ እና በድምፅ መስጫ ቀን አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ዝርዝር መረጃዎችን ተደራሽ አድርገዋል።

የመራጮችን ትምህርት እና የስነ-ዜጋ ትምህርትን በማዳረሱ ሂደት ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች በመራጮች ትምህርት ጥራት እና ተደራሽነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። በዚህም ምክንያት ከሚከሰቱ ችግሮች መካከልም የመራጮች ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፣ ዋጋ የሌላቸው ድምጽ እና የሚበላሹ ድምፆች መበራከት፣ እና ከምርጫ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች እና ሌሎችንም ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ የኅብረት ለምርጫ ግኝት ለሴቶች፣ የአካል ጉዳተኞች እና ድጋፍ ለሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎች ተደራሽ አለመሆን እና በቂ የገንዘብ ድጋፍ አለመኖር በመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ ዋና ተግዳሮቶች እንደነበሩ አሳይቷል። በተጨማሪም የቋንቋ እና የባህል ተግዳሮቶችም የመራጮች ትምህርት ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት ሆነው እንደነበር የታዛቢዎች ግኝቶች ያሳያሉ።

## የምርጫ ዘመቻዎች

አብዛኛው የታዛቢዎች ሪፖርት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ መስቃን እና ማረቆ ወረዳ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ በአሶሳ ዞን የሚገኙ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ያለምንም ገደብ ወይም እንቅፋት የምረጡኝ ዘመቻቸውን ማካሄዳቸውን እና በዘመቻው ላይ በንቃት መሳተፋቸውን ያሳያል። የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ እጩ ተወዳዳሪዎች ለመራጮች ቃል ከመግባቱ በተጨማሪ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ጸጥታ ነክ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነበር።

ተፎካካሪ ፓርቲዎች ለመራጮቻቸው ተደራሽ ለመሆን የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀማቸውን የሕብረቱ ታዛቢዎች ግኝቶች ያሳያሉ። ከታዛቢዎች ሪፖርቶች መካከል አንድ አምስተኛው(1/5) የሪፖርት ግኝት እንደሚያሣየው ፓርቲዎች የአደባባይ ሰልፍ በማድረግ ቅስቀሳቸውን ሲያደርጉ ነበር። አንድ ስድስተኛው (1/6) ሪፖርት ደግሞ ፓርቲዎች ከመራጮች ጋር የአዳራሽ ውስጥ ስብሰባ በማድረግ እንደ ቀዳሚ የምርጫ ቅስቀሳ ዘዴ አድረገው መጠቀማቸውን ያሳያል። በሌላ በኩል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የታዛቢ ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያዩ ዘዴዎችን (ከአንድ በላይ ዘዴዎችን) በመጠቀም ዘመቻዎችን ያካሄዱ መሆኑን ያሳያሉ። የማህበራዊ ሚዲያ ትስስርሮችን ለምርጫ ዘመቻ መጠቀምን በተመለከተም ፓርቲዎች የነበራቸው ደረጃ አነስተኛ እንደነበር የታዛቢዎች ሪፖርት ያመላከታል።

## የድምፅ መሰጫ ቀን

መራጮችን ከፀሀይ እና ከዝናብ የሚከላከል መጠለያ ማዘጋጀት የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ለምርጫ ሂደቱ መሰረታዊና አስፈላጊ ነገር ነው። በተለይም የምርጫ ሂደቱ የሚከናወነው በዝናባማ ቦታዎች ከሆነ መራጮችን ከዝናብ የሚያስጠልል መጠለያ መኖር እጅግ አሰፈላጊ ነው። በአንጻሩ ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ መራጮችን ከዝናብ ለመጠለል የሚያስችላቸው መጠለያ ካላገኙ ሳይመርጡ እንዲሄዱ የሚያሥገድድ ሲሆን የመራጮችን የመምረጥ የሚነፍግ ይሆናል። ይህንን በተመለከተም የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ሪፖርቶች አብዛኞቹ የምርጫ ጣቢያዎች ለመራጮች መጠለያ የሚሆን በቂ ቦታ እንዳልነበራቸው አመላክተዋል።

በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ መሰረት የምርጫ ቦርድ ሶስት አባላት ያሉት የምርጫ ጣቢያ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንዲያቋቁም ስልጣን ሰጥቶታል። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ዋና አስፈላጊነትም በምርጫ ጣቢያዎች የሚፈጠሩ ቅሬታዎችን በጣቢያ ደረጃ እንዲፈቱ ለማስቻል ነው። ከዚህ አኳያም የምርጫ ህጉ ድንጋጌ አንድ መራጭ የመምረጥ መብቱ ከተነፈገ ወዲያውኑ ቅሬታውን ለምርጫ ጣቢያ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ የማቅረብ እና ውሳኔ የማግኘት መብት እንዳለው ይገልጻል። ይህንን በተመለከተም የሕብረት ለምርጫ ታዛቢዎች ግኝቶች በአብዛኛዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች ቅሬታዎችን ለመስማት የተቋቋሙት ኮሚቴዎች የምርጫ ህጉን መሰረት ያላደረጉ ወይም ሙሉ በሙሉ አለመቋቋማቸውን ያሳያሉ።

በምርጫ ህጉ መሰረት ሁሉም ለመምረጥ የተፈቀደለት ዜጋ  እኩል የመምርጥ መብት አለው። ይህ የመምረጥ እኩልነትም መሰረት ያደረገውም "አንድ ሰው አንድ ድምጽ" በሚለው መርህ ላይ ሲሆን የዚህ መርህ አተገባበርም አንድ መራጭ አንድ በላይ ድምጽ እንዳይሰጥ እና ማጭበርበርን ለመቀነስ የሚያስችሉ መከላከያዎችን ማስቀመጥን ያካትታል። ለዚህ ተግባር ሲባልም  የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አንድ መራጭ አንድ ድምጽ ብቻ መስጠቱን ለማረጋገጥ የመራጮችን ጣት በማይለቅ ቀለም ምልክት መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል። ከዚህ ህጋዊ መርህ በተቃራኒ በአፋር በሚገኙ ሶስት የምርጫ ጣቢያዎች እና በአሶሳ አንድ ምርጫ ጣቢያ መራጮች ጣቶቻቸው ላይ በማይለቅ ቀለም ሳይደረግባቸው እንዲመርጡ የተደረገ መሆኑን  ሕብረት ለምርጫ ያሰማራቸው ታዛቢዎች ሪፖርት ያሳያል። ምንም እንኳን እንዲህ አይነቱ የህግ ጥሰት በአንዳድ ጣቢያዎች የተከሰተ ቢሆንም በስፋት ግን ጎልቶ የታየ ችግር አልነበረም።

የምርጫ ሕጉ ብቁ የሆኑ መራጮችን ለመመዝገብ ያስችል ዘንድ ዝርዝር መስፈርቶችን እና ሂደቶችን አስቀምጧል። የምርጫ ህጉ አንድ መራጭ ተመዘግቦ የመራጭነት ካርድ ካወጣ በኋላ የመራጩ ካርዱ  በጠፋበት ወይም ቢበላሸበት ምን መደረግ እንዳለበት መፍትሄዎችን በዝርዝር ያሰቀምጣል። በዚህም መሰረት ማንኛውም መራጭ የመራጭነት ካርዱ የጠፋበት ወይም የተበላሸ በምርጫ ጣቢያው በአካል በመገኘት የማመልከት መብት እንዳለው ይገልፃል። በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ አስፈፃሚዎች የመራጩን (አመልካቹን) ማንነት በመራጭ መዝገብ ላይ ካረጋገጡ በኋላ ጉዳዩን በቃለ-ጉባኤ በከመዘገቡ በኋላ መራጩ (አመለካቹ) ምትክ ካርድ ይሰጠዋል (የመራጮች ምዝገባ ካልተጠናቀቀ) ወይም በምርጫው እለት ከሆነ ደግሞ ጉዳዩን በቃለ-ጉባኤ በመያዝ መራጩ እንዲመርጥ ማድረግ የሚያስችላቸውን ስልጣን ለምርጫ  ጣቢያ አስፈፃሚዎች ይሰጣል። ከእነዚህ  ህጋዊ አሠራሮች በተቃራኒ በአሶሳ ዞን በሚገኙ ሁለት የምርጫ ጣቢያዎች ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ያልተገኙ ግለሰቦች በአካል ጉዳተኝነት ወይም በእድሜ ምክንያት እንዲመርጡ ተደርጓል።

የምርጫ ህጉ አንድ መራጭ  መምረጥ የሚችለው የመራጭነት ካርዱን ከያዘ፣  የመራጩ ስም በመራጮች መዝገብ ዝርዝር ውስጥ ሲገኝ ፣ እንዲሁም ቀደም ሲል ድምጽ እንዳልሰጠ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። እነዚህን መመዘኛዎች ብቻ ማሟላት የመራጭነት መብትን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን  መራጩ በተመዘገበበት የምርጫ ጣቢያ ድምጹን እንዲሰጥ ያስችለዋል። ከእነዚህ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎች ወይም መስፈርቶች በተቃራኒ በአፋር ክልል በአንድ የምርጫ ጣቢያ በርካታ ግለሰቦች የማንነት ማረጋገጫም ሆነ የምስክሮች ቃል ሳይቀርቡ እንዲመርጡ ተደርጓል።

## ድህረ-ምርጫ

በአንድ የምርጫ ሂደት የሲቪክ ምህዳሩ ወሳኝ ሚና አለው። በተለይም በጋዜጠኞች፣ በታዛቢዎች እና በሲቪል ማህበረሰብ  ድርጅት ሰራተኞች ላይ የሚደረግ ገደብ፣ ተቃውሞ እና ወከባ አለመኖሩ ጤናማና ዲሞክራሲያዊ  የምርጫ ሂደት እንዲኖር ከማስቻሉም በላይ በምርጫ ሂደቱ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና ነፃ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ያስችላል። ይህንን መሰል  ሰላማዊ የሆነ ከባቢ  ሊኖር የሚችለውም ያልተገደበ የሲቪክ ምህዳር ሲኖርና የባለድርሻ አካላት እንቅስቃሴም  ያልተገደበና ከስጋት ነፃ ሲሆኑ ነው፡፡

በምርጫው ውጤት ላይ  የነበረውን ቅቡልነት በተመለከተ የህዝብ አስተያየት በአብዛኛው አወንታዊ እና  እርካታን የሚያንፀባርቁ የነበረ ቢሆንም በአንፃሩ አነስተኛም ቢሆን ሂደቱ ያለመርካት እና የቅቡልነት ችግር እንደነበር ተመላክቷል።  ምንም እንኳን በአብዛኛው የህዝብ አስተያየት አዎንታዊ ቢሆንም ትክክለኛ መረጃን ከማሰራጨት  ወይም ተደራሽ ከማድረግ ጋር የተያያዙ ጉልህ ተግዳሮቶች እንደነበሩ የትዝብት ግኝቶች ያሳያሉ።  ከዚህ ጋር ተያይዞም በአንዳንድ የመገናኛ ብዙኃን የተሰራጩ ዘገባዎች የተጋነኑ ወይም የተሳሳቱ መረጃዎች  እንደነበሩ ይህም  ሕዝቡ በምርጫ ሒደቱ ላይ ባለው አመኔታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ነበር።  ከዚህ በተጨማሪም የምርጫውን ውጤት ይፋ  ማድረግን ወይም ማወጅን   በተመለከተ ከፍተኛ የህግ ጥሰት ተስተውሏል። በምርጫ ህጉ መሰረት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ውጤትን የማወጅ ስልጣን ያለው ብቸኛው አካል ነው።  ከዚህ የህግ ድንጋጌ በተቃራኒ ሰኔ 16 ቀን 2016 የጅግጅጋ ከንቲባ ቦርዱ ውጤት ከመግለጹ በፊት የብልፅግና ፓርቲ አሸንፏል ብለው በፌስቡክ ገፃቸው  ለጥፈዋል። በተጨማሪም ይህ ከንቲባ የእንኳን ደስ አለን ፕሮግራም በጽህፈት ቤታቸው አዘጋጅተው እንደነበር ይህም ምርጫ ቦርድ ይፋ ከመደረጉ በፊት ውጤቱን ቀድሞ በህዝብ ዘንድ ብዥታ ሊፈጥር የሚችልበት እደል ዝግ አይደለም። እንደነዚህ ያሉ ድርጊቶች የምርጫውን ሂደት ትክክለኛነት  በተመለከተ ጥያቄ ከማስነሳት አልፈው ወደ አለመግባባቶች እና ግጭቶች ሊመሩ ይችላሉ።

# ምዕራፍ አምስት፡ መደምደሚያ እና ምክረ-ሃሳቦች

## መደምደሚያ

ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ባልተከናወነባቸው አካባቢዎች እና ድጋሚ ምርጫ እንዲከናወንባቸው በቦርዱ ውሳኔ በተሰጠባቸው የምርጫ ክልሎች ማለትም በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ሶማሌ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች ሰኔ 16 ቀን 2024 የቀሪ ምርጫ እና ድጋሚ ምርጫዎች ተካሂደዋል። የሕብረት ለምርጫ ትዝብት ዋና አላማ ሰኔ 16 ቀን 2024 በአራቱም ክልሎች የተካሄዱትን የቀሪ ምርጫ እና ድጋሚ ምርጫዎች ተዛቢዎቹን አሰማርቶ ስልታዊ(systematic) በሆነ እና በተደራጀ መንገድ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማቅረብ በተካሄዱት ምርጫዎች ላይ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ነው።

በእነዚህ የቀሪ እና የድጋሚ ምርጫዎችን በመታዘብ ለማሳካት ከተወመጡት ዓላማዎች መካከል የሕብረቱን ምልከታ ዘዴን ማሻሻል፣ በታዛቢዎች ምልመላ፣ ስልጠና እና ማሰማራት ሂደት ላይ የበለጠ ልምድ መቅሰም እና የታዛቢ ግኝቶችን መሰብሰብ፣ መተንተን እና ሪፖርት ማድረግ ይገኙበታል። የሕብረት ለምርጫ የትዝብት ግኝቶች እንደሚያሳዩት የምልከታ ግኝት በአራቱም ክልሎች የተካሄዱት የቀሪ እና ድጋሚ ምርጫዎች ሰላማዊ ነበሩ። ሕብረቱ ታዛቢዎቹን ባሰማራባቸው የምርጫ ጣቢያዎችን የድምፅ መስጫ ቁሳቁሶችን ሙሉ በሙሉ መቅረባቸውን፣ የምርጫ ጣቢያዎችን ለአካል ጉዳተኞች፣ ለነፍሰ ጡር ሴቶች እና ለአረጋውያን ተደራሽ በማድረግ እንዲሁም በምርጫ ህጉ መሰረት አምስት የምርጫ አስፈፃሚዎችን በመመደብ ረገድ መሻሻል መታየቱን መታዘብ ተችሏል። እነዚህን መሰል መልካም ግኝቶች የነበሩ ቢሆንም የምርጫ ቦርድን ትኩረት እና ክትትል የሚሹ የህግ ጥሰቶችና ጉድለቶችም እንደነበሩ ሕብረት ለምርጫ አግኝቷል።

## ምክረ-ሃሳቦች

በተለምዶ ምርጫ ሲባል እንደ ዑደት ወይም ቀጣይነት ያለው ሂደት (Cycle) ሳይሆን የአንድ ቀን ተግባር ተደርጎ ይወሰዳል። በተመሳሳይም የስነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርት መርሃ ግብሮች ዝግጅቶች እና ትግበራዎች ብዙውን ጊዜ በምርጫ ዓመት ወይም ምርጫ ሲቃረብ ብቻ የሚከናወኑ ተግባራት አድርገን እንወስዳቸዋለን። ምንም እንኳን ህብረተሰቡ ስለ መብቱ፣ ግዴታው እና በምርጫ ሂደት የመሳተፍ አስፈላጊነትን እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን በተመለከተ ቀጣይነት ባለው መልኩ ማስተማርና ግንዛቤ ማስጨበጥ ተገቢ ቢሆንም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ግን በየአራት እና አምስት አመት አንዴ ወይም ምርጫ ሲመጣ ብቻ እየተከወኑ ይገኛሉ። የሕብረት ለምርጫ የትዝብት ግኝቶች እንደሚያሳዩት ሲሰጡ የነበሩት የመራጮች ትምህርት አጥጋቢ የሚባሉ አልነበሩም። ከዚህ ጋር ተያይዞ የጊዜ እጥረት፣ የመራጮች ትምህርት የሚሰጥበት የስነ-ዘዴ ውስንነት (የተለያዩ ዘዴዎችን አለመጠቀም)፣ ትኩረት የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን (አካል ጉዳተኞች፣ ሴቶችና ተፈናቃዮች) በማካተት ሂደት ላይ ውስንነት መኖር፣ አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች አለመሟላት እና በመራጮች ትምህርት ይዘትና ተደራሽነት ላይ የሚስተዋሉ ውስንነቶች መኖር በስነ-ዜጋና በመራጮች ትምህርት ተደራሽነት ላይ የተስተዋሉ ተግዳሮቶች ናቸው። ስለሆነም እነዚህን መሰል ተግዳሮቶችና ድክመቶች በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ለመቅረፍ ያስችል ዘንድ ሕብረት ለምርጫ የሚከተሉትን ምክረ-ሃሰቦች ያቀርባል።

- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የመራጮች ትምህርትን በመንደር ደረጃ ተደራሽ ለማድረግ ያስችላቸው ዘንድ በየአካባቢያቸው (በመንደር ደረጃ) ስልጠና የሚሰጡ ቡድኖችን ማቋቋም እና ስልጠና መስጠት አለባቸው።
- ወጣቱን ክፍል (በተለይም ተማሪውን) ለመድረስ እንዲቻል በሥነ ዜጋ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ የመራጮች ትምህርትን ማካተት ያስፈልጋል። ይህም ወጣት መራጮችን በቀላሉ ለመድረስ የሚያስችል ወጪ ቆጣቢ ዘዴ ነው።
- ምርጫ ቦርድ እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የየአካባቢውን ቋንቋ የሚጠቀሙ የማህበረሰብ ሬዲዮኖችን መጠቀም የመራጮች ትምህርትን ለገጠሩ ማህበረሰብ ተደራሽ ማድረግ አለባቸው።
- የመራጮች ትምህርት በተቻለ መጠን ለብዙሃኑ ተደራሽ እንዲሆን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አማራጮችን ማለትም በ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ማህበራዊ ሚዲያዎች፣ የህትመት ውጤቶች አማካኝነት እና ፊት ለፊት (በአካል) መሰጠት አለበት።
- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ከአንድ ምርጫ እስከ ሌላ ምርጫ ድረስ የስነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርትን ለማካሄድ የሚያስችል በቂ ገንዘብ መመደብ አለበት።
- ዓለም አቀፍ አጋሮች እና ለጋሽ ድርጅቶች አስቸጋሪና በገጠር አካባቢዎች የስነ-ዜጋና የመራጮች ትምህርት ለማካሄድ የተለያዩ ዘዴዎችን ቀይሰው ተደራሽ ለማድረግ ቁርጠኛ ለሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።
- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ጣቢያዎችን ሲያደራጅ መራጮችን ከዝናብና ከፀሃይ የሚከላከል መጠለያ ማቋቋምን እንደ አንድ ዋና የሥራው አካል አድርጎ ሊመለከተው ይገባል።

- በምርጫ ጣቢዎች የሚመደቡ ሴት  የምርጫ አስፈፃሚዎችን ከወንድ የምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር እኩል ለማድረግ ጥረት መደረግ አለበት።
- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የመራጮች እና የእጩ ተወዳዳሪዎች መብቶች ለማክበር እና ለመጠበቅ ጉዳያቸው እንዲሰማ በምርጫ ህጉ መሰረት በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንዲቋቋም  ማድረግ አለበት።
- የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ሕጉን በግልፅ ጥሰው የተገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች ላይ የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል። እንዲሁም  እንደነዚህ አይነት ሕገ-ወጥ የሆኑ አሰራሮች ዳግም እንዳይከሰት ለማድረግ እንዲረዳ በምርጫ አስፈጻሚዎች ስልጠና ወቅት በአጥፊዎች ላይየተወሰዱ እርምጃዎችን  ሰልጣኞች እንዲያውቁት ማድረግ አለበት።

# ስለ ኅብረት ለምርጫ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) ከ175 በላይ የሆኑ አገር በቀል የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ሲሆን፤ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። ኅብረት ለምርጫ በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት፣ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በመዝገብ ቁጥር 4748 በ2011 ዓ.ም ሕጋዊ ሰውነቱን ያገኘ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ነው።

ኅብረት ለምርጫ የተመሰረተበት ዋና አላማ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በምርጫ ምልከታ እና ክትትል፣ በመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ዙሪያ እና ከምርጫ በኋላ ሊከሰቱ የሚችሉ ግጭቶችን በመከላከል ላይ ያላቸውን ሚና ለማስተባበር እና ለማሳደግ ነው። ኅብረት ለምርጫ የምስራቅ እና የአፍሪካ ቀንድ የምርጫ ታዛቢዎች ኔትወርክ (East and Horn of Africa Election Observers Network (E-HORN)፣ የመላው አፍሪካ የምርጫ ታዛቢዎች አስተባባሪ መድረክ የሆነው የአፍሪካ የምርጫ ታዛቢዎች ኔትወርክ (African Election Observers Network (AfEONet) አባል እና በዓለም ዙሪያ ከ88 ሃገራት በላይ ቀጠናዊ ትስስር እና ድርጅቶችን አገናኝ ድርጅት የሆነው የአለም አቀፍ የሀገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች ኔትወርክ (Global Network of Domestic Election Monitors (GNDEM)) አባል ነው።

# ማሳሰቢያ

ይህ ሪፖርት ሊሳካ የቻለው በአየርላንድ ኤምባሲ እና በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ኤጀንሲ(USAID) ባደረጉት የላቀ የገንዘብ ድጋፍ ነው። በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች ወይም አስተያየቶች የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ እንጂ የአየርላንድ ኤምባሲ፣ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ኤጀንሲ (USAID)፣ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም(NDI) ወይም ሌሎች አጋር ድርጅቶችን አቋም እና ምልከታ የሚያንፀባርቁ አይደሉም።

---

**ስድስት ኪሎ፣ ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢኒስቲቱውት**
**ሕንጻ 2ኛ ወለል**
**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

**Tel.:+251 11 811 1455**

**Email: info@cecoe.org**